# አካላዊ ትንሣኤ

*1ቆሮ 15፥35 "ነገር ግን 'ሙታን እንዴት ይነሣሉ? የሚወጡትስ በምን ዐይነት አካል ነው?' የሚል ሰው ሊኖር ይችላል።"*

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አካላዊ ትንሣኤ መሠረታዊ አስተምህሮ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሙታንን አካል እንደሚያስነሣ፣ በመካከልም ባለው ጊዜ ተለያይቶ የነበረውን የሰውን ነፍስና መንፈስ ከሥጋው ጋር እንደገና አንድ ማድረጉን የሚያመለክት ነው።

(1) መጽሐፍ ቅዱስ የአካላዊ ትንሣኤን አስፈላጊነት ለመግለጽ ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉትን ሦስት ምክንያቶች አቅርቦአል፤ (ሀ) ሥጋዊ አካል ለሰው ልጅ አጠቃላይ ሰብእና እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ሰዎችም ያለ ሥጋዊ አካል ሙሉ አይሆኑም። ስለዚህ የክርስቶስ ቤዛነት ሥጋዊ አካልን ጨምሮ ለሰው ሁለንተና ሙሉ ደህንነት የሚሆን ስጦታ ነው (ሮሜ 8፥18-25 እንዲሁም በገጽ 981 ላይ፣ "ሰውና ሰብእናው" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (ለ) ሥጋዊ አካል የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው (1ቆሮ 6፥19)፤ በትንሣኤ ጊዜም እንደገና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ይሆናል። (ሐ) በማንኛውም ደረጃ ያለውን የኀጢአት ውጤት ለመሻር፣ የሰው የመጨረሻ ጠላት የሆነው ሥጋዊ ሞት በትንሣኤ አማካይነት መሸነፍ አለበት (1ቆሮ 15፥26)።

(2) ብሉይ ኪዳንና (ዘፍ 22፥1-14 ከዕብ 11፥17-19፤ መዝ 16፥10 ከሐሥ 2፥24 — ጋር ያወዳድሩ፤ ከኢዮ 19፥25-27፤ ከኢሳ 26፥19፤ ከዳን 12፥2፤ ከሆሴ 13፥14 ጋር ያነጻጽሩ) አዲስ ኪዳን ሁለቱም (ሉቃ 14፥13-14፤ 20፥35-36፤ ዮሐ 5፥21፡28-29፤ 6፥39-40፡44፡54፤ 1ቆሮ 15፥22-23፤ ፊል 3፥11፤ 1ተሰ 4፥14-16፤ ራእ 20፥4-6፡13) ወደፊት ስለሚሆነው አካላዊ ትንሣኤ ያስተምራሉ።

(3) የእኛ አካላዊ ትንሣኤ እውን እንደሚሆን በክርስቶስ ትንሣኤ ተረጋግጦአል (ማቴ 28፥6 ማብ፤ ሐሥ 17፥31፤ 1ቆሮ 15፥12፡20-23 ይመ)።

(4) በአጠቃላይ አነጋገር አካላዊ ትንሣኤ የሚያገኘው የአማኝ አካል የክርስቶስ አካል ራሱ ያገኘውን አካላዊ ትንሣኤ ይመስላል (ሮሜ 8፥29፤ 1ቆሮ 15፥20፡42-44፡49፤ ፊል 3፥20-21፤ 1ዮሐ 3፥2)። ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድ አካላዊ ትንሣኤን የሚያገኘው ሥጋ የሚከተለውን ይመስላል፤ (ሀ) በዚህ የሕይወት ዘመን ያለውን አካል የሚመስልና ቀጣይነት ያለው ሲሆን፣ ተለይቶም የሚታወቅ ነው (ሉቃ 16፥19-31)፤ (ለ) ለአዲሲቱ ሰማይና ለአዲሲቱ ምድር እንዲስማማ ተደርጎ ወደ ሰማያዊ አካል የተለወጠ ነው (1ቆ 15፥42-44፡47-48፤ ራእ 21፥1)፤ (ሐ) ከመበስበስና ከሞት ነጻ የሆነ የማይጠፋ አካል ነው (1ቆሮ 15፥42)፤ (መ) እንደ ክርስቶስ አካል የከበረ አካል ነው (1ቆሮ 15፥43፤ ፊል 3፥20-21)፤ (ሠ) ለበሽታ ወይም ለድካም የማይጋለጥ ብርቱ አካል ነው (1ቆሮ 15፥43)፤ (ረ) በተፈጥሮ ሕግ የማይገዛ መንፈሳዊ ማለትም ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ዲበ ተፈጥሮአዊ አካል ነው (ሉቃ 24፥31፤ ዮሐ 20፥19፤ 1ቆሮ 15፥44)፤ (ሰ) መብላትና መጠጣት የሚችል አካል (ሉቃ 14፥15፤ 22፥14-18፡30፤ 24፥43)።

(5) አማኞች አዲሱን አካላቸውን ሲቀበሉ የማይሞተውን ይለብሳሉ (1ቆሮ 15፥53)። ቅዱሳት መጻሕፍት ቢያንስ ቢያንስ ለዚህ የሚከተሉትን ሦስት ዐላማዎች ያመለክታሉ፤ (ሀ) አማኞች ሁሉ እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ፈጠረበት ዐላማ እንዲደርሱ ነው (ከ1ቆሮ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ለ) አማኞች ሙሉ በሙሉ እርሱን እንዲያውቁት በሚፈልገው ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዲያውቁት ነው (ዮሐ 17፥3)፤ (ሐ) እግዚአብሔር እርሱ እንደሚፈልገው ፍቅሩን ለልጆቹ እንዲገልጽ ነው (ዮሐ 3፥16፤ ኤፌ 2፥7፤ 1ዮሐ 4፥8-16)።

(6) ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ እርሱን በመከተል በሕይወት ያሉ ታማኞች ከትንሣኤ ቀን በፊት በክርስቶስ የሞቱ የጌታ ተከታዮች ያገኙትን አካላዊ ለውጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ይቀበላሉ (1ቆሮ 15፥51-53)። በዚያን ጊዜ ከሞት የተነሡት ቅዱሳን ያለበሱትን አዲስ ዐይነት አካል እነርሱም ይለብሳሉ። ሥጋዊ ሞትን ፈጽሞ አይሞቱም (በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የተኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(7) ኢየሱስ ክርስቶስ ለአማኞች የሕይወት ትንሣኤ እንደሚሆንላቸው ለኀጥአን ደግሞ የፍርድ ትንሣኤ እንደሚመጣባቸው ተናግሮአል (ዮሐ 5፥28-29)።

42የሙታን ትንሣኤም እንደዚሁ ነው፤
የሚበሰብስ አካል ይዘራል፤ የማይበሰብስ
አካል ሆኖ ይነሣል፤ 43በውርደት ይዘራል፤
በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል በኀይል
ይነሣል፤ 44ፍጥረታዊ አካል ይዘራል
መንፈሳዊ አካል ይነሣል።
ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል
ደግሞ አለ። 45ስለዚህ፣ "የመጀመሪያው ሰው
አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ" ተብሎ ተጽፎአል፤
የኋለኛው አዳም ግን ሕይወትን የሚሰጥ
መንፈስ ሆነ። 46ነገር ግን በመጀመሪያ
የመጣው መንፈሳዊው ሳይሆን ፍጥረታዊው
ነው፤ ከዚያም በኋላ መንፈሳዊው መጣ።
47የመጀመሪያው ሰው ከምድር የተገኘ
ምድራዊ ነው፤ የኋለኛው ግን ከሰማይ
ነው። 48ከምድር የሆ ኑት እንደ ምድራዊው
ናቸው፤ ከሰማይ የሆኑትም እንደ ሰማያዊው
ናቸው። 49የምድራዊውን ሰው መልክ እንደ
ለበስን፣ የሰማያዊ ውን ሰው መልክ ደግሞ
እንለብሳለን።*
50ወንድሞች ሆይ፤ ይህን እነግራችኋለሁ፤
ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት
አይወርሱም፤ የሚጠፋውም የማይጠፋውን
አይወርስም። 51እነሆ፤ አንድ ምስጢር
እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም፤
ነገር ግን ሁላችንም እንለወጣለን፤
52ይህም የሚሆነው የመጨረሻው መለከት
ሲነፋ ድንገት በቅጽበተ ዐይን ነው።
መለከት ይነፋል፤ ሙታን የማይበሰብሱ
ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን።
53የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተው
የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።
54የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተውም
የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ፣ "ሞት
በድል ተዋጠ" ተብሎ የተጻፈው ቃል
ይፈጸማል።
55እንዲሁም፣ "ሞት ሆይ፤ ድል መንሣትህ
የት አለ?
ሞት ሆይ፤ መንደፊያህስ የት
አለ?"።
56የሞት መንደፊያ ኀጢአት ነው፤ የኀጢ
አትም ኀይል ሕግ ነው። 57ነገር ግን በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን ለሚ
ሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።
58ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤
ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ።
ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤
ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ
እንዳልሆነ ታውቃላችሁ።

## ለቅዱሳን የተደረገ የገንዘብ መዋጮ

16 አሁን ደግሞ ለቅዱሳን ስለሚደረገው
ገንዘብ ማሰባሰብ፤ ለገላትያ አብያተ
ክርስቲያናት በሰጠሁት ትእዛዝ መሠረት
አድርጉ። 2ገንዘብ ማሰባሰብ የሚደረገው
እኔ በምመጣበት ጊዜ እንዳይሆን፣
ከእናንተ እያንዳንዱ እንደ ገቢው መጠን
በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን እየለየ ያስቀምጥ።
3በምመጣበት ጊዜ እናንተ ለመረጣችኋቸው
ሰዎች የመሸኛ ደብዳቤ ሰጥቼ ስጦታችሁን
ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያደርሱ
እልካቸዋለሁ። 4የእኔ መሄድ የሚያስፈልግ
ከሆነ አብረውኝ ይሄዳሉ።

## የሐዋርያው ዕቅድ

5በመቄዶንያ በኩል ማለፌ ስለማይቀር፣
መቄዶንያ ከደረስሁ በኋላ ወደ እናንተ
እመጣለሁ። 6ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም
ስፍራ በጕዞዬ እንድትረዱኝ፣ እናንተ ዘንድ
እንደ ይሆናል፤ ምናልባትም ክረምቱን
ከእናንተ ጋር እሰነብት ይሆናል። 7አሁን
እግረ መንገዴን ሳልፍ ልጐበኛችሁ አልፈል
ግም፤ ጌታ ቢፈቅድ ረዘም ላለ ጊዜ እናንተ
ዘንድ ለመሰንበት ተስፋ አደርጋለሁ። 8ነገር
ግን እስከ በዓለ ኀምሳ በኤፌሶን እቆያለሁ፤
9ምክንያቱም ታላቅ የሥራ በር ተከፍቶል
ኛል፤ ብዙ ተቃዋሚዎችም አሉብኝ።
10ጢሞቴዎስ ወደ እናንተ ከመጣ፣

15፥42 ቍ12:50:53:54፤ ዳን12፥3፤ ማቴ13፥43
15፥43 ፊል3፥21፤ ቈላ3፥4
15፥44 ቍ50
15፥45 ዘፍ2፥7፤ ዮሐ5፥21፤ 6፥57:58፤ ሮሜ5፥14፤ 8፥2
15፥46 ቍ44
15፥47 ዘፍ2፥7፤ 3፥19፤ መዝ90፥3፤ ዮሐ3፥13:31
15፥48 ፊል3፥20:21
15፥49 ዘፍ5፥3፤ ሮሜ8፥29
15፥50 ቍ42:53:54፤ ማቴ25፥34፤ ኤፌ6፥12፤ ዕብ2፥14
15፥51 ማቴ9፥24፤ 1ቆሮ13፥2፤ 14፥2፤ 2ቆሮ5፥4፤ ፊል3፥21
15፥52 ማቴ24፥31፤ ዮሐ5፥25
15፥53 ቍ42:50:54፤ 2ቆሮ5፥2:4
15፥54 ኢሳ25፥8፤ ዕብ2፥14፤ ራእ20፥14
15፥55 ሆሴ13፥14
15፥56 ሮሜ4፥15፤ 5፥12
15፥57 2ቆሮ2፥14፤ ሮሜ8፥37፤ ዕብ2፥14:15
15፥58 ኢሳ65፥23፤ 1ቆሮ16፥10
16፥1 ሐሥ9፥13፤ 16፥6፤ 24፥17
16፥2 ሐሥ20፥7፤ 2ቆሮ9፥4:5
16፥3 2ቆሮ3፥1፤ 8፥18:19 16፥5 ሐሥ16፥9፤ 1ቆሮ4፥19 16፥6 ሮሜ15፥24፤ ቲቶ3፥13
16፥7 ሐሥ18፥21 16፥8 ሐሥ2፥1፤ 18፥19
16፥9 ሐሥ14፥27 16፥10 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ15፥58

**15፥49* አንዳንድ የጥንት ቅጆች እንልበስ ይላሉ።

15፥51 **አንድ ምስጢር፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚገልጠው እውነት ኢየሱስ ከመንግሥተ ሰማይ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ራሱ ለመውሰድ ሲመለስ፣ በሕይወት ያሉ አማኞች አካል ድንገት በመለወጥ የማይጠፋና የማይሞት መሆኑን ለማመልከት ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንጥቀት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::
15፥51 **ሁላችን አናንቀላፋም፤** ሐዋርያው ጳውሎስ "እኛ" ሲል ከአዲስ ኪዳን እይታ አንጻር ክርስቶስ ታማኝ ለሆኑት አብያተ ክርስቲያናቱ በራሱ በጳውሎስ ትውልድ እንደሚመጣ ለማመልከት ነው:: ክርስቶስ በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመን ባይመለስም እርሱ እንደዚያ በማመኑ አልተሳሳተም፤ ክርስቶስ በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል ያውቃልና:: ክርስቶስ በራሳቸው ዘመን እንደሚመለስ በተስፋ የሚጠባበቁ ሁሉ የአዲስ ኪዳንን አመለካከት የሚጋሩ ናቸው:: የኢየሱስ ቃልና አዲስ ኪዳን በአጠቃላይ ማንኛውም አማኝ አሁን የመጨረሻው ሰዓት እንደሆነና ክርስቶስ በራሱ ዘመን እንደሚመለስ በማመን መኖር እንደሚገባው አጥብቆ ያስገነዝባል (ከ1፥7-8፤ ከሮሜ 13፥12፤ ከፊል 3፥20፤ ከ1ተስ 1፥10፤ 4፥15-17፤ ከቲቶ 2፥13፤ ከያዕ 5፥8-9፤ ከ1ዮሐ 2፥18:28፤ ከራእ 22፥7:12:20 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 24፥42:44 እና ማብ፤ ሉቃ 12፥35 እና ማብ ይመ):: ስለዚህ ክርስቶስ በራሳቸው ዘመን እንደሚመጣ በማመን የማይጠባበቁ ሁሉ በሐዋርያት መንገድ እየኖሩ አይደሉም::
15፥52 **እኛም እንለወጣለን፤** በገጽ 1810 ላይ፣ *"አካላዊ ትንሣኤ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::
16፥1 **ገንዘብ ማሰባሰብ፤** በምዕራፍ 16 ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ላሉ ድኾች ምእመናን ተገቢውን ገንዘብ ስለማሰባሰብ መመሪያ ሰጥቶአል፤ እንዲሁም ስለ ወደፊት ዕቅዱና በጌታም አብረውት ስለሚሠሩት ሠራተኞች በዝርዝር ተናግሮአል::

አብሮአችሁ ያለ ፍርሀት እንዲቀመጥ
አድርጉ፤ እርሱም እንደ እኔ የጌታን ሥራ
የሚሠራ ነውና። [11]ስለዚህ ማንም አይናቀው፤
በሰ ላም ወደ እኔ እንዲመለስ ርዱት፤ መመለ
ሱንም ከወንድሞች ጋር እየጠበቅን ነው።
[12]ስለ ወንድማችን ስለ አጵሎስ ደግሞ፣
ከወንድሞች ጋር ወደ እናንተ እንዲመጣ
አጥብቄ ለምኜው ነበር፤ እርሱ ግን አሁን
ለመምጣት አልፈለገም፤ ሲመቸው ግን
ይመጣል።
[13]ንቁ፤ በእምነት ጽኑ፤ በርቱ፤ ጠንክሩ፤
[14]የምታደርጉትን ሁሉ በፍቅር አድርጉ።
[15]የእስጢፋኖስ ቤት ሰዎች በአካይያ
የመጀመሪያዎቹ አማኞች እንደ ሆኑና
ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደ ሰጡ
ታው ቃላችሁ። ወንድሞች ሆይ፤ ይህን እለምና
ችኋለሁ፤ [16]እንደ እነርሱ ላሉትና ከእነርሱም
ጋር በአገልግሎት ለሚደክሙ ሁሉ ታዘዙ።
[17]እስጢፋኖስ፣ ፈርዶናጥስና አካይቆስ
በመምጣታቸው ደስ ብሎኛል፤ ምክንያቱም
እናንተ እዚህ ባለመኖራችሁ የጐደለኝን
አሟልተዋል፤ [18]የእኔንም የእናንተንም
መንፈስ አሳርፈዋልና። ስለዚህ እንደነዚህ
ያሉትን ሰዎች መታወቅ ይገባቸዋል።

16፥11 ሐሥ15፥33፣ 2ቆሮ1፥16፣ 1ጢሞ4፥12፣ 3ዮሐ1፥6
16፥12 ሐሥ18፥24
16፥13 1ቆሮ1፥8፣ 2ቆሮ1፥21፣ ገላ5፥1፣ ኤፌ6፥10፣ ፊል1፥27፣ 1ተሰ3፥8፣ ቲቶ1፥9
16፥14 1ቆሮ14፥1
16፥15 ሐሥ9፥13፣ 18፥12፣ 24፥17፣ ሮሜ16፥5፣ 1ቆሮ1፥16
16፥16 1ተሰ5፥12፣ ዕብ13፥17
16፥17 2ቆሮ11፥9፣ ፊል2፥30
16፥18 ሮሜ15፥32፣ ፊል2፥29፣ ፊሞ1፥7
16፥19 ሐሥ2፥9፣ 18፥2፣ ሮሜ16፥5
16፥20 ሮሜ16፥16
16፥21 ገላ6፥11፣ ቈላ4፥18፣ 2ተሰ3፥17፣ ፊሞ1፥19
16፥22 ሮሜ9፥3፣ ኤፌ6፥24፣ ራእ22፥20
16፥23 ሮሜ16፥20

### የመሰናበቻ ቃል

[19]በእስያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ[ሀ]፣
በቤታቸውም ያለችው ቤተ ክርስቲያን የከበረ
ሰላምታ በጌታ ያቀርቡላችኋል። [20]ወንድ ሞች
ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። እርስ በርሳችሁ
በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰ ጣጡ።
[21]ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁላችሁ
እኔ ጳውሎስ ነኝ።
[22]ጌታን የማይወድ ቢኖር የተረገመ
ይሁን። ጌታ ሆይ፤ ና![ለ]
[23]የጌታ ኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር
ይሁን።
[24]ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ
ጋር ነው፤ አሜን።[ሐ]

*[ሀ] 16፥19 በግሪኩ ጵርሲቃ የጵርስቅላ ሌላው አጠራር ነው፡፡*

*[ለ] 16፥22 በአራማይክ ጌታ ሆይ፣ ና ማለት ማራናታ ማለት ነው፡፡*

*[ሐ] 16፥24 አንዳንድ ቅጆች አሜን የሚለው የላቸውም፡*

16፥22 **የተረገመ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክቱን የሚደመድመው አማኞች ነን ብለው የሚናገሩ ነገር ግን ጌታን የማይወዱ ሆነው መገኘታቸው መረገም ወይመ በፍርድ ሥር መሆን እንደ ሆነ በማሳሰብ ነው፡፡ “ጌታን አለመውደድ” ማለት ከልብ የመነጨ ፍቅር ለእርሱ መግለጽ አለመቻል፣ እርሱን አለመታዘዝና (ዮሐ 14፥21) የአዲስ ኪዳን መገለጥ የሆነውን ሐዋርያዊ ወንጌል ማጣመም (ገላ 1፥9 እና ማብ) ማለት ነው፡፡ መረገም ማለት በምድር ላይ ካለችው ከእውነተኛይቱ መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያንና በመጨረሻም ዘመን ከሚገለጠው ከሰማያዊ መንግሥት መወገድ ማለት ነው፡፡ ጳውሎስ አንባቢዎቹ እንዲያስተውሉት የፈለገው የክርስቲያን ደቀ መዝሙር ከፍተኛ ፈተና ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከልብ የመነጨ የግል ታማኝነት የመግለጽ ጉዳይ መሆኑን ነው (ከሮሜ 10፥9 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

16፥22 **ጌታ ሆይ፤ ና** “ማራናታ” የሚለው አረማይክ ቃል የጸሎት ወይም በክርስቲያኖች መካከል የነበረ የሰላምታ አገላለጽ ሊሆን ይችላል፡፡ የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በቶሎ እንዲመጣ ያለማቋረጥ ትጸልይ ነበር፡፡ እውነተኛ ክርስቲያኖች የእርሱን መገለጥ የሚጠባበቁና (2ጢሞ 4፥8) ይህንንም ናፍቆታቸውን በቃልና በሥራ የሚገልጹ ናቸው (1ተሰ 1፥10፣ ራእ 22፥20)፡፡

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች – ሁለተኛ

*አስተዋፅኦ*

መግቢያ (1፥1-11)

I. ታማኞች ስለ ሆኑ ብዙኀን ጳውሎስ ያቀረበው መከላከያ (1፥12—7፥16)
  (ሀ) ከዳተኛ እንዳልነበረ ማስተባበያ መስጠቱ (1፥12-22)
  (ለ) የጉዞ ዕቅዱን ስለ መለወጡ ያቀረበው ገለጻ (1፥23—2፥17)
  (ሐ) የአገልግሎቱን ባሕርይ በተመለከተ የሰጠው ማብራሪያ (3፥1—6፥10)
    1. በአዲስ ኪዳን አገልግሎት ውስጥ ያለ ነው (3፥1-18)
    2. በግልጽነትና በእውነት የሚፈጸም አገልግሎት ነው (4፥1-6)
    3. በግል ሥቃይን በመቀበል የሚፈጸም ነው (4፥7—5፥10)
    4. ርኅራኄን በተሞላ መስጠት የሚፈጸም ነው (5፥11—6፥10)
  (መ) የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ያሳየው ፍቅርና ያቀረበው የግል አቤቱታ (6፥11—7፥16)

II. በኢየሩሳሌም ለነበሩ ችግረኛ ክርስቲያኖች ርዳታ መሰብሰቡ (8፥1—9፥15)
  (ሀ) ለክርስቲያን የተሰጠው የልግስና ጸጋ (8፥1-15)
  (ለ) ቲቶ የርዳታ አሰባሰቡን ሁኔታ መምራቱ (8፥16-24)
  (ሐ) ሌሎችን ለመርዳት ያለው ዝግጁነት (9፥1-5)
  (መ) ሌሎችን በልግስና ለመርዳት ያለው በጎ ምላሽ (9፥6-15)

III. ለጥቂት ዓመፀኞች የተሰጠ የጳውሎስ መልስ (10፥1—13፥10)
  (ሀ) ፍርሃትንና ደካማነትን በተመለከተ ለቀረበበት ክስ የተሰጠ መልስ (10፥1-18)
  (ለ) በሐዋርያነቱ ላይ ለተነሣ ጥያቄ ቅር በመሰኘት ያቀረበው የግል መከላከያ (11፥1—12፥18)
    1. በትምክህት ስለተናገረው ቃል ያቀረበው የይቅርታ ጥያቄ (11፥1-15)
    2. የአይሁድ እምነት ቅሪት ካላቸው ክርስቲያኖች ያነሰ አለመሆኑን አጥብቆ መግለጹ (11፥16—12፥10)
    3. ስለ ሐዋርያነቱ ያቀረበው ሕጋዊ መሠረት (12፥11-18)
  (ሐ) ለሦስተኛ ጊዜ መምጣቱ እንደ ማስጠንቀቂያ መጠቀሱ (12፥19—13፥10)
    1. የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች በተመለከተ ያለው ሥጋት (12፥19-21)
    2. ጸንቶ ለመቆም መወሰኑ (13፥1-10)።

ማጠቃለያ፡ (13፥11-14)

**ጸሐፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በሥቃይ ውስጥ የሚገኝ ክብር*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *55/56 ዓ.ም.*

***ታሪካዊ ዳራ***

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈው በቆሮንቶስ ላለችው ቤተ ክርስቲያንና በመላው አካይያ ላሉ ምእመናን ሲሆን፣ ይህን ያደረገው ራሱን ሁለት ጊዜ በስም በመጥቀስ ነበር (1፥1፤ 10፥1)። በሁለተኛው የወንጌል ጉዞው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ከመሠረተ

በኋላ በቤተ ክርስቲያኒቱ ችግር ስለ ተፈጠረ ጳውሎስና የቆሮንቶስ ምእመናን በተደጋጋሚ ተገናኝተው ነበር (የአንደኛ ቆሮንቶስን መግቢያ ይመ)።

የእነዚህ ግንኙነቶች ተከታታይነትና ሁለተኛ ቆሮንቶስ የተጻፈበት መነሻ ምክንያት እንደሚከተለው ቀርቦአል፤ (1) በእርሱና በቤተ ክርስቲያኒቱ መካከል የመጀመሪያ ግንኙነትና የደብዳቤ ልውውጥ ከተደረገ በኋላ (ለምሳ 1ቆሮ 1፥11፤ 5፥9፤ 7፥1) ሐዋርያው ጳውሎስ አንደኛ ቆሮንቶስን ኤፌሶን ሆኖ ጻፈ (በበልግ ወራት 55 ወይም 56 ዓ.ም)፤ (2) ቀጥሎም ሐዋርያው ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ላለው ችግር መፍትሔ ለመስጠት በኤጂያን ባሕር አቋርጦ ወደ ቆሮንቶስ ተጓዘ። በአንደኛ ቆሮንቶስና በሁለተኛ ቆሮንቶስ መካከል የተደረገው ይህ ጉብኝት (ከ13፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ) ለጳውሎስና ለማኅበረ ምእመኑ እጅግ ከባድ ነበር (2፥1-2)፤ (3) ከዚህ አስጨናቂ ጉብኝት በኋላ በቆሮንቶስ ያሉ ተቃዋሚዎች ምእመናንን በመከፋፈል ጳውሎስን እንዲቃወሙት ተስፋ በማድረግ እርሱንና ሐዋርያዊ ሥልጣኑን በመጋፋት ጥረት እያደረጉ አሁንም እየተቃወሙት እንዳሉ ወሬው ለጳውሎስ ኤፌሶን ሳለ ደረሰው፤ (4) ለደረሰው ወሬ ምላሽ ለመስጠት ጳውሎስ ሁለተኛ ቆሮንቶስን መቄዶንያ ሆኖ ጻፈ (55 ወይም 56 ዓ.ም. ማብቂያ)፤ (5) ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጳውሎስ እንደ ገና ወደ ቆሮንቶስ ተጉዞ እዚያ ሦስት ወር ያህል ተቀመጠ (ከሐሥ 20፥1-3ሀ ጋር ያነጻጽሩ)፤ በዚያ ተቀምጦም የሮሜን መልእክት ጻፈ።

## ዐላማ

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው በቆሮንቶስ ላሉት ለሚከተሉት ሦስት የሕዝብ ክፍሎች ነው፤ (1) በመጀመሪያ ለእርሱ ታማኝ የሆኑትንና እርሱንም መንፈሳዊ አባታቸው አድርገው የሚቈጥሩትን ብዙኀኑን ለማጽናናት ነው፤ (2) ሥልጣኑንና ሐዋርያነቱን ለማጣጣል እርሱን በግል መቃወምን በመቀጠል እንዲሁም መልእክቱን በማጣመም የሚናገሩትን ሐሰተኛ ሐዋርያት ለማጋለጥና የሐሰት ትምህርታቸውንም ለመቃወም ነው፤ (3) የሐዋርያው ጳውሎስን ተቀናቃኞች ሐሳብ በመቀበል የእርሱን ሥልጣንና ምክር የሚቃወሙትን በቤተ ክርስቲያን ያሉትን ጥቂቶችን ለመገሠጽ ነው። ሐዋርያው የልቡን ፍላጎት ግልጽ በማድረግ ታማኝነቱንና ሐዋርያዊ ሥልጣኑን እንደገና አረጋገጠ፤ ከዚህ በኋላም እንዳያምፁ ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው። ሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክት ጳውሎስ በቅርቡ ሊያከናውነው ላሰበው ጉብኝት ቤተ ክርስቲያኗን ለማዘጋጀት የተጻፈ ነው።

## ቅኝት

ሁለተኛ ቆሮንቶስ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፤ (1) በመጀመሪያ (ምዕ 1—7) ጳውሎስ ስለ ወንጌል መከራን እየተቀበለ ባለበት ጊዜ ከእርሱ ስላገኘው ማጽናናት አምላኩን እግዚአብሔርን በማመስገን ይጀምራል (ምዕ 1—7)፤ ክፉ ነገር በፈጸመው ሰው ላይ ስለ ወሰዱት የሥነ ሥርዐት እርምጃ የቆሮንቶስ ሰዎችን ያደንቃል፤ የጉዞ ዕቅዱንም መለወጡ ለፈጠረው ጥያቄ ስለ ራሱ ታማኝነት መከላከያን ያቀርባል። በ3፥1-6፥10 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰፊ ቦታ ስለ ተሰጠው ስለ እውነተኛ የክርስቲያን አገልግሎት ባሕርይ ያስተምራል። ከዓለም መለየት እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነ በአጽንዖት በመናገርና (6፥11—7፥1) በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብሎ በእርሱ ሥልጣን ላይ ዐምፀው ከነበሩት ብዙዎቹ ንስሐ መግባታቸውን ከቲቶ ሰምቶ ደስታውን በመግለጽ የመጀመሪያውን ክፍል አጠቃሎአል።

(2) በምዕራፍ 8—9 ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በችግር ላይ ላሉት ክርስቲያኖች በሚያሰባስበው ርዳታ የመቄዶንያ ክርስቲያኖች ያሳዩትን የልግስና መዋጮ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም እንዲያደርጉት አጥብቆ ይመክራል።

(3) ከምዕራፍ 10—13 ያለው የመልእክቱ መንፈስ ተለውጦአል። በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የተጠራበትን ጥሪ፣ ስጦታውንና እንደ እውነተኛ ሐዋርያ የተቀበለውን መከራ ገልጦ በማሳየት ስለ ሐዋርያነቱ መከላከያ አቅርቦአል። በዚህም የቆሮንቶስ ሰዎች በመካከላቸው ያሉትን ሐሰተኛ ሐዋርያት እንደሚለዩና እርሱም እንደ ገና በአካል በመካከላቸው ሲገኝ ከግጭ እንደሚድኑ ተስፋ ያደርጋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለተኛ ቆሮንቶስን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባለው በአንዱ ሥላሴን በሚያመለክተው ቡራኬ ያጠቃልለዋል (13፥14)።

## ልዩ ገጽታዎች

ሁለተኛ ቆሮንቶስን ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ሐዋርያው ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ ስለ ራሱ የሕይወት ታሪክ በይበልጥ የሚያመለክት

ነው:: ስለ ራሱ የግል ታሪክ የተጠቀሰው ግልጽ በሆነ ትሕትና፣ ይቅርታን በመጠየቅና፣ ቅር የተሰኘበትን ሁኔታ እንኳ በማመልከት ነበር፣ ይህን እንዲያደርግ ያስገደደውም በቆሮንቶስ የነበረው እጅግ አስከፊ ሁኔታ ነው:: (2) ከሌሎቹ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ይልቅ ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ልጆቹ ያለውን ፍቅርና ሐሳብ በስፋትና በጥልቀት የሚያመለክት ነው:: (3) በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ክርስቲያን ስለሚቀበለው መከራ (1፥3-11፣ 4፥7-18፣ 6፥3-10፣ 11፥23-30፣ 12፥1-10) እና ክርስቲያን ሁሉ መፈጸም ስለሚገባው የመስጠት አገልግሎት (ምዕ 8—9) በሚመለከት የተጻፈውን እጅግ የዳበረ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት የያዘ ነው:: (4) የዚህን መልእክት ልዩ ባሕርይ በትኩረት የሚያሳዩ እንደ ድካም፣ ሐዘን፣ እንባ፣ ዐደጋ፣ ጭንቀት፣ መከራ፣ መጽናናት፣ ትምክህት፣ እውነት፣ አገልግሎትና ክብር የመሳሰሉ ቁልፍ ቃላትን የያዘ ነው::

## የሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሁለተኛ ቆሮንቶስ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ12 ቀን መነበብ ይኖርበታል::

❑ 1፥1—2፥4 ❑ 2፥5—3፥6 ❑ 3፥7—4፥18 ❑ 5፥1—6፥2 ❑ 6፥3—7፥1 ❑ 7፥2-16 ❑ 8—9 ❑ 10 ❑ 11፥1-15 ❑ 11፥16-33 ❑ 12 ❑ 13

### ማስታወሻ

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፣ ከወንድማ
ችንም ከጢሞቴዎስ፤
በቆሮንቶስ ላለችው በእግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያን እንዲሁም በመላው አካይያ ለሚ
ኖሩ ቅዱሳን ሁሉ፤
2ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## የመጽናናት አምላክ

3የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ
አም ላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አምላክና አባት ይባረክ። 4እኛ ራሳችን
ከእ ግዚአብሔር በተቀበልነው መጽናናት፣
በመ ከራ ያሉትን ማጽናናት እንድንችል፣
እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል።
5የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ የመብዛቱን
ያህል መጽናና ታችንም በክርስቶስ በኩል
ይበዛልናል። 6መከራ ብንቀበል ስለ እናንተ
መጽናናትና መዳን ነው። ብንጽናናም እኛ
የተቀበልነውን መከራ በመቀበል በትዕግሥት
እንድትጸኑ ስለ እናንተ መጽናናት ነው።
7ስለ እናንተ ያለን ተስፋ ጽኑ ነው፤
ምክንያቱም በመከራችን እንደ ተካፈላችሁ
ሁሉ በመጽናናታች ንም እንደምትካፈሉ
እናውቃለን።
8ወንድሞች ሆይ፤ በእስያ ስለ ደረሰብን
መከራ እንድታውቁ እንወዳለን፤ በሕይወት
ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ
ከዐቅማችን በላይ የሆነ ጽኑ መከራ ደርሶብን
ነበር። 9በርግጥም የሞት ፍርድ እንደ ተፈ
ረደብን ይሰማን ነበር፤ ይህም የሆነው ሙታ
ንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር እንድንታመን
እንጂ፣ በራሳችን እንዳንታመን ነው። 10እርሱ
እንዲህ ካለው የሞት አደጋ አድኖናል፤ ያድ
ነናልም፤ ወደ ፊትም ደግሞ እንደሚያድነን
ተስፋችንን በእርሱ ላይ ጥለናል። 11እናን
ተም በጸሎታችሁ ደግፉን፤ በብዙዎች
ጸሎት ስለ ተሰጠን ስጦታ ብዙ ሰዎች ስለ
እኛ[u] ምስጋና ያቀርባሉ።

## ጳውሎስ ዕቅዱን ለወጠ

12እንግዲህ ትምክህታችን ይህ ነው፤
በዚህ ዓለም በተለይም ከእናንተ ጋር ባለን
ግን ኙነት፣ ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና
ቅንነት እንደኖርን ኅሊናችን ይመሰክራል፤
ይህም በሰው ጥበብ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር
ጸጋ ነው። 13ልታነቡት ወይም ልትረዱት

1፥1 ሐሥ16፥1፤ 18፥1፡12፤ 1ቆሮ1፥1፤ 10፥32፤ ኤፌ1፥1፤ 10፥32፤ ኤፌ1፥1፤ ቈላ1፥1፤ 2ጢሞ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ኤፌ1፥3፤ 1ጴጥ1፥3
1፥4 ኢሳ49፥13፤ 51፥12፤ 66፥13፤ 2ቆሮ7፥6፡7፡13
1፥5 ሮሜ8፥17፤ 2ቆሮ4፥10፤ ገላ6፥17፤ ፊል3፥10፤ ቈላ1፥24፤ 1ጴጥ4፥13
1፥6 2ቆሮ4፥15
1፥7 ቊ5
1፥8 ሐሥ2፥9፤ ሮሜ11፥25፤ 1ቆሮ15፥32
1፥9 ኤር17፥5፡7፤ ዮሐ5፥21
1፥10 ሮሜ15፥31፤ 1ጢሞ4፥10
1፥11 ሮሜ15፥30፤ 2ቆሮ4፥15፤ 9፥11፤ ፊል1፥19
1፥12 ሐሥ23፥1፤ 1ቆሮ1፥17፤ 2ቆ1፡4፡13 2ቆሮ2፥17፤ 1ተሰ2፥10

u 1፥11 ብዙ ቅጆች እናንተ ይላሉ

---

**1፥4 በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፤** «ማጽናናት» (ግሪክ፣ «ፓራክሌሲስ») የሚለው ቃል በችግር ጊዜ ለማበረታታትና ለመርዳት በአንድ ሰው አጠገብ መቆም ማለት ነው:: እግዚአብሔር ይህን ልዩ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ እየፈጸመው ነው፤ ልጆቹን ያጽናናቸው ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ልኮአልና (ዮሐ 14፥16 እና ማብ ይመ):: ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም ዐይነት ሥቃይ የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን አማኞችን ከሰማያዊ አባታቸው እንክብካቤና ርኅራኄ ሊለያቸው እንደማይችል ካጋጠመው አያሌ ችግር ተምሮአል (ሮሜ 8፥35-39):: የእርሱን ማጽናናት የተለማመድን እኛ ሌሎችን በችግራቸው እናጽናናቸው ዘንድ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን ችግር እንዲመጣ ይፈቅዳል (በገጽ 744 ላይ፣ **«የጻድቃን መከራ»** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥5 ሥቃይ ... መጽናናታችንም፤** በዚህ መልእክት በአጠቃላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስትና ሕይወት ሁለቱንም ማለትም ሥቃይንና (ከክርስቶስ ጋር ሥቃይን መካፈል ወይም አብሮ መቀበል) በክርስቶስ መጽናናትን እንደሚጨምር በአጽንዖት ተናግሮአል:: ይኸውም ኀጢአት ከሚያስከትለው አሳዛኝ ሁኔታ የተነሣ በዚህ ዘመን ክርስቶስ ከሕዝቡ ጋርና ስለ ሕዝቡ ሥቃይን ይቀበላል ማለት ነው (ከማቴ 25፥42-45፤ ከሮሜ 8፥22-26 ጋር ያነጻጽሩ):: አሁን የምንቀበለው ሥቃይ የግድ በዐመፅ ምክንያት የሚደርስብን ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን የክርስቶስ ሥቃይ ተካፋይ እንደ መሆናችን አብዛኛውን ጊዜ ሊሆን የሚችለው በሰይጣን፣ በዓለምና በሐሰተኛ አማኞች እጅ ነው::

**1፥8 በሕይወት ለመኖር እንኳ ተስፋ እስከምንቈርጥ ድረስ፤** ከቍ 8-10 ይመልከቱ:: ታማኝ የሆነ አማኝ፣ መታዘዝ ባለበት ኅብረት ከክርስቶስ ጋር እየኖረና በክርስቶስም እየተወደደ ዐደጋን፣ ፍርሃትንና ተስፋ መቍረጥን በሚያካትት ሁኔታ ውስጥ ሊገባ ይችላል፤ እንዲሁም የሰው ዐቅም ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሆነ ነገር ይጋፈጥ ይሆናል:: (1) እጅግ ከባድ የሆነ ችግር በሕይወታችን ሲከሠት፣ እግዚአብሔር እንደተወን ወይም ለእኛ ያለው ፍቅር እንዳበቃ ልናስብ አይገባንም:: ይልቁንስ እንደዚህ ዐይነት ነገሮች በአዲስ ኪዳን ዘመን በነበሩ ታማኝ አገልጋዮች ላይ ደርሰው እንደ ነበር ለራሳችን ማሰብ ይኖርብናል:: (2) ክርስቶስ ወደ እኛ እንዲቀርብና ወደ እርሱ በእምነት ስንመለከትም ድልን የሚያመጣልንን ጸጋ እንድንቀበል (2፥14፤ 12፥7-10፤ 13፥4) እግዚአብሔር እንደዚህ ዐይነት ተስፋ አስቈራጭ መከራ እንዲመጣብን ይፈቅዳል::

**1፥11 እናንተም በጸሎታችሁ ደግፉን፤** እኛ በምንጸልየው ጸሎት የእግዚአብሔር ኀይልና ሥራ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ እንዲለቀቅ እናደርጋለን፤ ይህም የማያከራክር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ነው:: ከዚህም የተነሣ በችግር ላይ ላሉት እንድንማልድ ልንበረታታ ይገባል (ከሮሜ 1፥9፤ ከኤፌ 1፥16፤ ከፊል 1፥3፤ ከቈላ 1፥3፤ ከ1ተሰ 1፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

**1፥12 ትምክህታችን ይህ ነው፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ለደስታውና ለትምክህቱ መሠረት ያደረገው ቅንነትና ሐቀኝነት የተሞላ ባሕርዩን ነበር:: መላው የክርስትና ሕይወቱን በተመለከተ ለጌታው ታማኝ ለመሆን፣ አዳኙን ከሰቀለችው ዓለም ጋር ላለመመሳሰል፣ እግዚአብሔርም ወደ ራሱ እስኪጠራው ድረስ በቅድስና ለመጽናት ቊርጥ ውሳኔ አድርጎአል (ሮሜ 12፥1-2):: በሚመጣው የዘላለም ሕይወት ከትልልቅ ደስታዎቻችን አንዱ የሚሆነው «ከእግዚአብሔር በሆነ ቅድስናና ቅንነት» ኅሊናችን በማይፈርድበት ሕይወት በአዳኛችን በክርስቶስ ፊት መኖራችን ነው::

የማት ችሉትን ነገር እንጽፍላችሁም፤
ሁሉንም እንደምትረዱ ተስፋ አደርጋለሁ።
14እና ንተ በእኛ እንደምትመኩ ሁሉ እኛም
በእ ናንተ እንደምንመካ አሁን የተረዳችሁን
በከ ፊል ቢሆንም፣ በጌታ ኢየሱስ ቀን
ሁሉን ትረዳላችሁ።
15በዚህ ርግጠኛ ስለ ነበርሁ በዕጥፍ እን
ድትጠቀሙ፣ በመጀመሪያ ልጐበኛችሁዐቅጄ
ነበር። 16ወደ መቄዶንያ ስሄድ እግረ መንገዴን
ልጐበኛችሁና ከመቄዶንያም በእ ናንተ
በኩል ተመልሼ ወደ ይሁዳ ስሄድ በጕዞዬ
እንድትረዱኝ ዐቅጄ ነበር። 17ይህን ሳቅድ
በሚገባ ሳላስብ ያደረግሁት ይመስላ ችኋልን?
ወይስ በዓለማዊ ልማድ እንዴ፣"አዎን፣
አዎን" ወዲያው ደግሞ፣ "አይደ ለም፣
አይደለም" የምል ይመስላችኋልን?
18እግዚአብሔር ታማኝ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ለእ
ናንተ የምንናገረው ቃላችን፣ "አዎን" እና
"አይደለም" ሊሆንአይችልም፤ 19ምክንያቱም
እኔም ሆንሁ ሲላስና^ ጢሞቴዎስ፣ እኛ የሰ
በክንላችሁ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክር
ስቶስ "አዎን" እና "አይደለም" አልነበረም፤
ነገር ግን በእርሱ ዘወትር፣ "አዎን" ነው።
20በእግዚአብሔር የተሰጡ ተስፋዎች ሁሉ፣
"አዎን" የሚሆኑት በእርሱ ነውና፤ እኛም
በእርሱ አማካይነት ለእግዚአብሔር ክብር፣
"አሜን" የምንለው በዚህ ምክንያት ነው።
21እንግዲህ፣ እኛንም እናንተንም በክርስ
ቶስ ጸንተን እንድንቆም የሚያደርገን እግዚ
አብሔር ነው፤ የቀባንም እርሱ ነው፤ 22የእ
ርሱ ለመሆናችን ማኅተሙን ያተመብን
ደግሞም ወደ ፊት ለምናገኘው ነገር የመን
ፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ እርሱ ነው።
23ወደ ቆሮንቶስ ተመልሼ ያልመጣሁት
እንዳላሳዝናችሁ ብዬ ነው፤ ይህ እውነት ካል
ሆነ እግዚአብሔር ይመስክርብኝ። 24ጸንታችሁ
የምትቆሙት በእምነት ስለ ሆነ፣ ደስ እንዲ
ላችሁ ከእናንተ ጋር እንሠራለን እንጂ በእ
ምነታችሁ ላይ ለመሠልጠን አይደለም።
2 እንግዲህ ላሳዝናችሁ ስላልፈለግሁወደ
እናንተ ዳግመኛ ላለመምጣት ወሰ
ንሁ፤ 2እኔ ባሳዝናችሁም እንኳ፣ ከእናን
ተው ካሳዘንኋችሁ በቀር ደስ የሚያሰኘኝ
ማን አለ? 3ባለፈው ጊዜ እንደዚያ የጻፍ
ሁላችሁ ወደ እናንተ ስመጣ ደስ ሊያሰኙኝ
የሚገባቸው ሰዎች እንዳያሳዝኑኝ በማለት
ነው፤ ምክንያቱም የእኔ ደስታ የሁላችሁ
ደስታ እንደሚሆን አምናለሁ። 4እንደዚያ
ስጽፍላችሁ በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭን
ቀት፣ በብዙም እንባ ውስጥ ነበርሁ፤ ይህን
ንም ያደረግሁት ለእናንተ ያለኝን ጽኑ
ፍቅር እንድታውቁ በማለት እንጂ፣ እናን
ተን ለማሳዘን አልነበረም።

## በደለኛን ይቅር ማለት

5ማንም ሰውን ቢያሳዝን፣ ነገር ማጋነን
አይሁንብኝና ያሳዘነው እኔን ብቻ ሳይሆን
በመጠኑም ቢሆን ሁላችሁንም ነው። 6እን

1፥14 1ቆሮ1፥8
1፥15 ሮሜ1፥11:13፤ 15፥29፤ 1ቆሮ4፥19
1፥16 ሐሥ16፥9፤ 19፥21፤ 1ቆሮ16፥5-7:11፤ 3ዮሐ1፥6
1፥17 2ቆሮ10፥2:3፤ 11፥18
1፥18 1ቆሮ1፥9
1፥19 ማቴ4፥3፤ ሐሥ15፥22፤ 16፥1፤ ዕብ13፥8
1፥20 ሮሜ15፥8:9፤ 1ቆሮ14፥16
1፥21 1ቆሮ16፥13፤ 1ዮሐ2፥20:27
1፥22 ዘፍ38፥18፤ ሕዝ9፥4፤ ሐጌ2፥23፤ 2ቆሮ5፥5
1፥23 ሮሜ1፥9፤ 1ቆሮ4፥21፤ 2ቆሮ2፥1:3፤ 13፥2:10
1፥24 ሮሜ11፥20፤ 1ቆሮ15፥1፤ 1ጴጥ5፥3
2፥1 2ቆሮ1፥23
2፥2 2ቆሮ7፥8
2፥3 ቍ4:9፤ 2ቆሮ7፥8:12:16፤ 8፥22፤ 12፥21፤ ገላ5፥10፤ 2ተሰ3፥4፤ ፊሞ21
2፥4 ቍ3:9፤ 2ቆሮ7፥8:12
2፥5 1ቆሮ5፥1:2
2፥6 1ቆሮ5፥4:5፤ 2ቆሮ7፥11

^1፥19 ግሪኩ ሲልያኑስ ይላል

**1፥20 አሜን፤** የክርስቲያን ጸሎትና ዐዋጅ ማጠቃለያ የሆነው «አሜን» የሚለው ቃል በእግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት እንዲሁም በተስፋ ቃሉ መፈጸም ላይ ያለንን እርግጠኝነት ያመለክታል። ይህ ቃል ከማይናወጠው ከክርስቶስ ወንጌል እውነት ጋር ያለንን አንድነትና እርግጠኝነት የምንመሰክርበት የእምነት ድምፅ ነው:: በራእይ 3፥14 ላይ ጌታ ኢየሱስ «አሜን የሆነው» በመባል ተጠርቶአል::

**1፥22 የመንፈሱን ዋስትና በልባችን ያኖረ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኩል በአማኞች ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን በአራት የአሠራር ገጽታዎች እንደሚከተለው በዝርዝር አቅርቦአል፤ (1) መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በሕይወታቸው ተመሥርተው እንዲቈሙ ያደርጋቸዋል፤ እንዲሁም በእምነታቸው እንዲጸኑ ይረዳቸዋል (1ጴጥ 1፥5 እና ማብ ይመ)::

(2) መንፈስ ቅዱስ አማኞች ይመሰክሩ ዘንድ ኀይልን ሊሰጣቸው (ሐሥ 1፥8 እና ማብ ይመ)፣ የክርስቶስን ሥራ እንዲሠሩ ሊያስችላቸው (ኢሳ 61፥1፤ ማቴ 10፥19-20፤ ዮሐ 14፥12፤ ሐሥ 10፥38)፣ እውነትን እንዲያውቁ ሊያደርጋቸው (1ዮሐ 2፥20) ይቀባቸዋል::

(3) መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር የባለቤትነት ማረጋገጫ ሕጋዊ ማኅተም ሲሆን፣ አማኞች የእርሱ ገንዘብ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግባቸው ምልክት እንዲሁም በሰብአዊ ማንነታቸው ውስጥ የቅድስና ባሕርይን እንዲያፈሩ የሚያስችላቸው ኀይል ነው (ከ3፥18፤ ከገላ 5፥22፤ ከኤፌ 1፥13 ጋር ያነጻጽሩ)::

(4) መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያደረ የርስታችን መያዣ ነው፤ ይኸውም ለአማኞች ወደ ፊት ከክርስቶስ ጋር ታላቅ ሕይወት እንዳለየሚያረጋግጥ ዋስትናወይም ቀብድ ነው (5፥5፤ ሮሜ 8፥23፤ ኤፌ 1፥13-14 እና ማብ ይመ)::

**2፥4 በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት፤** ክርስቲያን አገልጋይን በተመለከተ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መመዘኛዎች አንዱ የሚያፈቅርና በስሜት የሚነካ ልብ ያለው መሆኑ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጽድቅ መንገድ ተንሸራትቶ በመውጣት ወደ ኀጢአትና ወደ ስሕተት መንገድ ሲገባ ብዙ እንባ የሚያፈስ ልብ ነው (ከመዝ 126፥5-6፤ ከማር 9፥24 ማብ ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 19፥41 እና ማብ፤ ዮሐ 11፥35 እና ማብ፤ ሐሥ 20፥19 እና ማብ ይመ)::

**2፥6 ቅጣት በቂው ነው፤** ከባድ በደል የፈጸመን የቤተ ክርስቲያን ምእመን በተመለከተ ሊወሰድ የሚገባውን የአዲስ ኪዳን የሥነ ሥርዐት እርምጃ ሂደት ከዚህ ምንባብ ማግኘት እንችላለን (ለምሳሌ ኢግብረገባዊነት፣ ምንዝርና ወዘተ፤ 1ቆሮ 5 ይመ)፤ (1) የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ቅድስና በሚገባ ለመጠበቅ (ከ1ቆሮ 5፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ቤተ ክርስቲያን በደል የፈጸመውን ሰው መንፈሳዊ ተሐድሶን ለማምጣት የሚያስችለውን በቂ ቅጣት ልትሰጠው ይገባል፤ ይህም ቅጣት የእግዚአብሔርን ምሕረትና ወደ ኅብረት ተመልሶ የመግባቱን (ቍ 7) ተስፋ እስከሚያሳጣው ድረስ እጅግ ከባድ መሆን የለበትም:: ይቅርታና ፍቅር በደልን ለፈጸመው ሰው ያለ ቅጣት እንዳልተሰጡ ልብ ይበሉ::

(2) በቂ ቅጣት ከተሰጠ በኋላ በደል የፈጸመው ሰው በሚገባ ንስሓ ከገባና ከልቡ በመጸጸት ከተመለሰ፣ ይቅርታ ሊደረግለትና በፍቅር መንፈስ ሊያጽናኑት ይገባል (ቍ 7-8)::

ደዚህ ያለው ሰው ብዙዎች የወሰኑበት ቅጣት
በቂው ነው። [7]ደግሞም ከልክ በላይ አዝኖ
ተስፋ እንዳይቈርጥ፣ ይቅር ልትሉትና ል.ታ
ጽናኑት ይገባችኋል። [8]ስለዚህ አሁንም የም
ትወዱት መሆናችሁን እንድትገልጹለት እለ
ምናችኋለሁ። [9]የጻፍሁላችሁም፣ የሚያጋጥ
ማችሁን ፈተና መቋቋማችሁንና በሁሉም
ነገር ታዛገሮች መሆናችሁን ለማወቅ ነበር።
[10]እናንተ ይቅር የምትሉትን ሰው እኔም
ይቅር እለዋለሁ፤ በርግጥ ይቅር የምለው
ነገር ካለ፣ በክርስቶስ ፊት ይቅር የምለው
ስለ እናንተ ስል ነው። [11]ይህንንም የምናደ
ርገው ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ
ነው፤ የእርሱን ዕቅድ አንስተውምና።

## የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች

[12]የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ ወደ
ጢሮአዳ በሄድሁ ጊዜ፣ ጌታ በር ከፍቶልኝ
ነበር፤ [13]ይሁን እንጂ ወንድሜን ቲቶን
እዚያ ስላላገኘሁት መንፈሴ አላረፈም፤ ስለ
ዚህ ተሰናብቻቸው ወደ መቄዶንያ ሄድሁ።
[14]ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድ
ራጊነት እያዞረ ለሚመራን፣ የዕውቀቱንም
መዐዛ በእኛ አማካይነት በየስፍራው ለሚገ
ልጥ አምላክ ምስጋና ይሁን፤ [15]ምክንያቱም
በሚድኑትና በሚጠፉት መካከል ለእግዚአብሔር
የክርስቶስ መዐዛ ነን። [16]ለሚጠፉት ወደ
ሞት የሚወስድ የሞት ሽታ፣ ለሚድኑት
ግን ወደ ሕይወት የሚወስድ የሕይወት ሽታ
ነን፤ ታዲያ፣ ለዚህ ብቁ የሚሆን ማን ነው?
[17]እኛ'ኮ ትርፍ ለማግኘት ብለን የእግዚአብሔርን
ቃል ቀላቅ ለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ
ብዙዎቹ አይ ደለንም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር
እንደተላኩ ሰዎች በክርስቶስ ሆነን
በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን።

3 እንደ ገና ራሳችንን ልናመሰግን እን
ጀምራለንን? ወይስ እንደ ሌሎቹ ለእ
ናንተ ወይም ከእናንተ የተጻፈ የምስጋና
ደብዳቤ ያስፈልገን ይሆንን? [2]እናንተኮ
ሰው ሁሉ የሚያውቃችሁና የሚያነባችሁ
በልባችን ላይ የተጻፋችሁ ደብዳቤዎቻችን
ናችሁ፤ [3]እናንተ በቀለም ሳይሆን በሕያው
እግዚአብሔር መንፈስ፣ በድንጋይ ጽላት ላይ
ሳይሆን በሰው ልብ ጽላት ላይ የተጻፋች
ሁና በእኛ የተገለገላችሁ የክርስቶስ ግልጽ
ደብዳቤ ናችሁ።
[4]በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ላይ ያለን
እምነት ይህን የመሰለ ነው፤ [5]ብቃታችን
ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፣ በራሳችን ብቃት
ከእኛ ነው የምንለው አንዳች ነገር የለንም።
[6]እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን በመንፈስ

2፥7 ገላ6፥1፤ ኤፌ 4፥32፤ ቈላ3፥13
2፥9 ቊ3:4፤ 2ቆሮ7፥8:12:15፤ 10፥6
2፥11 ማቴ4፥10፤ ሉቃ22፥31፤ 2ቆሮ4፥4፤ 1ጴጥ5፥8:9
2፥12 ሐሥ14፥27፤ 16፥28፤ ሮሜ1፥1፤ 2ቆሮ4፥3:4፤ 8፥18፤ 9፥13፤ 1ተሰ3፥2፤ ቲቶ1፥4
2፥13 ሐሥ16፥9፤ 2ቆሮ7፥5:6:13፤ 8፥6:16:23፤ 12፥18፤ ገላ2፥1:3፤ ቲቶ1፥4
2፥14 ሕዝ20፥41፤ ሮሜ6፥17፤ 7፥25፤ 1ቆሮ15፥57፤ 2ቆሮ8፥7፤ 2ቆሮ9፥15፤ ኤፌ5፥2፤ ፊል4፥18
2፥15 ቊ14፤ ዘፍ8፥21፤ ዘፀ29፥18፤ ዘኁ15፥3፤ 1ቆሮ1፥18
2፥16 ሉቃ2፥34፤ ዮሐ3፥36፤

2፥16 2ቆሮ3፥5:6 2፥17 ሐሥ20፥33፤ 1ቆሮ5፥8፤ 2ቆሮ1፥12፤ 4፥2፤ 12፥19፤ 1ተሰ2፥5 3፥1 ሐሥ18፥21፤ ሮሜ16፥1፤ 1ቆሮ16፥3፤ 2ቆሮ5፥12፤ 10፥12:18፤ 12፥11 3፥2 1ቆሮ9፥2 3፥3 ቊ7፤ ዘፀ24፥12፤ 31፥18፤ 32፥15:16፤ ምሳ3፥3፤ 7፥3፤ ኤር31፥33፤ ሕዝ36፥26

(3) በደልን በፈጸመው ሰው የሚደረገው ቅጣትና ሕይወቱ እንዲታደስ የሚደረግበት መንገድ በገርነት መንፈስ (ገላ 6፥1)፣ በሐዘን፣ በቅንነት፣ በመንፈሳዊ ቊጭት፣ እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ ለእግዚእብሔር ስም በመቅናት፣ በደልን የፈጸመው ሰው ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ከተጠያቂነት እንዳያመልጥ በማድረግ ነው (7፥11 ይመ፡ ከ1ቆሮ 5፥5:13 ጋር ያነጻጽሩ)::

ዛሬ አያሌ አብያተ ክርስቲያናት የአዲስ ኪዳንን የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዐት እርምጃ አወሳሰድ መርሕ ትተዋል:: ኀጢአትን በመታገሥ በቸልታ ያልፉሉ፤ ያለ ምንም ቅጣት ለኀጢአተኛ ይቅርታ ያደርጋሉ፤ ጸጋን ያረክሳሉ፤ መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውንም ላለመስማት ጆሮአቸውን ይደፍናሉ (ራእ 1፥2-3 ይመ):: ከዚህም የተነሣ ኀጢአት በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ ሆኖአል፡ ፈሪሀ እግዚአብሔር ከመካከላቸው ጠፍቶአል (ማቴ 18፥15 እና ቤተ ክርስቲያን ልትወስደው ስለሚገባት የሥነ ሥርዐት እርምጃ የተሰጠውን ማብ ይመ)::

**2፥11 ሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንዳያገኝ ነው፤** ሰይጣን ለሚያደርስብን ጥቃት ዋና መከላከያዎቻችን ከሆኑት አንዱ በእኛ ላይ ጉዳት ለማድረግ ሳያቋርጥ የሚያደርገውን ጥረትና ለክርስቶስ ካለን ፍቅር እንድንሸራተት የሚሞክረውን ሙከራ ማወቅ ነው (ኤፌ 6፥11 እና ማብ ይመ)::

**2፥14 በድል አድራጊነት እያዞረ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር አማኞችን የክርስቶስ የቤዛነት ጸጋ ድል አድራጊዎችና ተሸላሚዎች አድርጎ በዓለም ፊት እያዞረ እንደሚያሳያቸው ይገልጻል:: በዚህ የድል አድራጊነት የጉዞ ሥርዐት የክርስቶስ ዕውቀትና ቤዛነትን ያገኘው የአማኞች ሕይወት በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት መልካም መዓዛ ያለው ሽታ በመሆን ይገለጣል:: ይህ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ሲሆን፣ ለሰዎች የሕይወት ወይም የሞት ሽታ ነው (ቊ 15-16)::

**2፥17 የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት፤** ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚገልጸው ገንዘብን፣ ተቀባይነትንና ስኬትን ለማግኘት ሲሉ ወንጌል የሚጠይቀውን ዋጋ የሚቀንሱትን ሰባኪዎች ነው (ከ11፥4:12-15 ጋር ያነጻጽሩ):: ችሎታ ያላቸውና ሰዎችን የሚያግባቡ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ስውር ሁኔታቸው ቅንነት የጐደለው ነው:: ለገንዘብና ለክብር በእጅጉ ይስገበገባሉ (ከዮሐ 10፥12-13፤ ከፊል 1፥15:17፤ ከ1ጴጥ 5፥2፤ ከ2ጴጥ 2፥1-3:14-16 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥3 በሰው ልብ ጽላት ላይ፤** በክርስቶስ ደም በተመሠረተው በአዲሱ ኪዳን ሥር (ማቴ 26፥28) መንፈስ ቅዱስ በሲና እንደ ተደረገው በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን (ዘፀ 31፥18)፣ "በሰው ልብ ጽላት ላይ" የእግዚአብሔርን ሕግ ይጽፋል (በገጽ 1970 ላይ፣ "*የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: በአማኞች ልብ ውስጥ የእግዚአብሔር ሕግ ተቀምጦአል፡ መታዘዝ የሚችሉትም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ነው (ኤር 31፥33 እና ማብ፤ ሕዝ 11፥19 እና ማብ ይመ):: ይህ የውስጥ ሕግ ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ሰዎች ሊኖረን የሚገባውን ፍቅር የያዘ ነው (ከማቴ 22፥34-40፤ ከሮሜ 13፥8-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥6 ፊደል ይገድላል፤** የሚገድለው ሕጉ ራሱ ወይም ተጽፎ ያለው የእግዚአብሔር ቃል አይደለም። ነገር ግን ፍርድን የሚያመጣው ያለ መንፈስ ቅዱስ ሕይወትና ኀይል ሕጉ የሚጠይቀውን ለመፈጸም መጣር ነው (ቊ 7:9 ይመ፡ ከኤር 31፥33፤ ከሮሜ 3፥31 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*

ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ ኪዳን አገል.ጋ
ዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን፤ ምክን
ያቱም ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይወ
ትን ይሰጣል። [7]እንግዲህ እስራኤላውያን
ከፊቱ ክብር የተነሣ የሙሴን ፊት ትኵር
ብለው ማየት እስኪሳናቸው ድረስ፣ ያ ከጊዜ
በኋላ የሚያልፈውና በድንጋይ ላይ በፊደል
የተቀረጸው የሞት አገልግሎት በክብር
ከመጣ፣ [8]ታዲያ፣ የመንፈስ አገልግሎት
እንዴት ከዚያ የላቀ ክብር አይኖረውም?
[9]ሰዎችን የሚኰንነው አገልግሎት የከበረ
ከሆነ፣ የሚያጸድቀው አገልግሎት የቱን ያህል
ይበልጥ የከበረ ይሆን! [10]ከዚህ በፊት ክቡር
የነበረው የላቀ ክብር ካለው ጋር ሲወዳደር
ክብር የሌለው ሆኖአል። [11]የሚያልፈው ያን
ያህል ክብር ከነበረው፣ ጸንቶ የሚኖረውማ
እንዴት የላቀ ክብር አይኖረውም?

[12]እንግዲህ ይህን የመሰለ ተስፋ
ስላለን፣ በድፍረት እንናገራለን።
[13]እስራኤላውያንየፊቱ ማንጸባረቅ እየጠፋ
ሲሄድ መጨረሻ ውን እንዳይመለከቱ፣
ፊቱን በጨርቅ እንደ ሸፈነው እንደ ሙሴ
አይደለንም። [14]ነገር ግን ብሉይ ኪዳን
በተነበበ ቍጥር ያ መሸፈኛ እስከ ዛሬ
ድረስ ስላልተወገደ ልቡናቸው እንደ ደነዘዘ
ነው፤ መሸፈኛው አሁንም አል ተወገደም፤
የሚወገደው በክርስቶስ ብቻ ነውና። [15]እስከ
ዛሬም ድረስ የሙሴ መጻሕ ፍት በተነበቡ
ቍጥር መሸፈኛው ልቡናቸውን ይሸፍናል።

3፥7 ቊ9:13፤
ዘፀ34፥29-35፤
ኢሳ42፥21፤
ሮሜ2፥29፤ 4፥15
3፥9 ቊ7፤
ዘዳ27፥26፤
ሮሜ1፥17፤ 3፥21፡
22
3፥12 ሐሥ4፥29፤
ሮሜ5፥4:5፤
8፥24:25
3፥13 ቊ7፤
ዘፀ34፥33
3፥14 ቊ6፤
ሐሥ13፥15፤
15፥21፤
ሮሜ11፥7:8፤
2ቆሮ4፥4

3፥16 ዘፀ34፥34፤
ኢሳ25፥7፤
ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1:2፤
ዮሐ8፥32፤
ገላ4፥6:7
3፥16 ዘፀ34፥34፤
ኢሳ25፥7፤
ሮሜ11፥23
3፥17 ኢሳ61፥1:2፤
ዮሐ8፥32፤
ገላ4፥6:7
3፥18 ዮሐ17፥22:
24፤ ሮሜ8፥29፤
1ቆሮ13፥12፤
2ቆሮ4፥4:6
4፥1 ቊ16

[16]ነገር ግን አንድ ሰው ወደ ጌታ ዘወር ሲል
መሸፈኛው ይወገዳል። [17]ጌታ መን ፈስ ነው፤
የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ።
[18]እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን
ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን፣[ሐ]
የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ
ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መን
ፈስ ከሆነ ጌታ ነው።

## በሸክላ ውስጥ የተቀመጠ ክቡር ዕቃ

4 ስለዚህ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ
ይህ አገልግሎት ስላለን ተስፋ አንቈ
ርጥም። [2]ነገር ግን ስውርና አሳፋሪ ነገሮ
ችን ትተናል፤ አናታልልም፤ የእግዚአብሔ
ርንም ቃል ከሐሰት ጋር አንቀላቅልም፤ ይል
ቁንም እውነትን በግልጽ እየተናገርን በሰው
ሁሉ ኅሊና ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖ ረን
ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት እናቀርባለን።
[3]ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ፣ የተ
ከደነው ለሚጠፉት ነው። [4]የእግዚአብሔር አም
ሳል የሆነውን የክርስቶስ፣ የክብሩን ወንጌል
ብርሃን እንዳያዩ፣ የዚህ ዓለም አምላክ
የማ ያምኑትን ሰዎች ልቡና አሳውሮአል።

3፥18 መዝ 18፥45፤ ኢሳ40፥31፤ 1ቆሮ7፥25፤
1ጢሞ1፥13:16 4፥2 ሮሜ6፥21፤ 1ቆሮ4፥5፤ 2ቆሮ2፥17፤
5፥11፤ ዕብ4፥12 4፥3 1ቆሮ1፥18፤ 2ቆሮ2፥12፤ 3፥14
4፥4 ቊ6፤ ዮሐ12፥31፤ 14፥9፤ 1ቆሮ1፥20፤ 2ቆሮ3፥14

*[ሐ]3፥18 ወይም የጌታን ክብር በጥሞና እያሰላሰልን*

---

በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። አማኙ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽም ዘንድ በክርስቶስ በኩል በሚገኘው ድነት መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕይወትንና ኀይልን ይሰጠዋል። በመንፈስ ቅዱስ ከሆነ ፊደል አይገድልም።

**3፥8 የመንፈስ አግልግሎት፤** ሐዋርያው ጳውሎስ አዲስ ኪዳንን፣ "*የመንፈስ አገልግሎት*" በሚል ጠርቶታል። አንድ ሰው በክርስቶስ በማመን መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል፤ ዳግም ይወለዳል (በገጽ 1606 ላይ፣ "***ዳግም ልደት***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ያገኛል (ሐሥ 1፥8፤ 2፥4)። በክርስቶስ ውስጥ ያሉት የቤዛነት በረከቶች ሁሉ የሚገኙት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው። የክርስቶስን ህልዎትና በረከቶቹን ሁሉ ወደ እኛ የሚያስተላልፍልን መንፈስ ቅዱስ ነው (ቊ 9፤ በገጽ 1679 ላይ፣ "***የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥17 መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ፤** በክርስቶስ በኩል የሚመጣው ነጻነት (ገላ 5፥1) ከሁሉም በፊት ከኀጢአት ባርነትና ፍርድ (ቊ 7-9፤ ሮሜ 6፥6:14፤ 8፥2፤ ኤፌ 4፥22-24፤ ቈላ 3፥9-10) እንዲሁም ከመላው የሰይጣን አገዛዝ (ሐሥ 26፥18፤ ቈላ 1፥13፤ 1ጴጥ 5፥8) አርነት መውጣት ነው፤ (1) እውነተኛው ነጻነት የሚጀምረው አማኙ ከክርስቶስ ጋር አንድነት ሲኖረው (ሐሥ 4፥12፤ ኤፌ 1፥7) እና መንፈስ ቅዱስን ሲቀበል ነው (በገጽ 1606 ላይ፣ "***ዳግም ልደት***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ከመንፈሳዊ እስራት ነጻ መውጣት የሚቻለው መንፈስ ቅዱስ በቀጣይነት በውስጣችን ሲያድርና ምሪቱንም በመከተል ስንታዘዝ ነው (ሮሜ 8፥1፤ ገላ 5፥18፤ ከዮሐ 15፥1-11 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) በክርስቶስ የተሰጠው ነጻነት አማኝ የፈለገውን እንዲያደርግ የሚፈቅድ አይደለም (1ቆሮ 10፥23-24)፤ ነገር ግን ማድረግ የሚገባውን እንዲያደርግ የሚፈቅድ ነጻነት ነው (ሮሜ 6፥18-23)። መንፈሳዊ ነጻነት ክፉ ድርጊትን የምንሸፋፍንበት ወይም በውስጣችን የሚፈጠረውን ጦርነት የምናስተባብልበት መንገድ አይደለም (ያዕ 4፥1-2፤ 1ጴጥ 2፥16-23)። ክርስቲያናዊ ነጻነት አማኞች በጽድቅ መንገድ (ሮሜ 6፥18 ...) እግዚአብሔ ርን (1ተሰ 1፥9) እና ሌሎችን ሰዎች (1ቆሮ 9፥19) እንዲያገለግሉ ነጻ ያወጣቸዋል። እኛ ለእግዚአብሔር በጸጋ የምንኖር (ሮሜ 5፥21፤ 6፥10-13) አሁን የክርስቶስ ባሪያዎች ነን (ሮሜ 1፥1፤ 1ቆሮ 7፥22፤ ፊል 1፥1)።

**3፥18 የጌታን ክብር ... እያንጸባረቅን፤** የክርስቶስን ቅርብነት፣ ፍቅር፣ ጽድቅና ኀይል በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ተግባራዊ ሲሆን፣ ማንነታችንን እርሱን ወደ መምሰል መልክ ይለውጠዋል (4፥6 ይመ፤ ከቈላ 1፥15፤ ከዕብ 1፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን የለውጡ ሂደት ዕድገት የሚያሳይና በከፊል የሚገለጥ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ፣ እርሱን ፊት ለፊት እናየዋለን፤ ሙሉ በሙሉም እንለወጣለን (1ዮሐ 3፥2፤ ራእ 22፥4)።

**4፥4 የዚህ ዓለም አምላክ፤** "የዚህ ዓለም አምላክ" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው አብዛኛውን የዚህን ዓለም እንቅስቃሴ የመቈጣጠር ኀይል ያለውን ሰይጣንን ነው (ከዮሐ 12፥31፤ 14፥30፤ 16፥11፤ ከኤፌ 2፥2፤ ከ1ዮሐ 5፥19 ጋር ያነጻጽሩ)። ይሁን እንጂ የእርሱ አገዛዝ ጊዜያዊና በእግዚአብሔር ፈቃድ የተገደበ ነው፤ እስከ ታሪክ ፍጻሜ ድረስ ብቻ የሚቆየው በእግዚአብሔር አምንታዊ ፈቃድ ነው (ራእ 19፥11-20፥10)። ራሳቸውን

5እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ
መሆ ኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤
እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ
አገል ጋዮች ሆነናል። 6በክርስቶስ ፊት
እግዚአብ ሔር የክብሩን ዕውቀት ብርሃን
ይሰጠን ዘንድ፣ "በጨለማ ብርሃን ይብራ"
ያለው እግዚአብሔር ብርሃኑን በልባችን
አብርቶአልና።
7ነገር ግን ይህ እጅግ ታላቅ ኀይል ከእግ
ዚአብሔር እንጂ ከእኛ አለመሆኑን ለማሳየት፣
ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን።
8ከየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኰታኰትም፤
ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቈርጥም፤ 9ብንሰ
ደድም ተጥለን አንቀርም፤ መትተው ቢጥ
ሉንም አንጠፋም። 10የኢየሱስ ሕይወት በሰ
ውነታችን እንዲገለጥ፣ የኢየሱስን ሞት ዘወ
ትር በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን።
11የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን
እንዲገለጥ፣ እኛ ሕያዋን የሆንን ሁልጊዜ
ስለ ኢየሱስ ለሞት ዐልፈን እንሰጣለንና።
12እንግዲህ ሞት በእኛ ይሠራል፤ ሕይወት
ግን በእናንተ።
13"አመንሁ፤ ስለዚህም ተናገርሁ" ተብሎ
እንደ ተጻፈ፣ እኛም በዚያው የእምነት መን
ፈስ እናምናለን፤ ስለዚህም እንናገራለን፤
14ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስን ከሙታን ያስ
ነሣው እኛንም ደግሞ ከኢየሱስ ጋር አስነ
ሥቶ ከእናንተ ጋር በፊቱ እንደሚያቀርበን
እናውቃለን። 15ለብዙ ሰዎች እየደረሰ ያለው
ጸጋ፣ ስእግዚአብሔር ክብር በምስጋና ላይ ምስ
ጋናን እንዲጨምር ይህ ሁሉ ለእናንተ
ጥቅም ሆኖአል።
16ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም፤ ውጫዊው
ሰውነታችን እየጠፋ ቢሄድም እንኳ፣ ውስ
ጣዊው ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል፤
17ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከ
ራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር
ያስገኝልናል። 18ስለዚህ ዐይናችን የሚያተ
ኵረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይ
ታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤
የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው።

4፥5 1ቆሮ1፥13:23፤ 9፥19
4፥6 ቍ4፤ ዘፍ1፥3፤ መዝ18፥28፤ 2ጴጥ1፥19
4፥7 መሳ7፥2፤ ኢዮ4፥19፤ ኢሳ64፥8፤ 1ቆሮ2፥5፤ 2ቆሮ6፥7፤ 2ጢሞ2፥20
4፥8 2ቆሮ7፥5፤ ገላ4፥20
4፥9 መዝ37፥24፤ ምሳ24፥16፤ ዮሐ15፥20፤ ሮሜ8፥35፤ ዕብ13፥5
4፥10 ሮሜ6፥5:6፤ 2ቆሮ1፥5
4፥11 ሮሜ8፥36
4፥12 2ቆሮ13፥9
4፥13 መዝ116፥10፤ 1ቆሮ12፥9
4፥14 ሐሥ2፥24፤ ኤፌ5፥27፤ ቈላ1፥22፤ 1ተሰ4፥14፤ ይሁ1፥24
4፥15 2ቆሮ1፥11 4፥16 ቍ1፤ መዝ18፥45፤ 103፥5፤ ኢሳ40፥31፤ ሮሜ፥22፤ ቈላ3፥10 4፥17 መዝ30፥5፤ ሮሜ8፥18፤ 1ጴጥ1፥6:7 4፥18 ሮሜ8፥24፤ 2ቆሮ5፥7፤ ዕብ11፥፦

ለኢየሱስ ክርስቶስ የማይሰጡ ሰዎች ሰይጣን ወደ ፈለገው አቅጣጫ የሚነዳቸው ይሆናሉ:: ወደ ድነት እንዳይመጡ እንዲሁም የወንጌልን ክብርና እውነት እያዳየዩ ዐይናቸውን ያሳውራል:: ይህን ለሞት የሚዳርግ ችግር ለማስወገድና መፍትሔ ለማምጣት በምልጃ ጸሎት ሥራውን ማሰር እንዲሁም ሰዎች ቃሉን እንዲሰሙ፣ እንዲያስተውሉና ለማመን ወይም ላለማመን የራሳቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ ወንጌልን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል (ሐሥ 1፥8) መስበክ ተገቢ ነው (ቍ 5-6፤ ማቴ 4፥10 በሰይጣን ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)::

**4፥7 ይህ የከበረ ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ፤** ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ ሐዘን፣ ዕንባ፣ ችግር፣ ግራ መጋባት፣ ድካምና ፍርሀት የሚሰማቸው "የሸክላ ዕቃ" ናቸው (ከ1፥4:8-9፤ 7፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: ነገር ግን በውስጣቸው የከበረ ሰማያዊ ነገር ስላለ አይሸነፉም:: ክርስትና ድካም የሌለበት ወይም መለኮታዊ ኀይል የሚገለጥበት ብቻ አይደለም:: ነገር ግን በሰው ደካማነት መለኮታዊ ኀይል የሚገለጥበት ነው (12፥9):: ይህም ሲባል የሚከተለውን ማለት ነው፡ (1) በማንኛውም ዐይነት ሥቃይ ውስጥ ብንሆን በእግዚአብሔር ኀይልና ፍቅር ከአሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን (ሮሜ 8፥37)፤ (2) ድካማችን፣ ችግራችንና ሥቃያችን ለክርስቶስ የተትረፈረፈ ጸጋ ምቹ እንድንሆንና የእርሱም ሕይወት በሥጋችን እንዲገለጥ ያደርጋል (ቍ 8-11 ይመ፤ ከ12፥7-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

**4፥8 ብንገፋም አንንኰታኰትም፤** በሕይወታችሁ የክርስቶስን ህልዎትና ኀይል ተለማምዳችሁ ከሆነ ከችግር፣ ከሕመም ወይም ከሥቃይ የተነሣ በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ በፍጹም ተሸንፋችሁ አትወድቁም:: ውጭአዊው ሁኔታ ከምትሸከሙት በላይ ሲሆንና ያላችሁ ሰብአዊ ዐቅም ሙጥጥ ብሎ ሲያልቅ እምነታችሁን፣ ተስፋችሁንና ብርታታችሁን ለማደስ የእግዚአብሔር ኀይልና በረከት ይሰጣችኋል:: በምንም ዐይነት ሁኔታ ቢያልፉ እግዚአብሔር ታማኝ ልጆቹን አይተዋቸውም (ሮሜ 8፥35-39፤ ዕብ 13፥5)::

**4፥11 ለሞት ዐልፈን እንሰጣለንና፤** ቍ 11-12 ይመልከቱ:: ሌላው ሰው ሕይወትን ያገኝ ዘንድ የክርስቶስን ሥቃይ መካፈልና ሞት በእኛ በራሳችን ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ሥራ መቀበል ይኖርብናል (ቍ 12):: ስለ ክርስቶስ ራስን መካድ፣ ችግርን፣ ተስፋ መቍረጥንና ሥቃይን መቀበል በሕይወታችን ለሌሎች የክርስቶስን ጸጋ እንድናካፍል ያደርገናል (ከ11፥23-29፤ ከሮሜ 8፥36-37፤ ከፊል 1፥29፤ ከ1ጴጥ 4፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: እንደዚህ ዐይነቱን የመሞት ታላቅ መርሕ ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስም በዮሐንስ 12፥24-25 ላይ አስተምሮአል::

**4፥16 ወጫዊው ... ውስጣዊው፤** "ውጫዊ" የሚለው ቃል አካላዊ ሥጋችንን የሚያመለክት ሲሆን፣ ይኸውም ለመበስበስ የተዳረገ እንዲሁም ከሚችኑቱና በሕይወት ውስጥ ከሚያጋጥሙ ችግሮች የተነሣ ወደ ሞት የሚገሠግሠው አካል ነው (ቍ 17):: "ውስጣዊ" የሚለው የክርስቶስ መንፈስ ያለበትን የሰውን መንፈስ የሚያመለክት ነው:: ሥጋችን የሚያረጅና የሚበሰብስ ቢሆንም ሳያቋርጥ ወደ እኛ በሚተላለፈው የክርስቶስ ሕይወትና ኀይል ውስጣችን እየታደሰ ይሄዳል፤ የእርሱ መንፈስ አእምሮአችንን፣ ስሜታችንና ፈቃዳችን ከእርሱ መልክና ዘላለማዊ ዕቅድ ጋር እንዲስማማ ያደርጋል::

**4፥17 ጊዜያዊ የሆነው መከራችን... ዘላለማዊ ክብር፤** ለክርስቶስ ታማኝ በመሆን የጸኑት በሕይወታቸው የሚቀበሉት መከራ፣ በክርስቶስ ከሚያገኙት ታላቅ ክብር ጋር ሲወዳደር እጅግ ቀላል ነው:: ይህ ክብር አሁን በከፊል አለን፤ ነገር ግን ወደ ፊት ሙሉ በሙሉ የምንቀበለው ነው (ከሮሜ 8፥18 ጋር ያነጻጽሩ):: ወደ ሰማያዊ ርስታችን ስንደርስ፣ እጅግ ከባድ የነበረው መከራ ከዘላለም መንግሥት ክብር ጋር ሲወዳደር ምንም እንዳልሆነ እንናገራለን:: ስለዚህ ችግር ሲያጋጥመን ተስፋ መቁረጥ ወይም እምነታችንን መተው የለብንም::

### ሰማያዊ መኖሪያችን

5 መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን
ቢፈርስም፣ በሰው እጅ ያልተሠራ ነገር
ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰ
ማይ እንዳለን እናውቃለን። 2እስከዚያውግን
የሰማዩን መኖሪያችንን ለመልበስ እየና
ፈቅን እንቃትታለን፤ 3በርግጥ ከለበስነው
ራቍታችንን ሆነን አንገኝም። 4በዚህ ድን
ኳን እስካለን ድረስ ከብዶን እንቃትታለን፤
ምክንያቱም ሟች የሆነው በሕይወት እንዲ
ዋጥ ሰማያዊውን መኖሪያችንን ልንለብስ
እንጂ ልንገፈፍ አንፈልግም። 5ለዚህ ዐላማ
ያዘጋጀን እግዚአብሔር ነው፤ ሊመጣ ላለው
ዋስትና እንዲሆነን መንፈሱን መያዣ አድ
ርጎ የሰጠንም እርሱ ነው።
6ስለዚህ ሁልጊዜ በመታመን እንኖራለን፤
በሥጋ እስካለን ድረስ ከጌታ ርቀን እንደም
ንገኝ እናውቃለን፤ 7ምክንያቱም የምንኖረው
በእምነት እንጂ በማየት አይደለም። 8ከሥጋ
ተለይተን ከጌታ ጋር መኖርን እንደ ምንመ
ርጥ ርግጠኛ ሆኜ እናገራለሁ። 9ስለዚህ
በሥጋ ብንኖርም ወይም ከሥጋ ብንለይም
ዐላማችን እርሱን ደስ ማሰኘት ነው። 10ሁላ
ችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እን
ቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው
ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን
ዋጋ ይቀበላል።

5፥1 ኢሳ38፥12፤ 1ቆሮ15፥47፤ 2ጴጥ1፥13፡14
5፥2 ቍ4፤ ሮሜ8፥23፤ 1ቆሮ15፥53፡54
5፥4 ቍ2፤ ሮሜ8፥23 1ቆሮ15፥53፡54
5፥5 ሮሜ8፥23፤ 2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13፡14
5፥7 1ቆሮ13፥12፤ 2ቆሮ4፥18
5፥8 ዮሐ12፥26
5፥9 ሮሜ14፥18፤ ኤፌ5፥10፤ ቈላ1፥10፤ 1ተሰ4፥1
5፥10 ማቴ16፥27፤ ሐሥ10፥42፤ ሮሜ2፥16፤ 14፥10፤ ኤፌ6፥8
5፥11 ኢዮ23፥15፤ 2ቆሮ4፥2፤ ዕብ10፥31፤ 12፥29፤ ይሁ1፥23
5፥12 2ቆሮ1፥14፤ 3፥1
5፥13 2ቆሮ11፥1፡6፡17፤ 12፥11
5፥14 ሮሜ6፥6፡7፤ ገላ2፥20፤ ቈላ3፥3

### የማስታረቅ አገልግሎት

11እንግዲህ ጌታን መፍራት ምን ማለት
እንደ ሆነ ስለምናውቅ፣ ሰዎች የምንናገረ
ውን እንዲቀበሉ ለማድረግ እንጥራለን።
የእኛ ማንነት በእግዚአብሔር ዘንድ የተገለጠ
ነው፤ ደግሞም በኅሊናችሁ ዘንድ ግልጽ
ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። 12ይህን
የምለው ራሳችንን በእናንተ ፊት እንደ ገና
ለማመስገን ሳይሆን፣ በእኛ እንድትመኩ
ዕድል ልሰጣችሁ ነው፤ ይኸውም በውጭ
በሚታየው ለሚመኩት እንጂ በልብ ውስጥ
ባለው ነገር ለማይመኩ መልስ መስጠት
እንድትችሉ ነው። 13ከአእምሮ ውጪ ብንሆን
ለእግዚአብሔር ብለን'ነው፤ ባለ አእምሮም
ብንሆን ለእናንተ'ነው። 14የክርስቶስ ፍቅር
ግድ ይለናልና፤ ምክንያቱም አንዱ ስለ ሁሉ
እንደ ሞተ እርግጠኞች ሆነናል፣ ከዚህም
የተነሣ ሁሉ ሞተዋል። 15በሕይወት ያሉትም
ለሞቱላቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው እንጂ
ከእንግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ
ስለ ሁሉ ሞተ።
16ስለዚህ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በው
ጫዊ ነገር አንመዝንም፤ ከዚህ ቀደም ክር
ስቶስን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤ ከእ
ንግዲህ ግን እንደዚህ አናደርግም። 17ስለ

5፥15 ሮሜ4፥25፤ 14፥7-9 5፥16 2ቆሮ10፥4፤ 11፥18
5፥17 ኢሳ65፥17፤ ዮሐ1፥13፤ ሮሜ6፥4፤ 16፥3፤ ገላ6፥15፤ ራእ21፥4፡5

**5፥1 ምድራዊ ድንኳን፤** ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *“መኖሪያችን የሆነው ምድራዊ ድንኳን ቢፈርስም”* የሚለውን ሁኔታን የሚገልጸውን ሐረግ የተጠቀመው፣ ክርስቶስ በቶሎ እንደሚመለስ ስለሚያውቅ ነው፤ ያም ሆነ ይህ እርሱ ሞትን እንደማይሞት፣ ከዚህም በላይ አካሉ ድንገት በቅጽበት ዐይን እንደሚለወጥ ተረድቶአል ማለት ነው (በገጽ 1907 ላይ፣ *“ንጥቀት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ ተመሳሳይ ጣምራ ሁኔታ ማለትም መሞት ወይም መለወጥ ዛሬም አማኞችን ሁሉ የሚመለከት ነው። እርሱ የሚመጣበትን ቀንም ሆነ ሰዓት ልናውቅ እንደማንችል ክርስቶስ ተናግሮአል (ማቴ 24፥36፡42፡44)፤ ይህም ሁነት ተፈጻሚነቱ የማይቀር ስለሆነ ቅዱስ ኑሮን ለመኖር በቂ የሆነ ምክንያት ነው (ማቴ 24፥42 እና ማብ፡ 1ዮሐ 3፥2-3 ይመ)።

**5፥1 ምድራዊ ድንኳን ... ቤት፤** (1) “ምድራዊ ድንኳን” የሚለው ሐረግ የአማኝን ምድራዊ አካል ወይም የአማኝን ምድራዊ ሕይወት የሚያመለክት ነው፤ (2) እንደዚሁም “በሰው እጅ ያልተሠራ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነ ዘላለማዊ ቤት በሰማይ” የሚለው ሐረግ አማኞች የትንሣኤ አካላቸውን እስኪያገኙ ድረስ የሚቀበሉትን በሰማይ የተዘጋጀላቸውን ጊዜያዊ አካል ወይም በዙሪያቸው ያለውን የሰማዩን ኑሮ ሁኔታ የሚያመለክት ነው።

አንዳንዶች ይህን አስቸጋሪ ምንባብ በመውሰድ ከሞት በኋላ ትንሣኤ ሲጠባበቁ አማኞች ከሥጋ እንደ ተለየ መንፈስ፣ በግልጽ እንደማይታይ ጥላ ወይም ከሥጋ እንደተለየች ቅርጽ አልባ ነፍስ ሆነው ይኖራሉ ብለው ያስተምራሉ። ይሁን እንጂ ሙሴና ኤልያስ የትንሣኤ አካላቸውን ቢጠባበቁም እንኳ የክርስቶስ ክብር በተገለጠበት ተራራ በግልጽ የታዩት ሰማያዊ አካልን ለብሰው እንደነበር ልብ ማለት ይገባል (በገጽ 1810 ላይ፣ *“አካላዊ ትንሣኤ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከዚህም በላይ በራእ 6፥9-11 እንደተገለጸው ነፍሶች የሚገለጡት በግልጽ የሚታዩ ነጭ ልብስ የለበሱ ሆነው እንጂ ከሥጋ እንደ ተለዩ ቅርጽ አልባ ነፍሶች ሆነው አይደለም።

**5፥8 ከጌታ ጋር መኖርን፤** ይህ ጥቅስና ሌሎቹ (ለምሳሌ፣ ሉቃ 23፥42-43፤ ፊል 1፥23) በሞትና በሚመጣው ሕይወት መካከል ያለው ጊዜ ብዙ እንደማይቆይ ያስተምሩናል (በገጽ 765 ላይ፣ *“ሞት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። አማኝ ሲሞት በአስቸኳይ ወደ ክርስቶስ ህልዎት ይገባል (1ቆሮ 13፥12)። ስለዚህ፣ “ሞትም ማትረፍ ነው” (ፊል 1፥21)። ይህ ማለት አሁን ክርስቶስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ የለም ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የክርስቶስን ህልዎት ለአማኞች እንዲገለጥ ማድረግ ነው (በገጽ 1679 ላይ፣ *“የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ነገር ግን ይህ የሚያመለክተው አሁን እኛ ከጌታ ጋር ያለነው በእምነት እንጂ በማየት አለመሆኑን ነው (ዕብ 11፥1)።

**5፥10 በክርስቶስ የፍርድ ወንበር፤** በፍርድ ቀን አማኞችን በተመለከተ ስለሚሰጠው ፍርድ የበለጠ ማብራሪያ ለማግኘት በገጽ 1822 ላይ፣ *“በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**5፥17 አዲስ ፍጥረት ነው፤** ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት የሚቀበሉ በእግዚአብሔር የመፍጠር ትእዛዝ አማካይነት (4፥6) መንፈስ ቅዱስ በሚገዛበት በእግዚአብሔር ፍጹም አዲስ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ አዲስ ፍጥረት ይሆናሉ (ሮሜ 8፥14፤ ገላ 5፥25፤

# በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ

*2ቆሮ 5፥10 "ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል።"*

አማኞች አንድ ቀን "በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት" ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ እንደሚሰጡ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። በአማኞች ላይ የሚሰጠውን የተለየ ፍርድ በተመለከተ የሚከተሉት እውነቶች ሊስተዋሉ ይገባል፤

(1) ክርስቲያኖች በሙሉ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ ምንም ዐይነት ልዩነት አይደረግም (ሮሜ 14፥12፤ 1ቆሮ 3፥12-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ መክ 12፥14 እና ማብ ይመ)።

(2) ይህ ፍርድ የሚሰጠው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ ዳግም ሲመለስ ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ 1ተሰ 4፥14-17 ይመ)።

(3) ፍርድ የሚሰጠው ክርስቶስ ነው (ዮሐ 5፥22፤ 2ጢሞ 4፥8)።

(4) በአማኞች ላይ የሚሰጠው ይህ የተለየ ፍርድ አስፈሪና ከባድ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ ይኸውም በተለይ የመጥፋትን ወይም የመቃጠልን ሁኔታ ማካተቱ (1ቆሮ 3፥15፤ 2ዮሐ 1፥8)፣ "በሚመጣበትም ጊዜ" በፊቱ ማፈር እንደሚሆን (1ዮሐ 2፥28) እንዲሁም በሕይወት ዘመን የተሠራ ሥራ ሁሉ ሊቃጠል እንደሚችል በማመልከቱ ነው (1ቆሮ 3፥13-15)። ይሁን እንጂ አማኝን በተመለከተ የሚሰጠው ይህ ልዩ ፍርድ የእግዚአብሔርን የዘላለም ኵነኔ ዐዋጅ የሚያካትት አይደለም።

(5) ማንኛውም ነገር በግልጽ ይወጣል። "ግልጽ" (ግሪክ፡ "ፋኔሩ"፤ 2ቆሮ 5፥10) የሚለው ቃል በግልጥ ወይም በይፋ እንዲታይ ማድረግ ማለት ነው። እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ መርምሮ እውነተኛ ምንነታቸውን በይፋ ወይም በግልጥ እንዲታወቅ ያደርጋል፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) ስውር ድርጊታችን (ማር 4፥22፤ ሮሜ 2፥16)፣ (ለ) ባሕርያችን (ሮሜ 2፥5-11)፤ (ሐ) የተናገርነው ቃል (ማቴ 12፥36-37)፤ (መ) በጎ ድርጊታችን (ኤፌ 6፥8)፤ (ሠ) አስተሳሰባችን (ማቴ 5፥22)፣ (ረ) በልባችን ውስጥ የተሰወረ ሐሳብ (1ቆሮ 4፥5)፣ (ሰ) ፍቅር አለማሳየታችን (ቈላ 3፥18—4፥1) እንዲሁም (ሸ) ሥራችንና አገልግሎታችን (1ቆሮ 3፥13)።

(6) በአጠቃላይ አማኞች ታማኝ ስለሆኑበት ወይም ታማኝ ስላልሆኑበት ጉዳይ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልስ ይሰጡበታል (ማቴ 25፥21፡23፤ 1ቆሮ 4፥2-5)፤ እንዲሁም ስለ ሠናት ሥራ ከተሰጣቸው ጸጋ፣ ዕድልና መረዳት አንጻር በኀላፊነት ይጠየቃሉ (ሉቃ 12፥48፤ ዮሐ 5፥24፤ ሮሜ 8፥1)።

(7) አማኝ በክፉ ድርጊቱ ንስሓ ሲገባ ከዘላለም ቅጣት አንጻር ምሕረትን ያገኛል (ሮሜ 8፥1)፤ ይሁን እንጂ ብድራትን ለመክፈል ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ይጠየቅበታል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል፣ "በደለኛውም የእጁን ያገኛል፤ አድልዎም የለም" ይላል (ቈላ 3፥25 ይመ፤ ከመክ 12፥14፤ ከ1ቆሮ 3፥15፤ ከ2ቆሮ 5፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። አማኝ የፈጸመው በጎ ድርጊትና ያሳየው ፍቅር በእግዚአብሔር ይታሰባል፤ እንዲሁም ሽልማትን ያስገኝለታል (ዕብ 6፥10)። የእግዚአብሔር ቃል፣ "ሰው ለሚያደርገው በጎ ነገር ሁሉ ሽልማቱን ከጌታ እንደሚቀበል ታውቃላችሁ" (ኤፌ 6፥8) ይላል።

(8) በአማኞች ላይ ከሚሰጠው የተለየ ፍርድ የተነሣ የሚገኙ ወይም የሚታጡ ውጤቶች ልዩ ልዩ ሲሆኑ፣ እነርሱም ደስታን (1ዮሐ 2፥28)፣ መለኮታዊ ማረጋገጫን (ማቴ 25፥21)፣ ሥራንና ሥልጣንን (ማቴ 25፥14-30)፣ ማዕረግን (ማቴ 5፥19፤ 19፥30)፣ ሽልማትን (1ቆሮ 3፥12-14፤ ፊል 3፥14፤ 2ጢሞ 4፥8) እንዲሁም ክብርን (ሮሜ 2፥10 ይመ፤ ከ1ጴጥ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ) ናቸው።

(9) በቅርብ መሆኑ የማይቀረው በክርስቲያኖች ላይ የሚሰጠው የተለየ ፍርድ በውስጣቸው ፈሪሃ እግዚአብሔርን የሚያመጣ መሆን አለበት (2ቆ 5፥11፤ ፊል 2፥12፤ 1ጴጥ 1፥17)፤ የጌታን መምጣት ለመጠባበቅና ለመጸለይ እንዲችሉ (1ጴጥ 4፥5፡7) እንዲሁም ንጹሕ አእምሮ ያላቸውና ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ በቅድስናና እግዚአብሔርን በመፍራት ለመኖር ያስችላቸዋል (2ጴጥ 3፥11)፤ ለሰው ሁሉ ምሕረትንና ቸርነትን እንዲያሳዩም ያደርጋቸዋል (ማቴ 5፥7 ይመ፤ ከ2ጢሞ 1፥16-18 ጋር ያነጻጽሩ)።

ዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት
ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ
ሆኖአል። [18]ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤
እርሱ በክርስቶስ አማካይነት ከራሱ ጋር አስ
ታረቀን፤ የማስታረቅንም አገልግሎት ሰጠን፤
[19]እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር
ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቈጥርባቸ
ውም ነበር፤ ለእኛም ደግሞ የማስታረቅ ቃል
ሰጠን። [20]ስለዚህ እኛ የክርስቶስ እንደራሴ
ዎች ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት
ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር
ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን።
[21]እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ
እን ድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን
እግ ዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት[ሠ] አደረገው።

**6** ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ
እንደ መሆናችን መጠን፣ የተቀበላችሁ
ዝ ትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደር
16 ጉት ዐደራ እንላችኋለን። [2]እርሱ፣
"በትክክለኛው ሰዓት ሰማሁህ፤
በመዳንም ቀን ረዳሁህ" ይላልና።
እነሆ፤ ትክክለኛው ሰዓት አሁን ነው፤
የመዳንም ቀን አሁን ነው።

5፥18 ሮሜ5፥10፣ 11፥36
5፥19 ሮሜ4፥8
5፥20 ቍ18፣ ኢሳ 27፥5፣ 2ቆሮ6፥1፣ ኤፌ6፥20
5፥21 ሮሜ1፥17፣ 1ቆሮ1፥30፣ ዕብ4፥15፣ 7፥26፣ 1ጴጥ2፥22፡24፣ 1ዮሐ3፥5
6፥1 1ቆሮ3፥9፣ 15፥2፣ 2ቆሮ5፥20
6፥2 መዝ69፥13፣ ኢሳ49፥8፣ 55፥6
6፥3 ማቴ5፥29፣ ሮሜ14፥13፡20፣ 1ቆሮ8፥9፡13፣ 9፥12፣ 10፥32
6፥5 ሐሥ16፥23፣ 1ቆሮ4፥11፣ 2ቆሮ11፥23-25
6፥6 ሮሜ12፥9፣ 1ቆሮ2፥4፣ 1ተሰ1፥5፣ 1ጢሞ1፥5
6፥7 ሮሜ13፥12፣

### ጳውሎስ የተቀበለው መከራ

[3]አገልግሎታችንእንዳይነቀፍ፣ ለማንም
ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም። [4]ይሁን እንጂ
በምናደርገው ነገር ሁሉ ራሳችንን እንደ እግ
ዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን:- በብዙ
ትዕግሥት፣ በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣
[5]በመገረፍ፣ በመታሰር፣ በሁከት፣ በሥራ
ብዛት፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመራብ፣ [6]በን
ጽሕና፣ በዕውቀት፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት፣
በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር፣ [7]በእ
ውነት ቃል፣ በእግዚአብሔር ኀይል፣ በቀኝና
በግራ እጅ የጽድቅ የጦር ዕቃ በመያዝ፣
[8]በክብርና በውርደት፣ በመመስገንና በመ
ሰደብ፣ ኖረናል፤ ደግሞም እውነተኞች ስን
ሆን ሐሰተኞች ተብለናል፤ [9]የታወቅን ስን
ሆን እንዳልታወቅን ሆነናል፤ ሞተዋል ስን
ባል እነሆ በሕይወት አለን፤ ብንደበደብም
አልተገደልንም፤ [10]ሐዘንተኞች ስንሆን ሁል

6፥7 2ቆሮ4፥2፡7፣ 10፥4፣ ኤፌ6፥10-18 6፥8 ማቴ27፥63፣ 1ቆሮ4፥10፡13 6፥9 ሮሜ8፥36፣ 2ቆሮ1፥8-10፣ 4፥10፡11 6፥10 ማቴ5፥12፣ ሐሥ3፥6፣ ሮሜ8፥32፣ 1ቆሮ3፥21፣ 2ቆሮ7፥4፣ 8፥9፣ ፊል2፥17፣ 4፥4፣ ቈላ1፥24፣ 1ተሰ1፥6

*[ሠ]5፥21 ወይም የኀጢአት መሥዋዕት*

---

ኤፌ 2፥10)። አማኝ አዲስ ሰው ይሆናል (ገላ 6፥15፣ ኤፌ 2፥10፡15፣ 4፥24፣ ቈላ 3፥10)፣ እግዚአብሔርን ለመምሰል ይታደሳል (4፥16፣ 1ቆሮ 15፥49፣ ኤፌ 4፥24፣ ቈላ 3፥10)፣ በታደሰ ዕውቀት (ቈላ 3፥10) እና ማስተዋል (ሮሜ 12፥2) ክብሩን በመካፈል (3፥18) የቅድስና ኑሮን ይኖራል (ኤፌ 4፥24)።

**5፥18 ከራሱ ጋር አስታረቀን፤** ዕርቅ (ግሪክ፡ "ካታላጌ") የክርስቶስ የቤዛነት ሥራ አንዱ ክፍል ነው፤ ይህም ኀጢአተኛ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ወደ ማድረግ የሚመለስበት ነው፤ (1) የሰው ዘር ያደረገው ኀጢአትና ዐመፅ የእግዚአብሔር ጠላት መሆንንና ከእርሱ መለየትን አስከትሎአል (ኤፌ 2፥3፤ ቈላ 1፥21)። ይህ ዐመፅ የእግዚአብሔርን ቍጣና ፍርድ አመጣ (ሮሜ 1፥18፡24-32፤ 1ቆሮ 15፥25-26፤ ኤፌ 5፥6)።

(2) ክርስቶስ በፈጸመው ስርየትን በሚያስገኘው ሞቱ እግዚአብሔር የኀጢአትን ግድግዳ አፈረሰ፤ ኀጢአተኛውም ወደ እግዚአብሔር የሚመለስበትን መንገድ ከፈተ (ቍ 19፤ ሮሜ 3፥25፤ 5፥10፤ ኤፌ 2፥15-16)።

(3) ዕርቁ ውጤታማ የሚሆነው እያንዳንዱ ሰው በግሉ ንስሓ ሲገባና በክርስቶስ ሲያምን ነው (ማቴ 3፥2፤ ሮሜ 3፥22)።

(4) ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁ ዘንድ ጥሪ በማድረግ የማስታረቅ አገልግሎት ተሰጥቶአታል (ቍ 20፤ ሮሜ 3፥25 እና ማብ ይመ)።

**5፥21 ኀጢአት የሌለበትን እርሱን … ኀጢአት አደረገው፤** ቅዱሳት መጻሕፍት በየትኛውም ስፍራ ክርስቶስ "ኀጢአተኛ" ነው ብለው አይናገሩም፤ ምክንያቱም እርሱ እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ነበረ። ይሁን እንጂ ክርስቶስ የእኛን ኀጢአት በራሱ ላይ አድርጎአል (በገጽ 202 ላይ፣ *"የስርየት ቀን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ ክርስቶስ ስለ እኛ ኀጢአት በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሲሆን (ኢሳ 53፥10)፣ እግዚአብሔር አብም ፍርዱን በእርሱ በክርስቶስ ላይ አደረገ። ክርስቶስ የእኛን ቅጣት በመቀበሉ፣ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን በጽድቅ ይቅር እንዲል አደረገው (ኢሳ 53፥5 እና ማብ፤ ሮሜ 3፥24-25 እና ማብ ይመ)።

**5፥21 የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፤** (1) በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ጽድቅ፣ ሕግን በመፈጸም የሚገኘውን ጽድቅ የሚያመለክት አይደለም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጆች አዲስ ፍጥረት ከመሆናቸው የተነሣ የሚያገኙት ጽድቅ ነው፤ ይኸውም በክርስቶስ የተመሠረተውና በእርሱም ከማመናቸው የተነሣ የሚገኘውን ባሕርያቸውንና ግብረገባዊ ሕይወታቸውን የሚያመለክት ነው (ፊል 3፥9፤ ሮሜ 3፥21 እና ማብ፤ 4፥22 እና ማብ ይመ)። የምንባቡ አጠቃላይ ዐውድ (ቍ 14-21) "በክርስቶስ ፍቅር" ተይዘው (ቍ 14) አዲስ ፍጥረት በመሆን (ቍ 17) የእግዚአብሔርና በዓለም ውስጥ ያለው የእርሱ ጽድቅ ተወካይ ሆነው የማስታረቅን አገልግሎት እየፈጸሙ (ቍ 18-20፤ በ1ቆሮ 1፥30 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የአማኝ ጽድቅ መሆኑን በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ) ለክርስቶስ የሚኖሩትን አማኞች (ቍ 15) የሚመለከት ነው።

(2) የእግዚአብሔር ጽድቅ የሚገለጠውና አማኝ በዚህ ዓለም በሕይወቱ ተግባራዊ የሚያደርገው በክርስቶስ ሲኖር ነው። የእግዚአብሔር ጽድቅ ልንሆን የምንችለው ከክርስቶስ ጋር በአንድነትና በኅብረት እስከኖርን ድረስ ብቻ ነው (ዮሐ 15፥4-5፤ ገላ 2፥20 እና ማብ፤ 1ዮሐ 1፥9 ይመ)።

**6፥1 የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት፤** ሐዋርያው ጳውሎስ አማኝ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደሚቀበልና ድነትን እንደሚያገኝ ያምናል (ቍ 2)፤ ከዚያም በኋላ ያመነው ሰው በመንፈሳዊ ግዴለሽነት ወይም ሆን ተብሎ በሚደረግ ኀጢአት፣ እምነትንና የወንጌልን ሕይወት በመተው እንደ ገና እንደሚጠፋም በሚገባ ያውቃል። ሰዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁና ጸጋውን እንዲቀበሉ ልናደፋፍራቸው ይገባል (5፥20)። የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚቀበሉም በከንቱ እንዳልተቀበሉ ማወቅ አለባቸው (ከቍ 14-18 ጋር ያነጻጽሩ)።

**6፥4 በመከራ … በጭንቀት፤** በ11፥23 ላይ የሐዋርያው ጳውሎስን ሥቃይ በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

ጊዜ ደስተኞች ነን፤ ድኾች ስንሆን ብዙዎ
ችን ባለጠጎች እናደርጋለን፤ ምንም የሌለን
ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።
[11]የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፤ ሁሉን በግልጽ
ነግረናችኋል፤ ልባችንንም ወለል አድርገን
ከፍተንላችኋል። [12]ፍቅራችሁን የነፈጋችሁን
እናንተ ናችሁ እንጂ እኛስ ፍቅራችንን አል
ነፈግናችሁም። [13]ልጆቼ እንደ መሆናችሁ
መጠን ይህን አሳስባችኋለሁ፤ እናንተም
በዚያው ልክ ልባችሁን ወለል አድርጋችሁ
ክፈቱልን።

## ከማያምኑ ሰዎች ጋር አለመተባበር

[14]ከማያምኑ ሰዎች ጋር አግባብ ባልሆነ
መንገድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዐመፅ ጋር ምን
ግንኙነት አለው? ብርሃንስ ከጨለማ ጋር ምን
ኅብረት አለው? [15]ክርስቶስ ከቤልሆር[*] ጋር
ምን ስምምነት አለው? የሚያምን ከማያምን
ጋር ምን ኅብረት አለው? [16]የእግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ከጣዖታት ጋር ምን ስምምነት
አለው? እኛኮ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ
መቅደስ ነን፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል
ተናግሯል፤ "ከእነርሱ ጋር እኖራለሁ፤
በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፤ አምላካቸው
እሆናለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።"
[17]"ስለዚህ ከመካከላቸው ውጡ፤
ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤
ይላል ጌታ።
ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤
እኔም እቀበላችኋለሁ።"
[18]"እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤
እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ
ትሆናላችሁ፤
ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።"

7 እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ
ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚ

6፥11 2ቆሮ7፥3
6፥13 2ቆሮ7፥2፤ 1ተሰ2፥11
6፥14 ዘዳ24፥3፤ ዘጸ 22፥10፤ 1ቆሮ5፥9:10፤ 6፥6፤ ኤፌ5፥7:11፤ 1ዮሐ1፥6
6፥15 ሐሥ5፥14፤ 1ቆሮ6፥6፤ 10፥21
6፥16 ዘሌ26፥12፤ ኤር32፥38፤ ሕዝ37፥27፤ ማቴ16፥16፤ 1ቆሮ3፥16፤ 10፥21፤ ራእ21፥3
6፥17 ኢሳ52፥11፤ ሕዝ20፥34:41፤ ራእ18፥4
6፥18 ዘፀ4፥22፤ 2ሳሙ 7፥18:4፤ 1ዜና 17፥13፤ ኢሳ43፥6፤
6፥18 ሮሜ8፥14 7፥1 1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ6፥17:18፤ 1ተሰ4፥7፤ 1ጴጥ1፥15:16

---

**6፥10 ድኾች፤** በእውነት ራሱን ለክርስቶስ የሰጠ ክርስቲያን በገንዘብ ቢደኸይ ከወንጌል ትምህርት ጋር የሚቃረን አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ ያለው የዚህ ዓለም ብልጽግና እጅግ ጥቂት እንደ ነበር አስረግጦ ነግሮናል፤ ይሁን እንጂ እርሱ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ መሆኑ መጠን ብዙዎችን በመንፈሳዊ ረገድ ባለ ጸጋ አድርጓል (ከ8፥9፤ ከሐሥ 3፥1 ...፤ ከኤፌ 3፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

**6፥14 ከማያምኑ ሰዎች ጋር ... አትጠመዱ፤** በእግዚአብሔር ዐይን ሰዎች በመጨረሻ በሁለት ተቃራኒ ክፍሎች ይከፈላሉ፤ እነርሱም በክርስቶስ የሆኑትና በክርስቶስ ያልሆኑት ናቸው (ቊ 14-16 እንዲሁም በገጽ 1782 ላይ፣ *"ሦስት ዐይነት ሰዎች"* ብሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ስለዚህ አማኞች በፈቃደኝነት ላይ በተመሠረተ ወዳጅነት ወይም እጅግ መቀራረብ ባለበት ኅብረት ከማያምኑ ሰዎች ጋር መጣመድ የለባቸውም፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነቱ ግንኙነት ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ኅብረት ሊያበላሽባቸው ይችላል። ይህም የንግድ ሽርክናን፣ በስውር አብሮ ማደርን፣ መተጫጨትን፣ ጋብቻንና የቅርብ ጓደኝነትን ይጨምራል። ክርስቲያን ከማያምን ሰው ጋር መተባበር ያለበት በማኅበራዊ ወይም በኢኮኖሚያዊ ረገድ ለኑሮው አስፈላጊ ሲሆን ወይም ለማያምኑ ሰዎች የድነትን መንገድ ለማሳየት ከተፈለገ ብቻ መሆን አለበት (በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖታት ጋር፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ዳግም የተወለደ አማኝ የእግዚአብሔርና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ መሆኑ (ዮሐ 14፥23፤ 1ቆሮ 6፥19 እንዲሁም በገጽ 641 ላይ፣ *"ቤተ መቅደሱ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) አጋንንት ሊያድርበት እንደማይችል በአጽንዖት ተናግሯል። (1) በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ጣዖታት አጋንንትን ይወክላሉ (ዘዳ 32፥17፤ 1ቆሮ 10፥20-21 እንዲሁም በገጽ 428 ላይ፣ *"የጣዖት አምልኮ ባሕርይ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን እጅግ አስከፊው ርኩሰት በራሱ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ጣዖታትን ማቆም ነው (2ነገ 21፥7:11-14)። ልክ እንደዚሁ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነውን አካላችንን አጋንንት የፈለጉትን እንዲያደርጉበት በመፍቀድ ማርከስ የለብንም (*"ቤልሆር"* የሚለው ቃል ሰይጣንን እንደሚያመለክት ከተጠቀሰበት ከቊ 15 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 10፥19 እና ማብ፤ 2ጢሞ 2፥25-26፤ 1ዮሐ 4፥4፤ 5፥18 ይመ)።

(2) በእውነተኛ አማኝ ሕይወት ውስጥ ክፉ መንፈስና መንፈስ ቅዱስ አብረው መኖር ባይችሉም፣ ሙሉ በሙሉ ባልተለወጠ ሰው ሕይወት ውስጥ ክፉ መንፈስ ሊኖር ይችላል (በገጽ 1606 ላይ፣ *"ዳግም ልደት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የተወሰኑ የኃጢአት ችግሮች ያሉበት ነገር ግን ክርስቶስን በእውነት ለመከተል ከሚሻ ሙሉ በሙሉ ካልተለወጠ ሰው አጋንንትን ማስወጣት ሊያስፈልግ ይችላል። በውስጡ ያለው የአጋንንት ኀይል ወይም የክፋት አሠራር ምሽግ እስኪሰበር ድረስ (በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ያ ሰው ሙሉ ድነትን ላያገኝና *"የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ"* ላይሆን ይችላል (ከማቴ 12፥28-29 ጋር ያነጻጽሩ)።

**6፥17 የተለያችሁ ሁኑ፤** በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሐፍ ይመልከቱ።

**7፥1 ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፤** የመለየትና የቅድስና ሕይወት የሌለው ሰው በምዕራፍ 6፥16-18 የተዘረዘሩት እግዚአብሔር በጸጋው የተናገራቸው የተስፋ ቃሎች ይገባኛል በማለት መጠየቅ እንደማይችል ሐዋርያው ጳውሎስ ያለ ጥርጥር በግልጽ ተናግሯል (በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ አንዳንዶች ክርስቲያናዊ ደስታቸውን (ዮሐ 15፥11)፣ የእግዚአብሔርን ጥበቃ (ዮሐ 17፥12:14-15)፣ የጸሎት መልሳቸውን (ዮሐ 15፥7:16) እና የእግዚአብሔርን አባታዊ ሀልዎት (ዮሐ 14፥21:23) በግልጽ ለምን እንዳጡ በግልጽ ያመለክታል። ከዓለም ጋር ተመሳስሎ መኖር የእግዚአብሔርን ሀልዎትና የተስፋ ቃል ማጣት ነው።

**7፥1 ራሳችንን እናንጻ፤** አማኞች ከማንኛውም ዐይነት ርኩሰት ጋር ተመሳስሎ ከመኖር መለየትና ባለማቋረጥም በኀጢአት የተሞላውን የሥጋን ምኞት ከመፈጸም መራቅ አለባቸው። በኀጢአት የተሞላውን ድርጊታችንን መግደል አለብን፤ ኀጢአታችንን ይበልጥ በመጥላትም ከድርጊቶቻችን መሸሽ ይኖርብናል (ቊ 9-11፤ ሮሜ 8፥12-13፤ ገላ 5፥16)።

ያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚ
7፥1 አብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም
14 እናድርገው።

## የጳውሎስ ደስታ

2ልባችሁን አስፉልን፤ እኛ ማንንም
አል በደልንም፤ ማንንም ወደ ብልሹነት
አልመ ራንም፤ ማንንም አላታለልንም።
3ይህንየምለው ልኰንናችሁ አይደለም፤
ምክንያ ቱም ከዚህ በፊት እንደ ነገርኋችሁ፣
በል ባችን ውስጥ ስፍራ አላችሁ፤ ስለዚህ
ብንኖርም ብንሞትም አብረን ነው። 4በእናንተ
ላይ ያለኝ እምነት ትልቅ ነው፤ በእናንተም
ላይ ያለኝ ትምክሕት ትልቅ ነው፤ እንዲሁም
እጅግ ተጽናንቻለሁ፤ በመከራ ችንም ሁሉ
ደስታዬ ወሰን የለውም።

5ወደ መቄዶንያ በመጣን ጊዜ ከየአቅጣ
ጫው መከራ ደረሰብን እንጂ ሰውነታችን
ዕረፍት አላገኘም፤ ከውጭ ጠብ፣ ከውስጥ
ደግሞ ፍርሀት ነበረብን። 6ይሁን እንጂ ሐዘ
ንተኞችን የሚያጽናና አምላክ በቲቶ መም
ጣት አጽናናን። 7የተጽናናነውም በመምጣቱ
ብቻ ሳይሆን፣ እርሱንም ልታጽናኑት በመ
ቻላችሁ ጭምር ነው። ስለ ናፍቆታችሁ፣
ስለ ሐዘናችሁና ለእኔም ስላላችሁ ቅናት ነግ
ሮናል፤ ስለዚህ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ደስ
ብሎኛል።

8በመልእክቴ ባሳዝናችሁም በዚህ አልጸ
ጸትም፤ ብጸጸትም እንኳ መልእክቴ ያሳዘና
ችሁ ለጥቂት ጊዜ እንደ ሆነ ተረድቻለሁ።
9አሁን ግን ደስ ብሎኛል፤ ደስታዬም ስላዘ
ናችሁ ሳይሆን፣ ሐዘናችሁ ንስሓ ለመግባት
ስላበቃችሁ ነው፤ ምክንያቱም ሐዘናችሁ
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ ከእኛ የተነሣ
ምንም አልተጐዳችሁም። 10እንደ እግዚአብ
ሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ወደ ድነት ለሚያደ
ርስ ንስሓ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበትም።
ዓለማዊ ሐዘን ግን ለሞት ያበቃል። 11ይህ
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው ሐዘን እን
ዴት ያለ ትጋት፣ እንዴት ያለ መልስ የመስ
ጠት ችሎታ፣ እንዴት ያለ ቍጣ፣ እንዴት
ያለ ፍርሀት፣ እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት
ያለ በጎ ቅናት፣ እንዴት ያለ ተግሣጽ እንዳ
ስገኘላችሁ ተመልከቱ። በዚህም ጒዳይ ንጹ
ሓን መሆናችሁን በሁሉ ረገድ አስመስክ
ራችኋል። 12እንግዲህ እኔ የጻፍሁላችሁ ስለ
በደለው ወይም ስለ ተበደለው ሰው አይደ
ለም፤ ነገር ግን ለእኛ ምን ያህል ታማኞች
እንደ ሆናችሁ፣ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን
እንድታዩ በማለት ነው። 13እኛም የተጽና
ናነው በዚህ ምክንያት ነው።

ከእኛም መጽናናት በተጨማሪ በቲቶ
ደስታ እኛም ይበልጥ ደስ ብሎናል፤ ምክን
ያቱም ሁላችሁም መንፈሱን አሳርፋች
ኋል። 14በእናንተ ላይ ያለኝን ትምክሕት
ለእርሱ ነግሬው ነበር፤ እናንተም አላሳፈ
ራችሁኝም። ነገር ግን ስንነግራችሁ የነበ
ረው ሁሉ እውነት እንደ ሆነ፣ እንደዚሁም
ስለ እናንተ ለቲቶ በትምክሕት የነገርነው
እውነት መሆኑ ተረጋግጦአል። 15እርሱም
በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ እንዴት እንደ
ተቀበላችሁትና ሁላችሁም እንደ ታዘዛችሁ
ሲያስታውስ ለእናንተ ያለው ፍቅር እየበ
ረታ ሄዶአል። 16እኔም በማናቸውም ነገር
ልተማመንባችሁ በመቻሌ ደስ ብሎኛል።

## የልግስና አስፈላጊነት

8 ወንድሞች ሆይ፤ እግዚአብሔር በመቄዶ
ንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰ
ጠውን ጸጋ እንድታውቁ እንፈልጋለን። 2የደ

7፥2 2ቆሮ6፥12፡13
7፥3 2ቆሮ6፥11፡12፤ ፊል1፥7
7፥4 ቍ13፡14፤ 2ቆሮ6፥10፤ 8፥24
7፥5 ዘዳ32፥25፤ ሐሥ16፥9፤ 2ቆሮ2፥13፤ 4፥8
7፥6 ቍ13፤ 2ቆሮ1፥3፡4፤ 2፥13
7፥8 2ቆሮ2፥2፡4
7፥10 ሐሥ11፥18
7፥11 ቍ7
7፥12 ቍ8፤ 1ቆሮ5፥1፡2፤ 2ቆሮ2፥3፡9
7፥13 ቍ6፤ 2ቆሮ2፥13
7፥14 ቍ4፡6
7፥15 መዝ55፥5፤ 1ቆሮ2፥3፤ 2ቆሮ2፥9፤ 10፥6፤ ፊል2፥12
7፥16 2ቆሮ2፥3
8፥1 ሐሥ16፥9
8፥2 ዘፀ36፥5፤ 2ቆሮ9፥11

ሠ7፥15 ግሪኩ ቤሌየር

**7፥5 መከራ ... ፍርሀት፤** የውጭ ችግሮችና የውስጥ ፍርሀቶች በእውነት ራሱን በሰጠና ዳግም በተወለደ አማኝ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ ሐዋርያው ጳውሎስ ከተናገረው ቃልና ከነበረው ተመክሮ እንገነዘባለን::

**7፥6 ሐዘንተኞችን የሚያጽናና፤** እግዚአብሔር የምሕረትና የመጽናናት አምላክ እንደ መሆኑ መጠን (1፥3) የተጨነቁትንና ያዘኑትን ማጽናናት የእርሱ ባሕርይ ነው:: በእርግጥ ብዙ በተጨነቅን ቍጥር፣ በሕይወታችን የክርስቶስ ማጽናናት እጅግ ይበዛል፤ ህልዎቱም ለእኛ ቅርብ ይሆናል:: በቲቶ አማካይነት እግዚአብሔር ሐዋርያው ጳውሎስን እንዳጽናና ልብ ይበሉ:: በችግር ውስጥ ያለን ሰው ለማጽናናት ምንጊዜም ቢሆን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ማስተዋል ይኖርብናል::

**7፥10 እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ... ዓለማዊ ሐዘን፤** ሐዋርያዊ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ሁለት የሐዘን ዐይነቶችን አመልክቶአል፤ (1) ስለ ኀጢአታችን በመጸጸት የምናሳየው ወደ ንስሓ የሚመራ እውነተኛ ሐዘን አለ፤ ይኸውም ከኀጢአት ሕይወት ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ የሚያደርግ የልብ መለወጥ ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ንስሓ ወደ ድነት ይመራል:: ለሐዋርያው ጳውሎስ ከኀጢአት ንስሓ ገብቶ በእምነት ወደ ክርስቶስ መመለስ፣ ሰው ድነትን ለማግኘት ሊያደርገው የሚገባ ኀላፊነት ነው (ማቴ 3፥2 እና ማብ ይመ)፤ (2) በሌላ በኩል ንስሓ ያልገቡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚያዝኑት ኀጢአታቸው ካስከተለባቸው መዘዝ የተነሣ ብቻ ነው፤ እንዲህ ዐይነቱ ሐዘን ዘላለማዊ ሞትንና ፍርድን ያስከትላል (ማቴ 13፥42፡50፤ 25፥30፤ ሮሜ 6፥23)::

**8፥1 በመቄዶንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት፤** ከ8፥1—9፥15 ይመልከቱ:: ምዕራፍ 8 እና 9 በኢየሩሳሌም ላሉ ድኾች ምእመናን ልግስና ስለማድረግ መመሪያ የተሰጠበት ክፍል ነው:: የሐዋርያ ጳውሎስ የተናገራቸው ቃሎች በአዲስ ኪዳን ስለ ክርስቲያናዊ ልግስና ከተሰጠው ትምህርት እጅግ በሰፋት የተገለጸውን ሐሳብ የያዙ ናቸው:: በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት መርሖች ለአማኞችና ለአብያተ ክርስቲናት በማንኛውም ጊዜ የሚጠቅሙ መመሪያዎች ናቸው (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)::

**8፥2 ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር፤** ምዕራፍ 8 እና 9 ስለ ክርስቲያናዊ ልግስና ዋና ዋና መርሖችንና የተስፋ ቃሎችን ያመለክታሉ፤ (1) እኛ የእግዚአብሔር ነን፤ ያለን ነገር ሁሉ ከእርሱ የተሰጠን በአደራ ነው (ቍ5)፤ (2) ገንዘብን ሳይሆን እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ እንዳለብን በልባችን ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ አለብን (ቍ 5፤ ማቴ 6፥24)፤ (3) የምንሰጠው በችግር ላይ ያሉትን

# የአማኞች መለየት

*2ቆሮ 6፥17-18 "ስለዚህ ከመካከላቸው ወጡ፤ ለእኔም የተለያችሁ ሁኑ፤ ይላል ጌታ። ርኩስ የሆነውን ነገር አትንኩ፤ እኔም እቀበላችኋለሁ። እኔ አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ ትሆናላችሁ፤ ይላል ሁሉን የሚችል ጌታ።"*

---

ከክፉ የመለየት ጽንስ ሐሳብ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ሲታይ እጅግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት መለየት ሁለት አቅጣጫዎችን ያካትታል፤ አንዱ አሉታዊ ሲሆን፣ ሌላው አዎንታዊ ነው። (ሀ) በግብረገባዊና በመንፈሳዊ ረገድ ከኀጢአትና ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ጽድቅንና የእግዚአብሔርን ቃል ከሚጻረር ማንኛውም ነገር ሁሉ ራስን መለየት ነው፤ (ለ) በታማኝነት፣ በአምልኮና በአገልግሎት የቀረበና የጠለቀ ኅብረት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር መጠጋት ማለት ነው። መለየት ከእነዚህ ከሁለቱ ጣምራ ትርጉሞች አንጻር ከእኛ ጋር ከሚኖረውና አምላካችን ከሆነው ከሰማያዊው አባታችን ከእግዚአብሔር ጋር እንድንገናኝ ያደርገናል፤ እኛም በሌላ በኩል ወንድና ሴት ልጆቹ እንሆናለን (2ቆሮ 6፥16-18)።

(1) በብሉይ ኪዳን መለየት ለእግዚአብሔር ሕዝብ አስፈላጊና መቋረጥ የሌለበት ነገር ነው (ዘፀ 23፥24 እና ማብ፤ ዘሌ 11፥44 እና ማብ፤ ዘዳ 7፥3 እና ማብ፤ ዕዝ 9፥2 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 342 ላይ፣ "የከነዓን መደምሰስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የእግዚአብሔር የራሱ ንብረት ይሆኑ ዘንድ ከሌሎች ሕዝቦች ይልቅ ቅዱስ፣ ልዩና የተለዩ መሆን ይጠበቅባቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በቅጣት ወደ አሶርና ወደ ባቢሎን ተማርከው እንዲሄዱ ያደረገበት አንዱ ቁልፍ ምክንያት ባለማቋረጥ በዙሪያቸው ያሉትን የጣዖት አምላኪዎችንና የክፉዎችን ሕዝቦች የኑሮ ዘይቤ የራሳቸው በማድረግ እነርሱኑ መስለው ለመኖር ስለ ፈለጉ ነበር (2ነገ 17፥7-8 እና ማብ፤ 24፥3 እና ማብ፤ 2ዜና 36፥14 እና ማብ፤ ኤር 2፥5፡13 እና ማብ፤ ሕዝ 23፥2 እና ማብ፤ ሆሴ 7፥8 እና ማብ ይመ)።

(2) በአዲስ ኪዳን አማኝ ከሚከተሉት ነገሮች መለየት እንዳለበት እግዚአብሔር ያዛል፤ (ሀ) ብልሹ ከሆነው ከዓለም ሥርዐትና ቅዱስ ካልሆነ ነገር ጋር ተመሳስሎ ከመኖር (ዮሐ 17፥15-16፤ 2ጢሞ 3፥1-5፤ ያዕ 1፥27፤ 4፥4 እንዲሁም በገጽ 2022 ላይ፣ "ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (ለ) በቤተ ክርስቲያን እያሉ ኀጢአትን ከሚሠሩና ንስሓ ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆኑ ሰዎች (ማቴ 18፥15-17፤ 1ቆሮ 5፥9-11፤ 2ተሰ 3፥6-15) እና (ሐ) የተሳሳተ የሥነ መለኮት ትምህርት ከሚያስተምሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች፣ ቤተ ክርስቲያኖች ወይም የባዕድ እምነት አራማጆች እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነት ከሚክዱ ሰዎች (ማቴ 7፥15፤ ሮሜ 16፥17፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ ቲቶ 3፥9-11፤ 2ጴጥ 2፥17-22፤ 1ዮሐ 4፥1፤ 2ዮሐ 1፥10-11፤ ይሁ 1፥12፡13)።

(3) መለየትን በተመለከተ ሊኖረን የሚገባው አስተሳሰብ የሚከተለው መሆን አለበት፤ (ሀ) ኀጢአትን፣ ርኩሰትንና ብልሹ የሆነውን የዓለምን ሥርዐት መጥላት (ሮሜ 12፥9፤ ዕብ 1፥9፤ 1ዮሐ 2፥15)፤ (ለ) ሐሰተኛ አስተምህሮን መቃወም (ገላ 1፥9)፤ (ሐ) ከኀጢአታቸው የተነሣ ልንለያቸው ለሚገባን ሰዎች እውነተኛ ፍቅርን መግለጥ (ዮሐ 3፥16፤ 1ቆሮ 5፥5፤ ገላ 6፥1፤ ከሮሜ 9፥1-3፤ ከ2ቆሮ 2፥1-8፤ 11፥28-29፤ ከይሁ 1፥22 ጋር ያነጻጽሩ) እና (መ) ቅድስናችንን ፍጹም ለማድረግ እግዚአብሔርን መፍራት (2ቆሮ 7፥1)።

(4) የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ መሆናችን መጠን የመለየታችን ዐላማ የሚከተለው መሆን አለበት፤ (ሀ) ባገኘነው ድነት (1ጢሞ 4፥16፤ ራእ 2፥14-17)፣ በእምነት (1ጢሞ 1፥19፤ 6፥10፡20-21) እና በቅድስና (ዮሐ 17፥14-21፤ 2ቆሮ 7፥1) ጸንቶ መቆም፤ (ለ) እግዚአብሔርን ጌታና አባት በማድረግ ሙሉ በሙሉ መኖር (ማቴ 22፥37፤ 2ቆሮ 6፥16-18) እና (ሐ) የማታምነውን ዓለም ወደ እውነትና ወደ ወንጌል በረከቶች ማምጣት (ዮሐ 17፥21፤ ፊል 2፥15)።

(5) ራሳችንን በሚገባ ለእርሱ ከለየን እግዚአብሔር ራሱ በጥበቃው፣ በበረከቱና በአባታዊ እንክብካቤው ወደ እኛ በመቅረብ ደስ ያሰኘናል። መልካም አባት መሆን ያለበትን ሁሉ ሊሆንልን ቃል ገብቶልናል። እርሱ መካሪያችንና መሪያችን ይሆናል፤ የገዛ ልጆቹ በመሆናችን ይወደናል፤ ይንከባከበናል (2ቆሮ 6፥16-18)።

(6) አማኞች ራሳችንን ከክፉ ለመለየት ፈቃደኞች ባንሆን የሚከሠተው አሳዛኝ ውጤት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት (2ቆሮ 6፥16)፣ ከአብ ያገኘነውን ተቀባይነት (6፥17) እና የልጅነት መብት (6፥18፤ ከሮሜ 8፥15-16 ጋር ያነጻጽሩ) ማጣት ይሆናል።

ረሰባቸው መከራ ጽኑ ቢሆንም ደስታቸው
ግን የላቀ ነበር፤ ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆ
ንም ልግስናቸው ግን የበዛ ነበር። 3እንደ
ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከዐቅማቸው በላይ
በፈቃዳቸው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁ።
4እነርሱም ቅዱሳንን ለመርዳት በሚደረገው
አገልግሎት ለመሳተፍ ዕድል ያገኙ ዘንድ
አጥብቀው ይለምኑን ነበር። 5እኛ ከጠበቅ
ነው በላይ፣ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ
ሰጡ፤ ቀጥለውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳ
ቸውን ለእኛ ሰጡ። 6ስለዚህ ቲቶ፣ በእና ንተ
መካከል ቀደም ሲል የጀመረውን የልግ ስና
ሥራ ከፍጻሜ እንዲያደርስ ለምነነው ነበር።
7እናንተም በሁሉ ነገር ይኸውም በእምነት፣
በቃል፣ በዕውቀት፣ በፍጹም ትጋ ትና
ለእኛም ባላችሁ ፍቅር<sup>ሩ</sup> ልቃችሁ እንደ
ተገኛችሁ፣ በዚህም የቸርነት ሥራ ልቃችሁ
እንድትገኙ ዐደራ እንላችኋለን።
8ይህን የምለው ትእዛዝ ለመስጠት ብዬ
አይደለም፤ ነገር ግን ሌሎች ከሚያሳዩት
ትጋት አንጻር የፍቅራችሁን እውነተኛነት
ለማረጋገጥ ነው። 9የጌታችንን የኢየሱስክር
ስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ ድኽነት
እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሀብ
ታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድኻ ሆነ።
10ስለዚህጉዳይየምሰጣችሁጠቃሚምክር
ይህ ነው፤ ባለፈው ዓመት በመስጠት ብቻ
ሳይሆን ለመስጠት በማሰብም ቀዳሚ ነበራ
ችሁ፤ 11አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር
በዐቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት፤
ይህም ለመስጠት የነበራችሁ በጎ ፈቃድ
እውን እንዲሆን ነው። 12ለመስጠት በጎ ፈቃድ
ካለን ስጦታው ተቀባይነት የሚያገኘው
ባለን መጠን ስንሰጥ እንጂ፣ በሌለን
መጠን ለመስጠት ስንሞክር አይደለም።
13ይህንን የምንለው እናንተ ተቸግራችሁ
ሌሎች ይድላቸው ለማለት ሳይሆን፣ ሁላ
ችሁም እኩል እንድትሆኑ ነው። 14በአሁኑጊዜ
የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጕድለት
ያሟላል፤ የእነርሱም ደግሞ በተራው የእ
ናንተን ጕድለት ያሟላል፤ በዚህም ያላች
ሁን እኩል ትካፈላላችሁ። 15ይህም፣ "ብዙ

8፥3 1ቆሮ16፥2
8፥4 ቍ1፤ ሐሥ9፡ 13፤ 24፥17
8፥6 ቍ10፡11፡ 16፡17፡23፤ 2ቆሮ2፥13፤ 12፥18
8፥7 ሮሜ15፥14፤ 1ቆሮ1፥5፤ 12፥8፤ 13፥1፡2፤ 14፥6፤ 2ቆሮ9፥8
8፥8 1ቆሮ7፥6
8፥9 ማቴ20፥28፤ ሮሜ3፥24፤ 2ቆሮ6፥10፤ 13፥14፤ ፊል2፥6-8
8፥10 1ቆሮ7፥25፡ 40፤ 16፥2፡3፤ 2ቆሮ9፥2
8፥11 ቍ12፡19፤ ዘፀ25፥2፤ 2ቆሮ9፥2
8፥1 2ማር12፥43፡44፤ 2ቆሮ9፥7
8፥14 ሐሥ4፥34፤ 2ቆሮ9፥12
8፥15 ዘፀ16፥18
8፥16 2ቆሮ2፥13፡14፤ ራእ17፥17
8፥17 ቍ6
8፥18 1ቆሮ7፥17፤ 2ቆሮ2፥12፤ 12፥18
8፥19 ቍ11፡12፤ ሐሥ14፥23፤ 1ቆሮ16፥3፡4
8፥21 ሮሜ12፥17፤ 14፥18፤ ቲቶ2፥14
8፥23 ቍ18፡22፤ 2ቆሮ2፥13፤ ፊል2፥25፤ ፊሞ17
8፥24 2ቆሮ7፥4፡ 14፤ 9፥2
9፥1 ሐሥ9፥13፤ 24፥17፤ 1ተሰ4፥9
9፥2 ሐሥ18፥12፤ 2ቆሮ7፥4፡14፤

የሰበሰበ አላትረፈም፤ ጥቂት የሰበሰበም
አልጐደለበትም" ተብሎ እንደ ተጻፈው
ነው።

## ቲቶ ወደ ቆሮንቶስ ተላከ

16እኔ ለእናንተ ያለኝን በጎ ሐሳብ በቲቶ
ልብ ውስጥ ያኖረ አምላክ የተመሰገነ ይሁን፤
17ምክንያቱም ቲቶ ወደ እናንተ የመጣው
ልመናችንን በመቀበል ብቻ ሳይሆን፣ በታ
ላቅ ጕጕትና በራሱ ፈቃድ በመነሣሣት
ነበር። 18ከእርሱም ጋር በወንጌል ስብከት
በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን
ወንድም ልከነዋል። 19ከዚህም በላይ ስጦ
ታውን በምንወስድበት ጊዜ አብሮን እንዲ
ሄድ በአብያተ ክርስቲያናት ተመርጦአል፤
ስጦታውንም የምንወስደው ጌታን ራሱን
ለማ ክብርና ሌሎችን ለመርዳት ካለን በጎ
ፈቃድ የተነሣ ነው። 20በዚህ በምናከናውነው
የቸ ርነት ሥራ አንዳች ነቀፋ እንዳይገኝብን
እንጠነቀቃለን። 21ምክንያቱም ዐላማችን
በጌታ ፊት ብቻ ሳይሆን፣ በሰውም ፊት
መል ካም የሆነውን ነገር ማድረግ ነው።
22ደግሞም ብዙ ጊዜ በብዙ መንገድ ተፈ
ትኖ ትጉ ሆኖ የተገኘውን ወንድማችንን
ከእነርሱ ጋር ልከነዋል፤ አሁንም በእናንተ
እጅግ ከመታመኑ የተነሣ ከመቼውም ጊዜ
ይልቅ እየተጋ ነው። 23ስለ ቲቶ የሚጠይቅ
ቢኖር፣ እርሱ እናንተን ለማገልገል አብሮኝ
የሚሠራ ባልደረባዬ ነው፤ ስለ ወንድሞቻ
ችንም የሚጠይቅ ቢኖር እነርሱ የአብያተ
ክርስቲያናት ተወካዮችና የክርስቶስ ክብር
ናቸው። 24ስለዚህ የፍቅራችሁን እውነተኛ
ነትና በእናንተም የምንታመነው የቱን ያህል
እንደ ሆነ በአብያተ ክርስቲያናት ፊት ግለ
ጡላቸው።

9 ለቅዱሳን ስለሚደረገው አገልግሎት
ልጽፍላችሁ አያስፈልግም። 2ምክንያ
ቱም ሌሎችን ለመርዳት ያላችሁን በጎ
ፈቃድ ዐውቃለሁ፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ

9፥2 8፥10፡11፡ 12፡19፡24

ሩ8፥7 አንዳንድ ቅጆች ለእናንተ ባለን ፍቅር

ለመርዳት (ቍ 14፤ 9፥12፤ ምሳ 19፥17፤ ገላ 2፥10፤ እንዲሁም በገጽ 1327 ላይ፣ *"ድኾችንና ችግረኞችን መርዳት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት (1ቆሮ 9፥14፤ ፊል 4፥15-18)፣ በሰማይ ሀብትን ለማከማቸት (ማቴ 6፥20፤ ሉቃ 6፥32-35) እና ፈሪሀ እግዚአብሔርን ለመማር (ዘዳ 14፥22-23) ነው፤ (4) የምንሰጠው በምናገኘው ገቢ መጠን መሆን አለበት (ቍ 3፡12፤ 1ቆሮ 16፥2)፤ (5) የምንሰጠው ፍቅራችንን ለመግለጥ ሲሆን (ቍ 24)፣ መደረግ ያለበትም በመሥዋዕትነትና (ቍ 3) በፈቃደኝነት (9፥7) ነው፤ (6) ለእግዚአብሔር ስንሰጥ የምንዘራው ገንዘብን ብቻ ሳይሆን እምነትን፣ ጊዜንና አገልግሎትን ጭምር ነው፤ የምናጭደውም ታላቅ እምነትና በረከት ይሆናል (ቍ 5፤ 9፥6፡10-12)፤ (7) እግዚአብሔር የተትረፈረፈ በረከትን ሲሰጠን፣ በጎ ሥራችንን በዚያው መጠን እንድናበዛው ነው (9፥8፤ ኤፌ 4፥28)፤ (8) መስጠት ሕይወታችንን በይበልጥ ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ያደርገናል (ማቴ 6፥21)፤ ከገንዘብ ጋር በተያያዙ ጕዳዮቻችንም ላይ የእግዚአብሔርን ክንድ እንዲገለጥ ያደርጋል (ሉቃ 6፥38)። ስለዚህ ጕዳይ የበለጠ ለመረዳት በገጽ 1406 ላይ፣ *"ዐሥራትና መባ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ።

**8፥9 እርሱ ... ድኻ ሆነ፤** መሥዋዕትነት ተከፍሎ የሚደረግ ስጦታ የክርስቶስ ማንነትና ባሕርይ ዋና ክፍል ነው። እርሱ ስለ እኛ ድኻ በመሆኑ፣ አሁን የእርሱን ዘላለማዊ ብልጥግና ተካፋይ ሆነናል። የእርሱ ጸጋ በውስጣችን መሥራቱ ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በእኛ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ተመሳሳይ አመለካከት እንዲኖር ይፈልጋል። የጸጋና የድነት ስጦታዎች ሁሉ፣ ሰማያዊ መንግሥት፣ ስለ ክርስቶስም በሰዎች ዘንድ ክብርን ማጣት እንኳ ቢሆን በንጢአት ቡትቶ ፈንታ የተቀበልነው ዘላለማዊ ብልጥግና ነው (ሉቃ 12፥15፤ ኤፌ 1፥3፤ ፊል 4፥11-13፡18-19፤ ዕብ 11፥26፤ ራእ 3፥17)።

እናንተ በአካይያ የምትኖሩ ሌሎችን ለመ
ርዳት ዝግጁ እንደ ሆናችሁ ለመቄዶንያ
ሰዎች አፌን ሞልቼ ተናግሬአለሁ፤ ቅን
ፍላጎታችሁም ብዙዎችን ለበጎ ሥራ አነሣ
ሥቶአል። [3]እንግዲህ በዚህ ነገር በእናንተ
ላይ ያለን ትምክሕት ከንቱ ሆኖ እንዳይ
ቀር አስቀድሞ ስለ እናንተ እንደ ተናገር
ሁት ተዘጋጅታችሁ እንድትገኙ ወንድሞ
ችን ልኬአለሁ። [4]ምናልባት የመቄዶንያ
ሰዎች ከእኔ ጋር መጥተው ሳትዘጋጁ ቢያገ
ኟችሁ፣ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ እኛም ያን
ያህል በእናንተ በመመካታችን እናፍራለን።
[5]ስለዚህ ወንድሞች አስቀድመው ወደ እና
ንተ እንዲመጡና ከዚህ በፊት ለመስጠት
ቃል የገባችሁትን ስጦታ አጠናቃችሁ እን
ድትጠብቁቸው፣ እነርሱን መለመን አስፈ
ላጊ ሆኖ አግኝቻለሁ፤ እንግዲህ በልግስና
ለመስጠት ያሰባችሁት ነገር በግዴታ ሳይ
ሆን በፈቃደኝነት የተዘጋጀ ይሆናል።

## በልግስና መስጠት

[6]ይህን አስታውሱ፤ ጥቂት የዘራ ጥቂት
ያጭዳል፤ ብዙ የዘራ ብዙ ያጭዳል። [7]እያ
ንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይ
ሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክን
ያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው
ይወዳል። [8]ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚያስፈ
ልጋችሁን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ
ሁሉ እንድትተርፉ፣ እግዚአብሔር ጸጋን ሁሉ
ሊያበዛላችሁ ይችላል፤ [9]ይህም፣
"በተነ፤ ለድኾችም ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።
[10]ለዘሪ ዘርን፣ ለመብላት እንጀራን የሚ
ሰጥ እርሱ የምትዘሩትን አትረፍርፎ ይሰ

9፥3 1ቆሮ16፥2፤
2ቆሮ8፥23
9፥4 ሮሜ15፥26
9፥5 ቊ3፤
2ቆሮ12፥17፡18፤
ፊል4፥17
9፥6
ምሳ11፥24፡25፤
22፥9፤ ገላ6፥7፡9
9፥7 ዘፀ25፥2፤
ዘዳ 15፥10፤
ሮሜ12፥8፤
2ቆሮ8፥12
9፥8 ኤፌ3፥20፤
ፊል4፥19
9፥9 መዝ112፥9፤
ሚል3፥10
9፥10 ኢሳ55፥10፤
ሆሴ10፥12
9፥11 ቊ5፤
1ቆሮ1፥5፤
2ቆሮ1፥11፤ 4፥15
9፥12 2ቆሮ1፥11፤
8፥14
9፥13 ቊ5፤
ማቴ9፥8፤
2ቆሮ2፥12፤ 8፥4፤
ዕብ13፥1
9፥15
ሮሜ5፥15፡16፤
2ቆሮ2፥14
10፥1
ማቴ11፥29፤
ገላ5፥2፤ ኤፌ3፥1
10፥2 ሮሜ12፥2፤
1ቆሮ4፥21
10፥3 ቊ2
10፥4 ቊ8፤
ኤር1፥10፤
23፥29፤
1ቆሮ2፥5፤
2ቆሮ6፥7፡13፥10

ጣችኋል፤ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያበዛላች
ኋል። [11]ሁልጊዜ በልግስና መስጠት እንድ
ትችሉ በሁሉ ነገር ያበለጽጋችኋል፤
ልግስ ናችሁም በእኛ በኩል የሚደርሳቸው
ሰዎች እግዚአብሔርን ለማመስገን
ምክንያት ይሆናቸ ዋል።
[12]ይህ የምትሰጡት አገልግሎት የቅዱሳ
ንን ጕድለት የሚያሟላ ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ
ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርብበት ነው።
[13]የክርስቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ስለ ታዘ
ዛችሁና ለእነርሱም ሆነ ለሌሎች ስላሳያ
ችሁት ልግስና ሰዎች ተፈትኖ ስላለፈው
አገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤
[14]ስለ እናንተም በሚጸልዩበት ጊዜ እግዚአብ
ሔር ከሰጣችሁ ታላቅ ጸጋ የተነሣ ይናፍቋች
ኋል። [15]በቃላት ሊገለጥ ስለማይቻል ስጦ
ታው እግዚአብሔር ይመስገን።

## ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ያቀረበው መከላከያ

10 እኔ ጳውሎስ፣ በእናንተ ፊት ስሆን
"ዐይነ ዐፋር"፣ ከእናንተ ስርቅ ግን፣
"ደፋር" የተባልሁ በክርስቶስ የዋህነትና ገር
ነት እለምናችኋለሁ። [2]ወደ እናንተ በምመጣ
በት ጊዜ በዓለማዊ መንገድ እንደምንኖር
አድርገው በሚቈጥሩን ሰዎች ላይ በድፍረት
ለመናገር ቈርጫለሁ፤ እናንተን ግን በዚያ
ዐይነት ድፍረት እንድናገር እንዳታደርጉኝ
እለምናችኋለሁ። [3]የምንኖረው በዚህ ዓለም
ቢሆንም፣ የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት
አይ ደለም። [4]ደግሞም የምንዋጋበት የጦር
መሣ ሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤
ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ
የሚችል መለኮ ታዊ ኀይል ያለው ነው።

**9፥6 ጥቂት ያጭዳል፤** ክርስቲያኖች የሚሰጡት በልግስና ወይም በጥቂቱ ሊሆን ይችላል፥ እግዚአብሔር በሰጡት መጠን ይከፍላቸዋል (ማቴ 7፥1-2)፡፡ ለሐዋርያው ጳውሎስ መስጠት ኪሣራ አይደለም፥ ነገር ግን የማይጠፋ ሀብትን የማከማቸት ዘዴ ነው፥ ለሚሰጡ ተመጣጣኝ የሆነ በረከት የሚገኝበትም ነው (8፥2 እና ማብ፥ 9፥11 እና ማብ ይመ)፡፡ ሐዋርያው የሚናገረው ስለ ስጦታው መጠን ሳይሆን፣ ስንሰጥ የልባችን ፍላጎትና አነሣሽ ምክንያት የቱን ያህል ጤናማ መሆን እንዳለበት ለማመልከት ነው፡፡ ድኻይቱ መበለት የሰጠችው ስጦታ እጅግ ጥቂት ነበረ፥ ነገር ግን ካላት ገንዘብ ጋር ሲመጣጠን እጅግ ከፍተኛ በመሆኑና በፍጹም ልብዋ በመስጠትዋ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ተቀበላት፤ (ሉቃ 21፥1-4 እና ማብ ይመ፥ ከምሳ 11፥24-25፤ 19፥17፤ ከማቴ 10፥41-42፤ ከሉቃ 6፥38 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

**9፥8 ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ፤** በችግር ላይ ያሉትን ለመርዳት መስጠት የሚችሉትን ያህል የሚሰጡ ምእመናን ራሳቸው ችግር በሚያጋጥማቸው ወቅት እግዚአብሔር በጸጋው አትረፍርፎ ይሰጣቸዋል፥ በተጨማሪም በጎ ሥራ ሁሉ ይበዛላቸው ዘንድ በበረከት ይሞላሉ (ከኤፌ 4፥28 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

**9፥11 በሁሉ ነገር ያበለጽጋችኋል፤** ልግስና ውጫዊ በሆነ መንገድ ይገለጽ ዘድን ልባችን ለሌሎች ሊኖረን በሚገባ እውነተኛ ፍቅርና ርኅራኄ መበልጸግ አለበት፡፡ ራሳችንንና ንብረታችንን መስጠት የሚከተሉትን ውጤቶች ያመጣል፥ (1) ለድኾች ወንድሞችና እኅቶች ችግር መድረስን፣ (2) ለእግዚአብሔር ውዳሴና ምስጋና ማቅረብን (ቊ 12) እና (3) ከረዳናቸው ወገኖች ፍቅርን መቀበልን ነው (ቊ 14)፡፡

**10፥1 እኔ ጳውሎስ … እለምናችኋለሁ፤** አብዛኞዎቹ የቆሮንቶስ ምእመናን የጳውሎስን ሥልጣን በመቀበል፣ ለትምህርቱና ለሐዋርያነቱ ያላቸውን አክብሮት በትህትና ገልጸዋል (7፥8-16)፡፡ ይሁን እንጂ ወንጌልን በመናቅና የሰይጣንን ሥራ በመሥራት (11፥13) እርሱን እየተቃወሙ እንዲሁም ማንነቱንና ባሕርዩን እያንቋሸሹ ያሉ በሐሰተኛ አገልጋዮች የሚመሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ፡፡ ከምዕራፍ 10-13 ባለው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተላለፈው መልእክት እነዚህን ሐሰተኛ ምእመናንን በተመለከተ ነበር፡፡

**10፥4 የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ፤** ውጊያችን ከክፉ መንፈሳዊያን ሰራዊት ጋር ነው (ኤፌ 6፥12)፡፡ ስለዚህ ሥጋዊ ብልጠት፣ ችሎታ፣ ሀብት፣ ድርጅታዊ ዘዴ፣ እንደበተ ርቱዕነት፣ ፕሮፖጋንዳ፣ ማራኪነትና ሰብእናን የመሳሰሉ ዓለማዊ መሣሪያዎች በራሳቸው የሰይጣንን ምሽግ ለማፍረስ ብቃት የላቸውም፡፡ የሰይጣንን ጠንካራ ምሽግ፣ ርኩሰትንና ሐሰተኛ ትምህርትን ለማፍረስ ብቃት ያላቸው እግዚአብሔር የሚሰጠን መሣሪያዎች ብቻ ናቸው፡፡

5በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት
የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ
እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን
ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን።
6መታዘዛችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለ መታዘዝን
ሁሉ ለመቅጣት ተዘጋጅተናል።
7እናንተ የምትመለከቱት ውጫዊውን
ነገር ብቻ ነው።[a] ማንም የክርስቶስ በመሆኑ
ቢመካ እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ ሁሉ
እኛም የክርስቶስ መሆናችንን ሊገነዘብ ይገ
ባዋል። 8ጌታ በሰጠን ሥልጣን እጅግ ብመ
ካም በዚህ አላፍርም፤ ሥልጣኑን የተቀበል
ነው እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይ
ደለምና። 9በመልእክቶቼ የማስፈራራችሁ
አይምሰላችሁ። 10አንዳንዶች፣ "መልእክቶቹ
ከባድና ጠንካራ ናቸው፤ ነገር ግን ሰውነቱ
ሲታይ ደካማ፣ ንግግሩም የተናቀ ነው"
ይላሉ። 11እንዲህ የሚሉ ሰዎች በሩቅ ሆነን
በመልእክታችን የምንናገረውን ሁሉ በቅ
ርብ ሆነን በተግባራችን የምንገልጸውም እን
ደዚያው መሆኑን መገንዘብ አለባቸው።
12ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ሰዎች ጋር
ራሳችንን ልንመድብ ወይም ልናነጻጽር አን
ደፍርም፤ እነርሱ ራሳቸውን በራሳቸው ሲመ
ዝኑና ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር ሲያነጻ
ጽሩ አስተዋዮች አይደሉም። 13እኛ ግን ከመ
ጠን በላይ አንመካም፤ የምንመካው እግዚአ
ብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም እንኳ
በሚደርሰው የአገልግሎታችን ወሰን ነው።

10፥5 ኢሳ2፥11:12፤ 1ቆሮ1፥19፤ 2ቆሮ9፥13
10፥6 2ቆሮ2፥9፤ 7፥15
10፥7 ዮሐ7፥24፤ 1ቆሮ1፥12፤ 3፥23፤ 14፥37፤ 2ቆሮ5፥12፤ 11፥23
10፥8 ቍ4:13:15፤ ኤር1፥10፤ 2ቆሮ13፥10
10፥10 ቍ1፤ 1ቆሮ1፥17፤ 2፥3፤ 2ቆሮ11፥6፤ ገላ4፥13:14
10፥12 ቍ18፤ 2ቆሮ3፥1
10፥13 ቍ15:16፤ ሮሜ12፥3

*[a]10፥7 ወይም ግልጥ የሆነውን እውነታ ብቻ ነው*
*[b]10፥13-15 ወይም [13]እኛ ግን ከመጠን በላይ ስለሆኑ ነገሮች አንመካም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በመደበልንና እስከ እናንተም እንኳ በሚደርሰው እንመካለን። [14-15]ደግሞ ሌሎች በሠሩት ሥራ ከመጠን በላይ ስለ ሆኑ ነገሮች አንመካም*

(1) እነዚህ *መሣሪያዎች መንፈሳዊና* ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስለሆኑ ብርቱዎች ናቸው:: በሌላ ስፍራ ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን *መሣሪያዎች* በዝርዝር ጠቅሶአል፡ እነርሱም እውነትን አጥብቆ *መያዝ፣* የጽድቅ ኑሮን *መኖር፣* ወንጌልን *ማወጅ፣* እምነት፣ ፍቅር፣ የድነት ተስፋ፣ የእግዚአብሔር ቃልና የማይቋረጥ ጸሎት ናቸው (ኤፌ 6፥11-19፤ 1ተሰ 5፥8):: ቤተ ክርስቲያን እነዚህን *መሣሪያዎች* ይዛ በጠላት ላይ ብትወጣ፣ ድል አድራጊ ትሆናለች:: የእግዚአብሔር ሀልዎትና የእግዚአብሔር *መንግሥት* ኀጢአተኞችን ለማዳን፣ አጋንንትን ለማስወጣት፣ አማኞችን ለመቀደስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ለማጥመቅና በሽተኞችን ለመፈወስ በኀይል ይገለጣል (በገጽ 1527 ላይ፣ *"አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(2) ዛሬ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜ የዓለምን ተግዳሮት በዓለማዊ *መሣሪያ* የመመከት ፈተና አለባት:: እነዚህ ዓለማዊ *መሣሪያዎች ሥጋዊ* ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ የሥነልቡና ዕውቀት፣ አስደሳች መስሕቦች፣ በመዝናናት ላይ የተመሠረቱ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ወዘተ ናቸው:: እነዚህ ነገሮች አብዛኛውን ጊዜ የአዲስ ኪዳን *መሠረታዊ ልምምዶች* የሆኑትን በጸሎት *መጠመድን፣* ለእግዚአብሔር ቃል ባለማወላወል ተገዥ መሆንንና ወንጌልን በኀይል መስበክን ተክተው ሲያገለግሉ የሚታዩ ናቸው:: ዓለማዊ *መሣሪያዎች* የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴ አያመጡም፤ ምክንያቱም እንደዚህ ዐይነት *መሣሪያዎች* የኀጢአትን ብርቱ ምሽግ ሊያፈርሱ፣ ከሰይጣን ኀይል ነጻ ሊያወጡን ወይም ዛሬ በዓለም እየተዛመተ ያለውን የክፋት ስሜት ሊያስወግዱ ፈጽሞ አይችሉም:: የዓለምን *መሣሪያዎች* ብንጠቀም ቤተ ክርስቲያንን ዓለማዊ በማድረግ ከእምነት ከጽድቅና ከመንፈስ ቅዱስ ኀይል *መሣሪያ* እንነጥላታለን:: እንዲህም ከሆነ በሚያሳዝን ሁኔታ ራሷ ቤተ ክርስቲያን በጨለማ ኀይል ትዋጣለች፤ ቤተሰቦችዋም ተጥለው በዓለም ኀይላት በመማረክ ይወሰዳሉ::

**10፥5 አእምሮንም ሁሉ እየማረክን፤** ክርስቲያናዊ ውጊያ አስተሳሰባችን ሁሉ ለክርስቶስ ፈቃድ እንዲገዛ ማድረግንም ይጨምራል:: ይህን ማድረግ አለመቻልም ወደ ኢግብረገባዊነትና ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራል (ሮሜ 6፥16:23፤ 8፥13):: አስተሳሰባችሁን በክርስቶስ ጌትነት ሥር ለማድረግ የሚከተሉትን አራት እርምጃዎች ውሰዱ፤ (1) ማንኛውንም ሐሳብ እግዚአብሔር እንደሚያውቅና ከእርሱም ምንም ነገር ሊሰወር እንደማይችል ልናውቅ ይገባል (*መዝ* 94፥11፤ 139፥2:4:23-24):: ስለምናስበው ነገር እንዲሁም ስለምንናገረው ቃልና ስለ ድርጊታችን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት *መልስ* እንሰጥበታለን (5፥10፤ *መክ* 12፥14፤ *ማቴ* 12፥35-37፤ *ሮሜ* 14፥12)::

(2) አእምሮ የጦር *ሜዳ* እንደ ሆነ ልናውቅ ይገባል:: አንዳንድ ሐሳቦች ከውስጣችን ሲመነጩ፣ ሌሎቹ ደግሞ በቀጥታ ከጠላት ይመጣሉ:: ከመማረኩ በፊት *ማንኛውም* ሐሳብ ከራሳችን ኀጢአተኛ ተፈጥሮና ከሰይጣን ኀይላት ጋር በውስጣችን ጦርነት ያደርጋል (ኤፌ 6፥12-13 *ይመ፤* ከማቴ 4፥3-11 ጋር *ያነጻጽሩ*):: በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ክፉና ጐጂ የሆነውን ሐሳብ ሁሉ በጽናት በመቋቋም ተቃወሙት (ፊል 4፥8):: እንደ አማኝ ጠላታችንን ድል የምናደርገው በበጉ ደም፣ በምስክርነታችን ቃል እንዲሁም ሰይጣንን፣ ፈተናንና ኀጢአትን ባለማቋረጥ "እምቢ" በማለት እንደ ሆነ ልብ ማለት አለብን (ቲቶ 2፥11-12፤ *ያዕ* 4፥7፤ *ራእ* 12፥11 *ይመ፤* ከማቴ 4፥3-11 ጋር *ያነጻጽሩ*)::

(3) ትኩረታችሁን በምድራዊ ነገሮች ላይ ከማድረግ ይልቅ በክርስቶስና በሰማያዊ ነገሮች ላይ ለማድረግ ቍርጥ ውሳኔ አድርጉ (*ፊል* 3፥19፤ *ቈላ* 3፥2)፤ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር ሥር የሆነ አእምሮ ሕይወትና ሰላም ያለበት ነው (ሮሜ 8፥6-7):: አእምሮአችሁን በእግዚአብሔር ቃል (*መዝ* 1፥1-3፤ 19፥7-14፤ 119)፣ ክቡር በሆኑ ነገሮች፣ በጎነት ወይም ምስጋና ባለባቸው ነገሮች የተሞላ ይሁን (*ፊል* 4፥8)::

(4) ምንጊዜም ቢሆን ዐይኖቻችሁ ስለሚያዩትና ጆሮዎቻችሁ ስለሚሰሙት ነገር ጥንቃቄ አድርጉ፤ እንደዚሁም (ሀ) ዐይኖቻችሁ የሥጋ ምኞት *መሣሪያ* እንዳይሆኑ (ኢዮ 31፥1፤ 1ዮሐ 2፥16)፣ (ለ) *መጽሐፍና መጽሔት* ስታነቡ፣ ስዕልና የቴሌቭዥን ፕሮግራም ስትመለከቱ ወይም ዕለታዊ ኑሮአችሁን ስትኖሩ (*መዝ* 101፥3፤ ኢሳ 33፥14-15፤ ሮሜ 13፥14) በዐይኖቻችሁ ፊት ከንቱ ወይም ክፉ ነገር እንዳይቀመጥ በቈራጥነት ተቃወሙ::

**10፥12 ራሳቸውን በራሳቸው ሲመዝኑ፤** ራሳችንን ዓለም ከሚጠቀምበት ከዘመኑ መለኪያና በዙሪያችን ካሉ አማኞች ሕይወት ጋር ካነጻጸርን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚገባ ገና እንዳላወቅን ያሳያል:: ራሳችንን የምንመዝንበት መለኪያ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በክርስቶስና በሐዋርያት ተገልጾአል::

[14]የክርስቶስን ወንጌል ይዘን ወደ እናንተ
በመጣን ጊዜ፣ ከተመደበልን የአገልግሎት
ወሰን አላለፍንም። [15]ደግሞም ሌሎች በደ
ከሙበት ሥራ ከመጠን በላይ በመመካት
ከተመደበልን ወሰን አናልፍም፤ ይልቁንም
እምነታችሁ እየደገ በሄደ ቍጥር በእናንተ
ዘንድ የተመደበልን አገልግሎት እየሰፋ እን
ደሚሄድ ተስፋ እናደርጋለን። [16]ስለዚህ በሌ
ላው ሰው ክልል አስቀድሞ በተሠራ ሥራ
ሳንመካ፣ ከእናንተ ወዲያ ባለው አገር ወን
ጌልን መስበክ እንችላለን። [17]ነገር ግን፣
"የሚመካ በጌታ ይመካ"፤ [18]ምክንያቱም ጌታ
ራሱ የሚያመሰግነው እንጂ፣ ራሱን በራሱ
የሚያመሰግን ተቀባይነት አይኖረውም።

## ጳውሎስና ሐሰተኞች ሐዋርያት

**11** ጥቂቱን ሞኝነቴን እንደምትታገሡኝ
ተስፋ አደርጋለሁ፤ በርግጥም
እየታገሣችሁኝ ነው። [2]በእግዚአብሔር ቅናት
እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት
ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ
ባል አጭቻችኋለሁና። [3]ነገር ግን እባብ
ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት
የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ
ካላችሁ ቅንነ ትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ
እሠጋለሁ። [4]ምክንያቱም አንድ ሰው
ወደ እናንተ መጥቶ እኛ ከሰበክንላችሁ
ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብ ክላችሁ፣ ወይም
ከተቀበላችሁት መንፈስ የተለየ መንፈስ
ብትቀበሉ ወይም ከተቀበላችሁት ወንጌል
የተለየ ወንጌል ብትቀበሉ፣ ነገሩን በዝምታ

10፥14 1ቆሮ3፥6፤
2ቆሮ2፥12
10፥15 ቍ13፤
ሮሜ15፥20፤
2ተሰ1፥3
10፥16
ሐሥ19፥21፤
ሮሜ1፥1፤
2ቆሮ2፥12
10፥17
መዝ34፥2፤
44፥8፤ ኤር9፥24፤
1ቆሮ1፥31
10፥18 ቍ12፤
ሮሜ2፥29
11፥1 ቍ4:16:
17:19:20:21፤
ማቴ17፥17፤
2ቆሮ5፥13
11፥2 ሆሴ2፥19፤
2ቆሮ4፥14፤
ኤፌ5፥26:27
11፥3 ዘፍ3፥1-
6:13፤
1ጢሞ2፥14፤
ራእ12፥9
11፥4 ቍ1፤
ሮሜ8፥15፤
1ቆሮ3፥11፤
ገላ1፥6-9
11፥5
2ቆሮ12፥11፤
ገላ2፥6
11፥6 1ቆሮ1፥17፤
2ቆሮ8፥7፤
ኤፌ3፥4
11፥7ሮሜ1፥1፤
1ቆሮ9፥18፤
2ቆሮ12፥13

ታልፉታላችሁ ማለት ነው። [5]እኔ ግን
"ታላላቅ ሐዋርያት" ከሚባሉት በምንም
የማንስ አይመስለኝም። [6]የንግግር ችሎታ
ባይኖረኝም እንኳ፣ ዕውቀት ግን አለኝ፤
ይህ ንንም በሁሉ መንገድ በሚገባ ግልጽ
አድር ገንላችኋል።

[7]እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን ዝቅ አድ
ርጌ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ዋጋ ለእ
ናንተ መስበኬ እንደ ኀጢአት ተቈጥሮብኝ
ይሆን? [8]እናንተን ለማገልገል ስል ከሌሎች
አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በመቀበሌ እነ
ርሱን ዘርፌአቸዋለሁ። [9]ከእናንተም ጋር
ሳለሁ አንዳች ባስፈለገኝ ጊዜ፣ ከመቄዶንያ
የመጡ ወንድሞች የሚያስፈልገኝን ስለ
ሰጡኝ ለማንም ሸክም አልሆንሁም። በእና
ንተ ላይ በምንም ነገር ሸክም እንዳልሆን
ተጠንቅቄአለሁ፤ ወደ ፊትም እጠነቀቃ
ለሁ። [10]የክርስቶስ እውነት በውስጤ እስካለ
ድረስ፣ በአካይያ አውራጃ ይህን ትምክሕ
ቴን ማንም ሊገታው አይችልም። [11]ይህን
የምለው ለምንድን ነው? ስለማልወዳችሁ
ነውን? እንደምወዳችሁ እግዚአብሔር ያው
ቃል። [12]ከእኛ ጋር እኩል ለመሆን በሥራ
ቸው እየተመኩ ቀን የሚጠብቁትን ሰዎች
ምክንያት ለማሳጣት አሁን የማደርገውን
ወደ ፊትም አደርጋለሁ።

[13]እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋ
ርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋውጡ፣

11፥8 ፊል4፥15:18 11፥9 2ቆሮ12፥ 13:14:16፤
ፊል4፥15:18 11፥10 ሐሥ18፥12፤ ሮሜ9፥1፤ 1ቆሮ9፥15
11፥11 ቍ31፤ ሮሜ1፥9፤ 2ቆሮ12፥15
11፥13 ማቴ7፥15፤ ቲቶ1፥10፤ ራእ2፥2

**11፥3 የእናንተም ልቡና … እንዳትወሰዱ፤** በቆሮንቶስ ያሉት አንዳንዶች በሐሰተኛ ሰባኪዎች ተታለው በመሳትና የተለየ ወንጌል በመቀበል ትልቅ ዐደጋ ላይ ነበሩ (ቍ 4)። እነርሱም የእነዚህን፣ “አታላዮች ሠራተኞች” (ቍ 13) ትምህርት በመቀበል፣ ሕይወትን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ከመስጠት ተንሸራተው በመሳት የተወሰዱ ናቸው። ዛሬ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት የጽድቅ አገልጋዮች ነን የሚሉ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፤ ይሁን እንጂ ትምህርታቸው የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረንና ተከታዮቻቸውንም ለመንፈሳዊ ውድቀት የሚዳርግ ነው (የሚቀጥሉትን ሁለት ማብራሪያዎች እንዲሁም ማቴ 23፥13 እና ማብ ይመ)። ራሳችንን ከእነርሱ መጠበቅ አለብን (በገጽ 1519 ላይ፣ *“የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች”* በሚል ርእስና በገጽ 1716 ላይ፣ *“የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው”* በሚል ርእስ የቀረቡትን ጽሑፎች ይመ)።

**11፥4 ቢሰብክላችሁ … የተለየ ወንጌል፤** የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ እውነተኛ እንደ ሆነ ሊናገሩ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በሌላ በኩል እነርሱም ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ልዩ መገለጥና ዕውቀት እንዳላቸው ያም ከቅዱሳት መጻሕፍት ያላነሰ ሥልጣን እንዳለውና ለቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ የሚጠቅም እንደ ሆነ ይናገራሉ። እንዲህ ዐይነቱ የሐሰት ትምህርት አብዛኛውን ጊዜ የክርስትና እምነት ከሌሎች ሃይማኖቶች ወይም ፍልስፍናዎች ጋር ተደባልቆ አብሮ እንዲጓዝ ያደርገዋል። ይህ የሚከተሉትን ስሕተቶች ያመጣል፤ (1) ተገኘ የተባለውን አዲሱን መገለጥ በክርስቶስ ለሐዋርያት ከተገለጠው ከመጀመሪያው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ እኩል የሥልጣን ደረጃ ላይ እንዲቀመጥ ያደርገዋል፤ (2) የመጽሐፍ ቅዱስን አስፈላጊነት ይቀንሳል፤ ክርስቶስንም፣ “ከቅዱሳን”፣ ከእንቅስቃሴ ጀማሪዎች ወይም ከቤተ ክርስቲያን መሥራቾች በታች በማድረግ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጠዋል፤ (3) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “ምስጢራዊ መገለጥ” ተብሎ የሚጠራውን ለመመርመር ጥልቅ ወይም ልዩ መረዳት እንዳላቸው አድርገው ይቈጥራሉ።

**11፥13 ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለዋውጡ … አታላዮች ሠራተኞች፤** ትልቁ አታላይ ሰይጣን (ቍ 3፤ ዮሐ 8፥44) ክፉ ሰዎችን “ሐሰተኛ ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተኞች” አድርጎ በመለወጥ ለዐላማው በመሣሪያነት ይጠቀምባቸዋል፤ (1) መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን አታላይ መሪዎች በሰይጣን ኀይል የተሞሉ እንደ ሆኑ በመግለጽ (ሀ) እግዚአብሔርን ለማገልገል ታላቅ ሥራ የሚሠሩ የሚመስሉ (ቍ 15፤ ራእ 13፥2)፣ (ለ) ማራኪ የወንጌል ስብከትን የሚሰብኩ (ቍ 4፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)፣ (ሐ) ጻድቃን የሚመስሉ ነገር ግን እግዚአብሔርን መፍራትን የሚቃወሙና ኀይሉን የሚክዱ (2ጢሞ 3፥5) እንደሆኑ ይናገራል።

(2) እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን “የክርስቶስ ሐዋርያት” እና “የጽድቅ አገልጋዮች” በማስመሰል ይለውጣሉ (ቍ 15)። ስለዚህ መልእክታቸው በተገኘው ሁኔታ ሁሉ ሃይማኖታዊ መልክን እንዲይዝ በማድረግ (2ጢሞ 3፥5) እውነተኛ

ሐሰተኞች ሐዋርያትና አታላዮች ሠራተ
ኞች ናቸው። 14ይህም የሚያስደንቅ ነገር
አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብ
ርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋወ
ጣል። 15እንግዲህየእርሱአገልጋዮች፣የጽድቅ
አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ
2ቆሮ 12፥7-10 የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም
እንደ ሥራቸው ይሆናል።

## ጳውሎስ በደረሰበት መከራ ይመካል

16እንደ ገና ይህን እላለሁ፤ ማንም ሰው
እንደ ሞኝ አይቍጠረኝ፤ እናንተም የምት
ቈጥሩኝ ከሆነ እኔም በጥቂቱ እንድመካ
እንደ ሞኝ ተቀበሉኝ። 17እንደዚህ ልበ
ሙሉ ሆኜ የምናገረው እንደ ሞኝ እንጂ
እንደ ጌታ ፈቃድ አይደለም። 18ብዙዎች
በዓለማዊ ነገር ስለሚመኩ እኔም ደግሞ
እመካለሁ። 19እናንተም ብልሆች ስለ
ሆናችሁ ሞኞችን በደስታ ትታገሣላችሁ፤
20ማንም ተነሥቶ ባሪያ ቢያደርጋችሁ፣
ቢበዘብዛችሁ፣ ለጥቅሙ ሲል ቢጠጋችሁ፣
ቢንቀባረርባችሁ ወይም ፊታችሁን በጥፊ
ቢመታችሁ ትታገሣላ ችሁ። 21እኛ ግን
ለዚያ እጅግ ደካሞች መሆ ናችንን እያፈርሁ
እናገራለሁ።

ማንም በድፍረት በሚመካበት ነገር ሁሉ
እኔም ደፍሬ መመካት እንደምችል እንደ
ሞኝ እናገራለሁ። 22እነርሱ ዕብራውያን ናቸ
ውን? እኔም ነኝ፤ እስራኤላውያን ናቸውን?
እኔም ነኝ፤ የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔም
ነኝ። 23የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን?
እንደ እብደ ሰው ልናገርና እኔ እበልጣቸዋ

11፥14 ማቴ4፥10
11፥15 ማቴ16፥27፤ ፊል3፥19
11፥16 ቍ1
11፥17 ቍ21፤ 1ቆሮ7፥12:25
11፥18 ቍ21፤ 2ቆሮ5፥16፤ 10፥4፤ ፊል3፥3:4
11፥19 ቍ1፤ 1ቆሮ4፥10
11፥20 ቍ1፤ ገላ2፥4፤ 4፥9፤ 5፥1
11፥21 ቍ17:18፤ 2ቆሮ10፥1፥10፤ ፊል3፥4
11፥22 ሉቃ3፥8፤ ሮሜ9:4፤ 11፥1፤
11፥22 ፊል3፥5 11፥23 ሐሥ16፥23፤ ሮሜ8፥36፤ 1ቆሮ3፥5፤ 15፥10፤ 2ቆሮ6፥4:5

---

የክርስቶስን አገልጋዮች ለመምሰል ይሞክራሉ:: በእውነተኝነት ሌሎችን የሚንከባከቡና የሚወዱ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይቅርታን፣ ሰላምን፣ ስኬትን፣ ፍቅርንና ሌሎች አያሌ ጠቃሚ ነገሮችንም ሊሰብኩ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሕይወታቸው በሰይጣን ቍጥጥር ሥር ነው:: ወንጌላቸው ብዙውን ጊዜ ሰብአዊ አስተሳሰብን የተመረኰዘ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ትርጓሜ የያዘ አይደለም (ከገላ 1፥6-7፤ ከ1ጴጥ 2፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ):: ትምህርታቸው ከአዲስ ኪዳኑ ሐዋርያዊ አስተምህሮ ያፈነገጠ ነው (1ዮሐ 4፥1 እና ማብ ይመ)::

(3) አማኞች ሁሉ ከእነዚህ አሳሳች አገልጋዮችና መሪዎች መጠንቀቅ አለባቸው (ቍ 3-4፤ ማቴ 7፥15፤ 16፥6)፤ እንዲሁም በማራኪነታቸው፣ በአንደበተ ርቱዕነታቸው፣ በትምህርታቸው፣ በታምር ሠሪነታቸው፣ ብዙ ተከታይ በማፍራታቸው ወይም ተወዳጅ በሆነ መልእክታቸው መታለል የለባቸውም::

(4) የሃይማኖት መሪዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለተገኘው ቤዛነት እንዲሁም በክርስቶስና በአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ለቀረበው ወንጌል ባላቸው አስተሳሰብና ታማኝነት መሠረት ሊመዘኑ ይገባል (ገላ 1፥9 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ ***"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

11፥23፤ ከዚህ ቍጥር እስከ ምዕራፉ መጨረሻ ያለው ክፍል የሐዋርያው ጳውሎስን ሥቃይ የሚያመለክት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያው ጳውሎስ በተናገረው ቃል ሙሉ በሙሉ ራሱን ለክርስቶስ፣ ለቃሉና ክርስቶስ ለሞተበት ዐላማ የሰጠ ሰው የሚደርስበትን ሐዘንና ሥቃይ ገልጾአል (በገጽ 744 ላይ፣ ***"የጻድቃን መከራ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ስሜት የሚያውቅ እንዲሁም የክርስቶስን ልብ የተረዳና የሐዘን ስሜቱን የተካፈለ ነበር:: ከዚህ ቀጥሎ ሐዋርያው የክርስቶስን ሥቃይ የተካፈላባቸው ሃያ መንገዶች ተዘርዝረዋል፤

(1) እግዚአብሔርን ሲያገለግል ባጋጠመው ከባድ ሥራ ብዙ ጊዜ መድከሙ (ሐሥ 14፥22)::

(2) ኅብረተሰቡን ባጥለቀለቀው ኀጢአት ምክንያት በታላቅ ሐዘን ውስጥ መግባቱ (ሐሥ 17፥16)::

(3) "በብዙ እንባ" እግዚአብሔርን ማገልገሉ (2፥4)::

(4) ለመጽሐፍ ቅዱሳዊና ለሐዋርያዊው እምነት ታማኝ ያልሆኑ አስተማሪዎች የተጣመመ ወንጌል በመስበካቸው ስለ ደረሰው ጥፋት "ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትና ቀን" ቤተ ክርስቲያንን ማስጠንቀቁ (ሐሥ 20፥31 እንዲሁም በገጽ 1716 ላይ፣ ***"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

(5) ከውድ ወንድሞቹ በመለየቱ መጨነቁ (ሐሥ 20፥17-38) እንዲሁም በዚሁ ምክንያት እነርሱ ሲያዝኑ ልቡ መሰበሩ (21፥13)::

(6) "ወንድሞቹ" የክርስቶስን ወንጌል ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በልቡ "ታላቅ ሐዘንና ጭንቀት" መኖሩ (ሮሜ 9፥2-3፤ 10፥1)::

(7) የክርስቶስን ሥራ ሲሠራ በእርሱ ላይ አያሌ ፈተናዎችና ችግሮች መድረሳቸው (4፥8-12፤ 11፥23-29፤ 1ቆሮ 4፥11-13)::

(8) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኀጢአት በቸልታ በመታለፉ ማዘኑ (2፥1-3፤ 12፥21፤ 1ቆሮ 5፥1-2፤ 6፥8-10)::

(9) ክርስቶስንና እውነተኛውን ወንጌል ለተዉት ሲጽፍ፣ "በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት" ውስጥ መሆኑ (2፥4)፡

(10) ወደ ክርስቶስ ለመሄድ እንዲሁም ከኀጢአትና ከዚህ ዓለም ጣጣ ነጻ ለመሆን በመሻት መቃተቱ (5፥1-4 ይመ፤ ከፊል 1፥23 ጋር ያነጻጽሩ)::

(11) ለቤተ ክርስቲያን ግብረገባዊና አስተምህሮአዊ ንጽሕና ራሱን ስለ ሰጠ "ከየአቅጣጫው መከራ" መቀበሉ (7፥5፤ 11፥3-4)::

(12) ዕለት ዕለት የአብያተ ክርስቲያናት ሐሳብ ሁሉ የሚያስጨንቀው መሆኑ (11፥28)::

(13) ወደ ኀጢአት ለሚነዱ ክርስቲያኖች በውስጡ መቈጨቱ (11፥29)::

(14) በአዲስ ኪዳን ከተገለጠው እምነት ውጭ የሆነን ወንጌል በሚሰብኩ ላይ ዘላለማዊ እርግማንን ማውረዱ (ገላ 1፥6-9)::

(15) ከጸጋ ለወደቁት ሴት ስትወልድ እንደምታምጥ ማማጡ (ገላ 4፥19፤ 5፥4)::

(16) የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ለሆኑት "እንባ" ማፍሰሱ (ፊል 3፥18)::

(17) አንዳንዶች በሚደርስባቸው ፈተና ከእምነት ይወድቁ እንደ ሆነ በመሥጋት መጨነቁ (1ተሰ 3፥5-8)::

ለሁ፤ ደግሞም ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአ
ለሁ፤ ብዙ ጊዜ ታስሬያለሁ፤ ብዙ ጊዜ
ተገ ርፌአለሁ፤ ብዙ ጊዜ ለሞት ተቃርቤአ
ለሁ። [24]አይሁድ ለአርባ ጅራፍ አንድ የቀ
ረው አምስት ጊዜ ገርፈውኛል። [25]ሦስት
ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፤ አንድ ጊዜ
በድንጋይ ተወግሬአለሁ፤ ሦስት ጊዜ የመር
ከብ አደጋ ደርሶብኛል፤ አንድ ሌሊትና ቀን
በባሕር ላይ አድሬአለሁ፤ [26]ብዙ ጊዜ በጒዞ
ተንከራትቻለሁ፤ ደግሞም ለወንዝ ሙላት
አደጋ፣ ለወንበዴዎች አደጋ፣ ለገዛ ወገኖቼ
አደጋ፣ ለአሕዛብ አደጋ፣ ለከተማ አደጋ፣
ለገጠር አደጋ፣ ለባሕር አደጋ እንዲሁም
ለሐሰተኞች ወንድሞች አደጋ ተጋልጬ
ነበር። [27]ብዙ ጥሬአለሁ፤ ብዙ ደክሜአለሁ፤
ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፤ ተርቤአለሁ፤
ተጠምቻለሁ፤ ብዙ ጊዜ ምግብ ሳልቀምስ
ኖሬአለሁ፤ በብርድና በራቁትነት ተቈራ
ምጃለሁ። [28]ሌላውን ነገር ሳልቈጥር፣ ዕለት
ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያ
ናት ሁሉ ሐሳብ ነው። [29]ደካማ ማን ነው?
እኔስ አብሬ አልደክምምን? በኀጢአት የሚ
ሰናከል ማን ነው? እኔስ አልቈጭምን?

[30]መመካት ካለብኝ፣ ደካማነቴን በሚያ
ሳዩ ነገሮች እመካለሁ። [31]ለዘላለም የተመ
ሰገነው የጌታ የኢየሱስ አምላክና አባት
እን ደማልዋሽ ያውቃል። [32]ደማስቆ ሳለሁ
ከን ጉሥ አርስጦስዮስ በታች የሆነው ገዥ
ሊይ ሲዘኝ ፈልጎ፣ የደማስቆ ሰዎችን ከተማ
ያስጠብቅ ነበር። [33]ነገር ግን በግንቡ መስ
ኮት በኩል በቅርጫት አውርደውኝ ከእጁ
አመለጥሁ።

11፥24 ዘዳ25፥3
11፥25 ሐሥ14፥19፤ 16፥22፤ 27፥1-44
11፥26 ሐሥ20፥3፤ 21፥31፤ ገላ2፥4
11፥27 ሐሥ18፥3፤ 1ቆሮ4፥11፡12፤ 2ቆሮ6፥5፤ ቈላ1፥29
11፥28 1ቆሮ7፥17
11፥29 ማቴ5፥29፤ ሮሜ14፥1፤ 1ቆሮ2፥3
11፥30 ቊ16፤ 1ቆሮ2፥3፤ 2ቆሮ12፥5፡9፤ ገላ6፥14
11፥31 ቊ11፤ ሮሜ1፥9፡25፤ 9፥5
11፥32 ሐሥ9፥24
11፥33 ሐሥ9፥25
12፥1 ቊ5፡7፡9፤ 1ቆሮ2፥10፤ 2ቆሮ11፥16፡30
12፥2 ቊ4፡ሐሥ8፥39፤ ሮሜ16፥3፤ 2ቆሮ11፥11፤ ኤፌ4፥10
12፥4 ቊ2፤ ሉቃ23፥43፤ ራእ2፥7
12፥5 ቊ9፡10፤ 1ቆሮ2፥3
12፥6 ቊ11፤

## ጳውሎስ ያየው ራእይና የተሰጠው መውጊያ

12 በመመካት የሚገኝ ጥቅም ባይኖ
ርም፣ መመካት ካስፈለገ ከጌታ
ወደ ተቀበልሁት ራእይና መገለጥ እመራ
ለሁ። [2]ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ
ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀ በክር
ስቶስ አንድ ሰው ዐውቃለሁ፤ የተነጠቀው
በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ አላው
ቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። [3]ይህ ሰው
በሥጋ ይሁን ወይም ከሥጋ ውጭ እኔ
አላውቅም፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፤ [4]እር
ሱም ወደ ገነት እንደ ተነጠቀ፣ በዚያም
በሰው አንደበት ሊገለጥ የማይችል፣ ሰውም
እንዲ ናገረው ያልተፈቀደለት ነገር ሰማ።
[5]እን ደዚህ ስላለው ሰው እመካለሁ፤ ስለ ራሴ
ግን ከደካማነቴ በስተቀር አልመካም። [6]መመ
ካት ብፈልግ እንኳ እንደ ሞኝ መቈጠር
የለብኝም፤ ምክንያቱም የምናገረው እውነት
ነው። ነገር ግን ማንም ስለ እኔ ከሚያየውና
ከሚሰማው በላይ እንዳይገምተኝ ከመመ
ካት እቈጠባለሁ።

[7]ከዚህ ታላቅ መገለጥ የተነሣ እንዳልታ
በይ የሥጋዬ መውጊያ፣ እርሱም የሚያሠ
ቃየኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ። [8]ይህ
ነገር ከእኔ እንዲወገድልኝ፣ ጌታን ሦስት
ጊዜ ለመንሁት፤ [9]እርሱ ግን፣ "ጸጋዬ ይበ
ቃሃል፤ ኀይሊ ፍጹም የሚሆነው በድካም

12፥6 2ቆሮ10፥8፤ 11፥16 12፥7 ቊ1፤ ዘኍ33፥55፤ ማቴ4፥10፤ 1ቆሮ2፥10 12፥8 ማቴ26፥39፡ 44 12፥9 1ነገ19፥12፤ ሮሜ3፥24፤ 1ቆሮ2፥3፤ ፊል4፥13

(18) ጽድቅን ከመውደዱና እግዚአብሔርን ለማክበር ከመፈለጉ የተነሣ መሰደዱ (2ጢሞ 3፥12)።

(19) በእስያ ያሉ አማኞች ስለ ተዉት ማዘኑ (2ጢሞ 1፥15)።

(20) የሚመጣውን ክሕደት አስመልክቶ ጢሞቴዎስ እውነተኛውን እምነት እንዲጠብቅ ያቀረበለት ጥብቅ ልመና (1ጢሞ 4፥1፤ 6፥20፤ 2ጢሞ 1፥14)።

**12፥2 በክርስቶስ አንድ ሰው፤** ሐዋርያው ጳውሎስ "በክርስቶስ አንድ ሰው" በማለት የተናገረው ስለ ራሱ ሲሆን፣ ይህም ምናልባት ስለ ክርስቶስ ወንጌልና አማኞች በመንግሥተ ሰማይ ሊቀበሉት ስላለው በቃል ሊገለጽ ስለማይቻለው ክብር ለመረዳት መገለጥን ይቀበል ዘንድ ወደ ሰማይ የተወሰደበትን ጊዜ ለማመልከት ነው (ቊ 7 ይመ፤ ከሮሜ 8፥18፤ ከ2ጢሞ 4፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ለሐዋርያው የተሰጠው ይህ ታላቅ ክብርና መገለጥ በሐዋርያዊው አገልግሎቱ ለረዥም ጊዜ በደረሰበት ከባድ ሥቃይ አበረታታው፤ ጽናትም ሆነው።

**12፥2 ሦስተኛው ሰማይ፤** መጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ሰማያት እንዳሉ ያመለክታል፤ (1) የመጀመሪያው ሰማይ በመሬት ዙሪያ ያለው ከባቢ አየር ነው (ሆሴ 2፥18፤ ዳን 7፥13)፤ (2) ሁለተኛው ሰማይ ከዋክብት ያሉበት ነው (ዘፍ 1፥14-18)፤ (3) ሦስተኛው ሰማይ ደግሞ ገነት ተብሎ የሚጠራው (ቊ 3-4፤ ሉቃ 23፥43፤ ራእ 2፥7) የእግዚአብሔር መኖሪያና በሞት የተለዩ አማኞች ቤት ነው (5፥8፤ ፊል 1፥23)። ይህኛው ሰማይ ያለበት ትክክለኛ ስፍራ አልተገለጠም።

**12፥7 የሥጋዬ መውጊያ፤** "መውጊያ" ወይም "እሾኽ" የሚለው ቃል ሕመምን፣ ችግርን፣ ሥቃይን፣ ውርደትን ወይም አካላዊ ደካማነትን የሚያመለክት እንጂ በኀጢአት መፈተንን አይደለም (ከገላ 4፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (1) የጳውሎስ መውጊያ ምን እንደ ሆነ ተለይቶ ስላልተገለጸ፣ "መውጊያ" ያለባቸው የዚህን ምንባብ መንፈሳዊ ትምህርት ከራሳቸው ሕይወት ጋር ሊያዛምዱት ይችላሉ፤ (2) የጳውሎስ መውጊያ ምንጩ የአጋንንት ሥራ ወይም መነሻው አጋንንት ራሱ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ይሁንታዊ ፈቃድ የሆነ ነው (ከኢዮ 2፥1 … ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) በሌላ በኩል ለጳውሎስ ይህ መውጊያ የተሰጠው በተቀበለው መገለጥ እንዳይታበይ ለማድረግ ይሆናል፤ (4) የጳውሎስ መውጊያ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጸጋ ላይ አብዝቶ እንዲመካ አድርጎታል (ቊ 9 እና ማብ፤ ዕብ 12፥10)።

**12፥8 ሦስት ጊዜ ለመንሁት፤** ብዙ ጊዜ በጥብቅ ለሚጸለይበት ጉዳይ እግዚአብሔር መልስ ካልሰጠ፣ የሚመጣው ነገር ይጸለይበት ከነበረው እጅግ የተሻለ ነው (የሚቀጥለውን ማብ ይመ፤ ኤፌ 3፥20)።

**12፥9 ጸጋዬ ይበቃሃል፤** ጸጋ የእግዚአብሔር ሀልዎት፣ የእግዚአብሔር ሞገስና ኀይል ነው። ይህም እግዚአብሔርን ለሚጠሩ የሚሰጥ ኀይልና ሰማያዊ ብርታት ነው። ይህ ጸጋ የሚያርፈው ድካማቸውንና የሚገጥማቸውን ችግር ስለ ወንጌል ሲሉ በሚቀበሉ ታማኝ በሆኑ አማኞች ላይ ነው (ፊል 4፥13፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (1) ስለ ክርስቶስ ስም ያለብን ድካምና መከራ ሲበዛ፣ ፈቃዱን እንድንፈጽም

ጊዜ ነውና" አለኝ። ስለዚህ የክርስቶስ ኀይል
በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ
በድካሜ እመካለሁ። 10ስለ ክርስቶስ በድ
ካም፣ በስድብ፣ በመከራ፣ በስደትና በጭን
ኤፌ ቀት ደስ የምሰኘው ለዚህ ነው፤ ስደክም ያን
6፥10-18 ጊዜ ብርቱ ነኝና።

## ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የነበረው ጭንቀት

11በመመካቴ ሞኝ ሆኛለሁ፤ ለዚህም ያበ
ቃችሁኝ እናንተ ናችሁ፤ ስለ እኔ መመስ
ከር የሚገባችሁ እናንተ ነበራችሁ። ደግ
ሞም እኔ ከምንም የማልቈጠር ብሆንም፣
"ታላላቅ ሐዋርያት" ከሚባሉት በምንም
አላንስም። 12የእውነተኛ ሐዋርያ ምልክቶች
በመካከላችሁ ተደርገዋል፤ እነርሱም በትዕ
ግሥት መጽናት፣ ምልክቶች፣ ድንቅ ነገሮ
ችና ታምራት ናቸው። 13በእናንተ ላይ ሸክም
ካለመሆኔ በቀር፣ ከሌሎች አብያተ ክርስ
ቲያናት በምን አነሳችሁ? ይህን በደሌን
ይቅር በሉኝ።

14ወደ እናንተ ለመምጣት ስዘጋጅ ይህ
ሦስተኛዬ ነው፤ ስመጣ በምንም ነገር ሸክም
አልሆንባችሁም፤ እኔ እናንተን እንጂ ከእ
ናንተ ምንም አልፈልግምና፤ ደግሞም ወላ
ጆች ለልጆች ገንዘብ ያከማቻሉ እንጂ ልጆች
ለወላጆች አያከማቹም። 15እኔ ግን ስለ እና
ንተ ያለኝን ሁሉ ራሴንም ጭምር ብሰጥ
ደስ ይለኛል፤ ታዲያ እኔ የምወዳችሁ ይህን
ያህል ከሆነ፣ እናንተ የምትወዱኝ በጥቂቱ
ነውን? 16የሆነው ሆኖ ሸክም አልሆንሁ
ባችሁም፤ ነገር ግን በተንኰልና በዘዴ ያጠ
መድኋችሁ ሳይመስላችሁ አልቀረ 17ለመ
ሆኑ ወደ እናንተ በላክኋቸው ሰዎች አማካ
ይነት በአንዱ እንኳ በዘበዝኋችሁን? 18ቲቶ
ወደ እናንተ እንዲመጣ ለመንሁት፤ ወን
ድማችንንም ከእርሱ ጋር ላክሁት። ቲቶ
በዘ በዛችሁን? ከእርሱ ጋር በአንድ መንፈስ
አልተመላለስንምን? አካሄዳችንስ አንድ
አልነበረምን?

19እስከ አሁን ድረስ በእናንተ ፊት ራሳ
ችንን ስንከላከል የኖርን ይመስላችኋልን?
በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት እንናገራ
ለን፤ ደግሞም ወዳጆች ሆይ፤ ይህን ሁሉ
የምናደርገው እናንተን ለማነጽ ነው። 20ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ፣ እኔ እንደምፈል
ገው ሆናችሁ ላላገኛችሁ እችላለሁ ወይም
እናንተ እንደምትፈልጉኝ ሆኜ ላታገኙኝ
ትችላላችሁ ብዬ እፈራለሁ፤ ምናልባትም
በመካከላችሁ ጥል፣ ቅናት፣ ቍጣ፣ አድመ
ኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፣ እብሪትና
ሁከት ይኖራል ብዬ እሠጋለሁ። 21ዳግመ
ኛም ስመጣ አምላኬ በእናንተ ፊት ያዋር
ደኝ ይሆን ብዬ እፈራለሁ፤ ይኸውም ብዙ
ዎች ከዚህ በፊት ስለሠሩት ኀጢአትና ስለ
ፈጸሙትም ርኵሰት፣ ዝሙትና መዳራት
ንስሓ ሳይገቡ ቀርተው እንዳላዝን ነው።

## የመጨረሻ ምክር

13 ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተኛዬ
መሆኑ ነው፤ "ማንኛውም ነገር
በሁለት ወይም በሦስት ምስክር ይጸናል።"
2በሁለተኛው ጕብኝቴ እናንተ ዘንድ በነበር
ሁበት ጊዜ አስጠንቅቄአችሁ ነበር፤ አሁንም
በሩቅ ሆኜ እንደ ገና አስጠነቅቃችኋለሁ፤

12፥10 ማቴ5፥12፤ 2ቆሮ6፥4፤ 13፥4፤ 2ተሰ1፥4
12፥11 1ቆሮ15፥9:10፤ 2ቆሮ11፥1:5
12፥12 ዮሐ4፥48
12፥13 ቍ14፤ 1ቆሮ9፥12:18፤ 2ቆሮ11፥7
12፥14 ምሳ19፥14፤ 1ቆሮ4፥14:15፤ 2ቆሮ13፥1
12፥15 2ቆሮ11፥11፤ ፊል2፥17፤ 1ተሰ2፥8
12፥16 2ቆሮ11፥9
12፥18 2ቆሮ2፥13፤ 8፥6:16:18
12፥19 ሮሜ9፥1፤ 14፥19፤ 1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ10፥8
12፥20 ሮሜ1፥29:30፤ 1ቆሮ1፥11፤ 3፥3፤ 4፥18:21፤ 14፥33፤ 2ቆሮ2፥1-4፤ ገላ5፥20
12፥21 1ቆሮ6፥18፤ 2ቆሮ2፥1:4፤ 13፥2
13፥1 ዘዳ19፥15፤ ማቴ18፥16፤ 2ቆሮ12፥14
13፥2 ቍ10፤ 2ቆሮ1፥23፤ 12፥21

---

እግዚአብሔር ጸጋውን ያበዛልናል:: የሚሰጠንም ጸጋ የዕለት ኑሮአችንን ለማሸነፍ፣ እርሱን ለማገልገል፣ ሥቃያችንንና የሥጋ መውጊያችንን ለመታገሥ ሁልጊዜ የሚያስችል ብቃት አለው (ከ1ቆሮ 10፥13 ጋር ያጸጽሩ):: ወደ ክርስቶስ በቀረብን ቍጥር፣ እርሱ ሰማያዊ ብርታቱንና ማጽናናቱን ይሰጠናል፤ (2) በድካማችን ልንመካና ዘላለማዊ ፋይዳውን ልንመለከት ይገባናል፤ ምክንያቱም ወደ ሰማያዊ ቤታችን የሕይወት ጕዞ ስናደርግ ድካማችን የክርስቶስ ኀይል በላያችን እንዲያርፍ፣ በውስጣችንም እንዲኖር ያደርጋል::

**12፥15 እኔ ... ያለኝን ሁሉ ራሴንም ጭምር ብሰጥ ደስ ይለኛል፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎች ያለው ፍጹም ፍቅር ለእረኞች፣ ለአስተማሪዎችና ለወንጌል መልእክተኞች ሁሉ ትልቅ ምሳሌ ነው:: አንድ አባት ለልጆቹ የሚገልጸውን ፍጹም ፍቅር (ከ6፥11-13፤ 7፥1-4 ጋር ያነጻጸሩ) የሚመስል ነው:: ስለ ሌላው ለመኖር የተቻለውን ያህል ጥረት ለሚያደርግ የተዘጋጀ ፍቅር ነው፤ እንዲህ ዐይነቱ ፍቅር ስለራሱ የሚያስብ ሳይሆን፣ በሥሩ ላሉት ለሌሎች ግድ የሚለው እውነተኛ ፍቅር ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ ለገለጸው ፍቅር ከራሱ ጥቅም አንጻር ምንም ምላሽ አልፈለገም፤ ነገር ግን የእርሱ ፍላጎት ፍቅሩን የገለጸላቸው ሰዎች ልብ ወደ ክርስቶስ ዘወር እንዲል ነበር:: ታማኝ የሆነ ማንኛውም የወንጌል አገልጋይ እንዲህ ዐይነቱ ፍቅር ሊኖረው ይገባል::

**12፥20 ስም ማጥፋት፣ ሐሜት፤** ክርስቲያናዊ የሆነውን የፍቅር ሕግ በመቃወም ሌሎች ሰዎች እንዲጐዱ የሚያደርገውን የንግግር ኀጢአት መጽሐፍ ቅዱስ ያወግዛል:: የሌላውን ሰው ባሕርይ ዝቅ የሚያደርግ ማንኛውም የንቀት ንግግር ሊወገዝ ይገባል:: ሌላው ሰው የተሳሳተበትን ድርጊት አንሥቶ መነጋገር ወይም መግለጽ ተገቢ የሚሆነው፣ አጥፊውን ሰው በመርዳት ለመመለስ ወይም ሌሎችንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመጠበቅ በቅን ልቦና ሲደረግ ነው (ሮሜ 1፥29፤ ኤፌ 4፥31፤ 2ጢሞ 4፥10:14-15፤ 1ጴጥ 2፥1)::

**12፥21 ብዙዎች ከዚህ በፊት ስለ ሠሩት ኀጢአት ... እንዳላዝን፤** ክርስቲያን አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ያሉ ብዙዎች ስለሠሩት ኀጢአት ንስሓ ለመግባት ባይፈቅዱና ኀጢአታቸውን ባይተዉ በመንፈሳዊ ረገድ ሙታን ናቸውና ሊያዝኑላቸው ይገባል:: ለእነርሱ የተላለፈው እጅግ አሳዛኙ መልእክት ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች (1ቆሮ 6፥9)፣ ለገላትያ ሰዎች (ገላ 5፥21) እና ለኤፌሶን ሰዎች (ኤፌ 5፥5-6) የተናገረው ቃል ነው፤ ይኸውም ከእግዚአብሔር መንግሥት እንደወጡ የሚገልጸው የውግዘት ቃል ነው::

**13፥2 አልራራላቸውም፤** አንድ አገልጋይ ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር የሚገልጸው መልካም ቃል በመናገር ብቻ ሳይሆን የግሣጼ ቃልንም ይጨምራል (12፥15 እና ማብ ይመ):: ትዕግሥት የራሱ የጊዜ ገደብ አለው፤ ይኸውም የቤተ ክርስቲያንን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲመጣ ለጥፋተኞች ርኅራኄ ሊደረግላቸው አይገባም:: የሰውን ፍላጎት ለማርካት

ወደ እናንተም ተመልሼ ስመጣ ከዚህ በፊት
ኀጢአት ለሠሩትም ሆነ ለሌሎች አልራራላ
ቸውም፤ 3ይህም የሚሆነው ክርስቶስ በእኔ
አድሮ እንደሚናገር ማስረጃ በመፈለጋችሁ
ነው። እርሱም በመካከላችሁ ብርቱ እንጂ
ደካማ አልነበረም። 4የተሰቀለው በድካም
ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ኀይል ሕያው ሆኖ
ይኖራል። እኛም በእርሱ ደካሞች ብንሆንም፣
እናንተን ለማገልገል ግን በእግዚአብሔር ኀይል
ከእርሱ ጋር ሕያዋን ሆነን እንኖራለን።
5በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳች
ሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ። ከፈር
የወጣችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ ኢየሱስ ክር
ስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን?
6እኛ ግን ብቁ መሆናችንን እንደምትገነ
ዘቡ ተስፋ አደርጋለሁ። 7አሁንምምንም
ክፉ ነገር እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እን
ጸልያለን፤ የምንጸልየውም እኛ ብቁዎች
እንደሆንን ሰዎች እንዲያዩልን አይደለም፤
ነገር ግን እኛ ምንም እንኳ ብቁዎች ባንሆ
ንም እናንተ መልካም የሆነውን ነገር እንድ
ታደርጉ ነው። 8ለእውነት እንጂ በእውነት
ላይ ምንም ማድረግ አንችልምና። 9እኛ

13፥3
ማቴ10፥20፤
1ቆሮ5፥4
13፥4 ቆላ9፤
ሮሜ1፥4፤ 6፥4፤
6፥5፤ 1ቆሮ1፥25፤
2፥3፤ 6፥14፤
ፊል2፥7፡8፤
1ጴጥ3፥18
13፥5 ሰቆ3፥40፤
ዮሐ 6፥6፤
ሮሜ8፥10፤
1ቆሮ11፥28
13፥9 ቆላ11፤
1ቆሮ2፥3፤
2ቆሮ2፥3፤ 4፥12፤
ኤፌ4፥13
13፥10
2ቆሮ1፥23፤ 10፥8
13፥11 ማር9፥50፤
ሮሜ15፥33፤
ኤፌ6፥23፤
1ተሰ4፥1፤
2ተሰ3፥1፤
1ዮሐ4፥16
13፥12
ሮሜ16፥16
13፥13 ፊል4፥22

ደካሞች ስንሆን፣ እናንተ ግን ብርቱዎች
ስትሆኑ ደስ ይለናል፤ ጸሎታችንም እናንተ
ፍጹማን እንድትሆኑ ነው። 10ከእናንተ ርቄ
ሳለሁ እነዚህን ነገሮች የምጽፍላችሁ ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ ሥልጣኔን በኀ
ይል እንዳልጠቀም ነው፤ ጌታም ይህን ሥል
ጣን የሰጠኝ እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍ
ረስ አይደለም።

## የመጨረሻ ሰላምታ

11በተረፈ ወንድሞች ሆይ፤ ደኅና ሁኑ።
ፍጹማን ሁኑ፤ ምክሬን ስሙ፤ አንድ ሐሳብ
ይኑራችሁ፤ በሰላምም ኑሩ። የፍቅርና የሰላ
ምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።
12በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ
ሰላምታ ተሰጣጡ። 13ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል።
14የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣
የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም
ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

13፥14 ሮሜ5፥5፤ 16፥20፤ 2ቆሮ8፥9፤ ፊል2፥1፤
ይሁ1፥21

---

ሲባል ልል ከመሆን ይልቅ ቅድስና የተሞላበት የጽድቅ ቀኑጣ ያስፈልጋል።

**13፥5 በእምነት መሆናችሁን ለማወቅ ራሳችሁን መርምሩ፤** አማኞች የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው እርግጠኛ ከመሆን የበለጠ ዕውቀት አያስፈልጋቸውም (ከ1ዮሐ 5፥13 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 17፥3 እና ማብ ይመ)። ክርስቲያን እንደሆኑ የሚናገሩ አማኞች በሙሉ ድነታቸው አሁን እውን መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ራሳቸውን መመርመር ያስፈልጋቸዋል (በገጽ 2030 ላይ፣ *"የድነት ዋስትና"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**13፥14 ጸጋ ... ፍቅር ... ኅብረት፤** የሐዋርያው ጳውሎስ የቡራኬ ቃል የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በሥላሴ ላይ ያላትን እምነት ይመሰክራል። ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናን የሚከተሉትን ነገሮች እንዲለማመዱ ይጸልያል፤ (1) የክርስቶስን ጸጋ፤ ይኸውም ቅርበቱን፣ ኀይሉን፣ ምሕረቱንና ማጽናናቱን ነው፤ (2) ከበረከቶቹ ሁሉ ጋር የእግዚአብሔርን አባታዊ ፍቅር እና (3) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊኖር የሚገባ ጥብቅ ኅብረት። እነዚህ ሦስትዮሽ እውነታ የያዙ በረከቶች በዘላቂነት በሕይወታችን የሚታዩ ከሆነ ያለን የዘላለም ድነት የተረጋገጠ ይሆናል።

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## (ሀ) መንፈስ ቅዱስ ከፍጥረትና ከአስተርእዮ ጋር ያለው ግንኙነት

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 1. በፍጥረት ሥራ ውስጥ ነበር | ዘፍ 1፥2፤ ኢዮ 33፥4 |
| 2. ለእግዚአብሔር ፍጥረታት ሕይወትን ይሰጣል | ዘፍ 2፥7፤ ኢዮ 33፥4፤ መዝ 104፥30 |
| 3. ነቢያትንና ሐዋርያትን ለእግዚአብሔር ሥራ ያነሣሣል | ዘኍ 11፥29፤ ኢሳ 59፥21፤ ሚክ 3፥8፤ ዘካ 7፥12፤ 2ጢሞ 3፥16፤ 2ጴጥ 1፥21 |
| 4. በቃሉ ይናገራል | 2ሳሙ 23፥1-2፤ ሐሥ 1፥16-20፤ ኤፌ 6፥17፤ ዕብ 3፥7-11፤ 9፥8፤ 10፥15 |

## (ለ) መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለው ግንኙነት

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 1. ኢየሱስ በማርያም ማኅፀን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ተጸነሰ | ማቴ 1፥18፡20-23፤ ሉቃ 1፥34-35 |
| 2. በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ | ማቴ 3፥16-17፤ ማር 1፥12-13፤ ሉቃ 3፥21-22፤ 4፥1 |
| 3. በመንፈስ ቅዱስ ሰበከ | ኢሳ 11፥2-4፤ 61፥1-2፤ ሉቃ 4፥16-27 |
| 4. በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ታምራትን አደረገ | ኢሳ 61፥1፤ ማቴ 12፥28፤ ሉቃ 11፥20፤ ሐሥ 10፥38 |
| 5. አማኞችን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃል | ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥8፤ ሉቃ 3፥16፤ ዮሐ 1፥33፤ ሐሥ 1፥4-5፤ 11፥16 |
| 6. መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ ሆኖ እንደሚመጣ ቃል ገብቶአል | ዮሐ 14፥16-18፡25-26፤ 15፥26-27፤ 16፥7-15 |
| 7. መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ እንደሚፈስ ቃል ገብቶአል | ዮሐ 7፥37-39 |
| 8. ራሱን ለአማኞች በመንፈስ ቅዱስ ይገልጣል | ዮሐ 16፥13-15 |
| 9. በመንፈስ ቅዱስ ራሱን ለመስቀል ሞት አሳልፎ ሰጠ | ዕብ 9፥14 |
| 10. በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ከሞት ተነሣ | ሮሜ 1፥3-4፤ 8፥11 |
| 11. መንፈስ ቅዱስን ከአብ ተቀበለ | ዮሐ 16፥5-14፤ ሐሥ 2፥33 |
| 12. በአማኞች ላይ መንፈስ ቅዱስን አፈሰሰ | ሐሥ 2፥33፡38-39 |
| 13. በመንፈስ ቅዱስ ከፍ ከፍ አለ | ዮሐ 16፥13-14 |
| 14. መንፈስ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ይጸልያል | ራእ 22፥17 |

## (ሐ) መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 1. ቤተ መቅደሱ እንደመሆኗ መጠን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኖራል | 1ቆሮ 3፥16፤ ኤፌ 2፥22፤ ከሐጌ 2፥5 ጋር ያነጻጽሩ |

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## (ሐ) መንፈስ ቅዱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት (ከለፈው የቀጠለ)

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 2. በቤተ ክርስቲያን ላይ እንደ ዝናም ይወርዳል | ሐሥ 1፥5፤ 2፥1-4፡16-21፤ ከኢሳ 32፥15፤ 44፥3፤ ከሆሴ 6፥3፤ ከኢል 2፥23-32 ጋር ያነጻጽሩ |
| 3. ለቤተ ክርስቲያን ይናገራል | ራእ 2፥7፡11፡17፡27፤ 3፥6፡13፡22 |
| 4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ኅብረት ይፈጥራል | 2ቆሮ 13፥14፤ ፊል 2፥1 |
| 5. ቤተ ክርስቲያንን አንድ ያደርጋል | 1ቆሮ 12፥13፤ ኤፌ 4፥4 |
| 6. ስጦታዎችን ለቤተ ክርስቲያን ይሰጣል | ሮሜ 12፥6-8፤ ኤፌ 4፥11፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ ገጽ 40 |
| 7. በመለኮታዊ መገለጦች ቤተ ክርስቲያንን ያንጻል | ሐሥ 4፥30-33፤ 1ቆሮ 12፥7-13፤ 14፥1-33 |
| 8. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይሾማል | ሐሥ 20፥28፤ ኤፌ 4፥11፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ ገጽ 40 |
| 9. መንፈስ ቅዱስን በተሞሉ ሰዎች ይሠራል | ሐሥ 6፥3፡5፡8፤ 8፥6-12፤ 15፥28፡32 ይመ፤ ከዘኍ 27፥18፤ ከመሳ 6፥34፤ ከ1ሳሙ 16፥13፤ ከዘካ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ |
| 10. ሰባኪዎችን በኀይል ያስታጥቃል | 1ቆሮ 2፥4 |
| 11. የእግዚአብሔርን ሰዎች ለወንጌል አገልግሎት ይልካል | ሐሥ 13፥2-4 |
| 12. የወንጌል ተልእኮን ሥራ ይመራል | ሐሥ 8፥29፡39፤ 16፥6-7፤ 20፥23 |
| 13. ቤተ ክርስቲያንን ከስህተት ይጠብቃል | 2ጢሞ 1፥14 |
| 14. ክሕደትን በተመለከተ ለቤተ ክርስቲያን ማስጠንቀቂያን ይሰጣል | 1ጢሞ 4፥1፤ ከነህ 9፥30 ጋር ያነጻጽሩ |
| 15. ቤተ ክርስቲያንን ለመንፈሳዊ ውጊያ ያስታጥቃል | ኤፌ 6፥10-18 |
| 16. ክርስቶስን ያከብራል | ዮሐ 16፥13-15 |
| 17. የጽድቅ ሕይወት እንዲኖሩበት ያደርጋል | ሮሜ 14፥17፤ ኤፌ 2፥21-22፤ 3፥16-21፤ 1ተሰ 4፥7-8 |

## (መ) መንፈስ ቅዱስ ከአማኝ ጋር ያለው ግንኙነት

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 1. በአማኝ ሕይወት ውስጥ ይኖራል | ሮሜ 8፥11፤ 1ቆሮ 6፥15-20፤ 2ቆሮ 3፥3፤ ኤፌ 1፥13፤ ዕብ 6፥4፤ 1ዮሐ 3፥24፤ 4፥13 |
| 2. ስለ ኀጢአታችን ይወቅሰናል | ዮሐ 16፥7-11፤ ሐሥ 2፥37 |
| 3. ዳግም ልደት እንድናገኝ ያደርጋል | ዮሐ 3፥5-6፤ 14፥17፤ 20፥22፤ ሮሜ 8፥9፤ 2ቆሮ 3፥6፤ ቲቶ 3፥5 |

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## (መ) መንፈስ ቅዱስ ከአማኝ ጋር ያለው ግንኙነት (ካለፈው የቀጠለ)

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 4. የእግዚአብሔርን ፍቅር ወደ እኛ ያስተላልፋል | ሮሜ 5፥5 |
| 5. እግዚአብሔር አባታችን እንደ ሆነ እንድናውቅ ያደርገናል | ሮሜ 8፥14-16፤ ገላ 4፥6 |
| 6. "ኢየሱስ ጌታ ነው" እንድንል ያስችለናል | 1ቆሮ 12፥3 |
| 7. ክርስቶስን ለእኛ ይገልጥልናል | ዮሐ 15፥26፤ 16፥14-15፤ 1ቆሮ 2፥10-11 |
| 8. የእግዚአብሔርን እውነት ይገልጥልናል | ነህ 9፥20፤ ዮሐ 14፥16-17:26፤ 16፥13-14፤ 1ቆሮ 2፥9-16 |
| 9. እውነትን ከስሕተት እንድንለይ ያስችለናል | 1ዮሐ 4፥1-3 |
| 10. ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት እንድንገባ ያደርገናል | 1ቆሮ 12፥13 |
| 11. ለሚለምኑ ሁሉ ይሰጣል | ሉቃ 11፥13 |
| 12. ወደ ክርስቶስ አካል ያጠምቀናል | 1ቆሮ 12፥13 |
| 13. በክርስቶስ የተጠመቅነው ወደ እርሱ ነው | ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥8፤ ሉቃ 3፥16፤ ዮሐ 1፥33፤ ሐሥ 1፥4-5፤ 11፥16 |
| 14. ይሞላናል | ሉቃ 1፥15:41:67፤ ሐሥ 2፥4፤ 4፥8:31፤ 6፥3-5፤ 7፥55፤ 11፥24፤ 13፥9:52፤ ኤፌ 5፥18፤ ከዘፀ 31፥3፤ ከመሳ 14፥19፤ ከ1ሳሙ 10፥10 ጋር ያነጻጽሩ |
| 15. እንመሰክር ዘንድ ኀይልንና ድፍረትን ይሰጠናል | ሉቃ 1፥15-17፤ 24፥47-49፤ ሐሥ 1፥8፤ 4፥31፤ 6፥9-10፤ 19፥6፤ ሮሜ 9፥1-3 |
| 16. ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ይሰጠናል | ማር 16፥17-18፤ 1ቆሮ 1፥7፤ 12፥7-11፤ 1ጴጥ 4፥10-11፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ ገጽ 40 |
| 17. ራእይንና ትንቢትን ይሰጣል | ኢዩ 2፥28-29፤ ሐሥ 2፥17-18፤ 10፥9-22፤ 1ቆሮ 14፥1-5:21-25 |
| 18. ፍሬውን በውስጣችን ያበዛል | ሮሜ 14፥17፤ 1ቆሮ 13፤ ገላ 5፥22-23፤ 1ተሰ 1፥6 |
| 19. ቅድስናን የተሞላ ሕይወት እንዲኖረን ያደርጋል | መዝ 51፥10-12፤ 143፥10፤ ሕዝ 11፥19-20፤ 37፥26፤ ሮሜ 8፥4-10፤ 15፥16፤ ገላ 5፥16-18:25፤ ፊል 2፥12-13፤ 2ተሰ 2፥13፤ 1ጴጥ 1፥2 |
| 20. ከኀጢአት ኀይል ነጻ ያወጣናል | ሮሜ 8፥2፤ ኤፌ 3፥16 |
| 21. ሰይጣንን በእግዚአብሔር ቃል እንድንዋጋው ያስችለናል | ኤፌ 6፥17 |
| 22. በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንድንናገር ይረዳናል | ማቴ 10፥17-20፤ ማር 13፥11፤ ሉቃ 12፥11-12 |
| 23. መጽናናትንና ብርታትን ይሰጠናል | ዮሐ 14፥17-18:26-27፤ ሐሥ 9፥31 |

# የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

## (መ) መንፈስ ቅዱስ ከአማኝ ጋር ያለው ግንኙነት (ካለፈው የቀጠለ)

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 24. እንድንጸልይ ይረዳናል | ሐሥ 4፥23-24፤ ሮሜ 8፥26፤ ኤፌ 6፥18፤ ይሁ 20 |
| 25. እንድናመልክ ያደርገናል | ዮሐ 4፥23-24፤ ሐሥ 10፥46፤ ኤፌ 5፥18-19፤ ፊል 3፥3 |
| 26. ኀጢአት ስንሠራ ያዝናል | ዘፍ 6፥3፤ ኤፌ 4፥30፤ ከማቴ 12፥31-32 ጋር ያነጻጽሩ |
| 27. የፍጹም ቤዛነታችን ዋስትና ነው | 2ቆሮ 1፥22፤ 5፥5፤ ኤፌ 1፥13-14 |
| 28. የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እንድንናፍቅ ያደርገናል | ሮሜ 8፥23፤ ራእ 22፥20 |
| 29. ሟች ለሆነው ሥጋችን ሕይወትን ይሰጣል | ሮሜ 8፥11 |

## (ሠ) መንፈስ ቅዱስ ከኀጢአተኞች ጋር ያለው ግንኙነት

| ሥራ | ማገናዘቢያ ጥቅሶች |
|---|---|
| 1. ስለ ኀጢአት፣ ስለጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል | ዮሐ 16፥7-11 |
| 2. አማኞች ለኀጢአተኞች ወንጌል ይሰብኩ ዘንድ ይልካቸዋል | ሐሥ 1፥8፤ 2፥17፡21፤ 4፥31፤ 11፥12-18፤ 13፥1-4 |
| 3. የወንጌልን የማዳን እውነት ይገልጣል | ሉቃ 4፥18-19፤ ዮሐ 15፥26-27፤ ሐሥ 4፥8፤ 11፥15፡18፤ 14፥3፤ 1ቆሮ 2፥4፡12፤ 1ተሰ 1፥5 |